ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ሐሙስ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 075 ኅዳር 15 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






# የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ ትግራይ ክልል አቋርጦ የቆየውን በረራ ሊጀምር ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ ትግራይ ክልል ተቋርጦ የቆየውን መደበኛ በረራ ለመጀመር በዝግጅት ላይ መሆኑን የአየር መንገዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ መስፍን ጣሰው ተናገሩ።

አየር መንገዱ ለዳግም በረራ መዘጋጀቱ በክልሉ የሰብዓዊ ድጋፍ ተደራሽነትን ለማሳለጥ ወሳኝ ሚና እንዳለው ተገልጿል።

በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የተደረሰውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ መንግሥት ወደ ትግራይ ክልል ሰብዓዊ ድጋፍን በስፋት ተደራሽ ለማድረግ በቁርጠኝነት እንደሚሠራ መግለጹ ይታወሳል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈጻሚ መስፍን ጣሰው፤ በመንግሥትና ሕወሓት መካከል የተደረሰውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ ወደ ትግራይ ክልል ተቋርጦ የቆየውን መደበኛ በረራ ለመጀመር ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

አስቀድሞ ወደ አካባቢው በየቀኑ በርካታ በረራዎች እንደነበሩ አስታውሰው፤ ከክስተቱ በኋላ ግን አገልግሎቱ መቋረጡን ተናግረዋል።

አየር መንገዱ የአገር ውስጥ በረራ ከሚያደርግባቸው በርካታ መዳረሻዎች መካከል የትግራይ ክልል አንዱ

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በክልሉ የዘንድሮ የመኸር ምርት 15 በመቶ ጭማሪ እንደሚገኝ ተገለፀ

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ ፡- በዘንድሮ የመኸር ምርት ከአስር እስከ አስራ አምስት በመቶ ጭማሪ እንደሚገኝ የሲዳማ ክልል አስታወቀ፡፡ የአረንጓዴ አሻራ ልማት ለምርት መጨመር የበኩሉን አስተዋፅዖ ማበርከቱም ተጠቁሟል፡፡

የሲዳማ ክልል የግብርና እና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ ኃላፊ አቶ መስፍን ቀሬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ክልሉ በዘንድሮ መኸር ምርት ከአስር እስከ አስራ አምስት በመቶ ጭማሪ እንደሚያሳይ ይጠበቃል፡፡

ዘንድሮ በዘር የተሸፈነው ማሳ መጠን ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር ከ83 ሺህ ሄክታር ወደ 91 ሺህ 222 ሄክታር አድጓል ያሉት ቢሮ ኃላፊው፤ ከዚህም ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅ ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ መስፍን ገለጻ፤ በምርት ዘመኑ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ 72 ሺህ ኩንታል ማዳበሪያ መጠቀም ተችሏል፡፡ ከዚህም ባሻገር የማዳበሪያ እጥረትን ለመሸፈን 133 ሺህ ቶን ኮምፖስት በመጠቀም ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ጥረት ተደርጓል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በማሳ ላይ የሚገኘው ሰብል ግማሹ እያሸተና ከፊሉም በእድገት ደረጃ ላይ ስለሚገኝ ክልሉ ዘግይቶ ወደ ሰብል መሰብሰብ እንደሚገባ ገልጸው



**በመኸር እርሻ ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል**

የሰብል ምርታማነትን የሚያጠቁ እንደ ቢጫ ዋግ ያሉ በሽታዎችን የመከላከል ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡ የአፈር አሲዳማነትን ለመከላከል ከ13 ሺህ ኩንታል በላይ ኖራ መጠቀም መቻሉንም ጠቁመዋል፡፡

በበጋ መስኖ እርሻ ተግባራዊ ለማድረግ ለልማት ሠራተኞች ስልጠና በመስጠት ንቅናቄ መደረጉን ቢሮ ኃላፊው ገልጸው ክልሉ በበጋ መስኖ እርሻ 67 ሺህ ሄክታር በዘር ለመሸፈን አቅዷል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

ከታቀደውም እርሻ 10ሺህ ሄክታር በስንዴ የሚሸፈን

በክልሉ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል









**‹‹የሕወሓት ታጣቂ በአጭር ጊዜ ትጥቅ ፈትቶ ወደ ካምፕ እንዲሰባሰብ እየተሰራ ነው››**

- ሌተናል ጀኔራል ታደሰ ወረደ

ገጽ 4




**የሕዝብ እምባ ጠባቂ ተቋም አንድ ሺህ 270 የበደል ቅሬታዎችን መቀበሉን አስታወቀ**



ገጽ 4

## በመጪዎቹ ሁለት ዓመታት 10 ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ ይሆናሉ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት የመጀመሪያው ትውልድ የሆኑ 10 ዩኒቨርሲቲዎች ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር እንደሚጀምሩ ትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ።

በትምህርት ሚኒስቴር የአስተዳደርና መሠረታዊ ጉዳዮች ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ሰለሞን አብርሃ እንደተናገሩት፤ እየተደረጉ ያሉ የለውጥ ሥራዎች የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ የተቀመጠውን ፍኖተ ካርታ መሠረት ያደረጉ ናቸው።

ዩኒቨርሲቲዎችን ራስ ገዝ ማድረግ ከሪፎርም ሥራዎቹ አንዱ ተግባር መሆኑን የጠቀሱት ዶክተር ሰለሞን፣ ለዚህም የአሠራር ሥርዓቶች፣ የሕግ ማዕቀፎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተዘጋጅተዋል ብለዋል።

ከጥቂት ወራት በኋላ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ራሱን ችሎ እንደሚተዳደርና በዚህም የሚሰጠውን ተልዕኮ በአግባቡ መፈጸም የሚያስችል አቅም በመፍጠር ጥራት ያለው የትምህርትና የምርምር ሥራ ያከናውናል ብለዋል።

የኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ታሪክ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር የተሳሰረ ነው ያሉት ዶክተር ሰለሞን፤ አሁን ካለው አቅምና የትምህርት ፕሮግራሞች አንጻር ራስ ገዝ ለማድረግ ቀዳሚ ሆኖ መመረጡን ተናግረዋል።

በመጪዎቹ ሁለት ዓመታት ደግሞ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ የምርምር ተልዕኮ በተሰጣቸውና የመጀመሪያው ትውልድ ተብለው የተለዩ 10 ዩኒቨርሲቲዎች ራሳቸውን በራሳቸው ወደ ማስተዳደር ይገባሉ ብለዋል።

እንደ ሃዋሳ፣ ጅማ፣ ባህርዳር፣ጎንደር፣ መቀሌ እና አንድ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ የምርምር ተልዕኮ የተሰጣቸው ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ የማድረጉ ሥራ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተወሰደ ልምድ እንደሚከናወንም ተናግረዋል።

ዩኒቨርሲቲዎቹ ራስ ገዝ ሲሆኑ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት አይተዳደሩም ማለት አለመሆኑን የገለጹት ዶክተር ሰለሞን ከተጠያቂነትና ከኃላፊነት ጋር ተልዕኮዋቸውን የሚፈጽሙበት አሠራር መፍጠር ነው ብለዋል።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ጣሰው ወልደሃና፣ ዩኒቨርሲቲው ራስ ገዝ መሆኑ የሀገሪቱን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ለመፍታት የሚያስችለውን ተልዕኮ በተገቢው እንዲወጣ ያስችላል ብለዋል።

ራስ ገዝ ሆነው እንዲወጡ መደረጉ አቅማቸውን አጠናክረው የተሻለ ሥራ ለመሥራት የሚችሉበት ዕድል እንደሚፈጠርና የትምህርት ጥራትን ለማሳደግ ወሳኝ መሆኑንም አመላክተዋል።

ዩኒቨርሲቲው የምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎቱን ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ እንዲያሰርጽ እድል የሚፈጥር መሆኑን ጠቅሰዋል።

የገቢ አቅሙን በሁለት እና ሦስት እጥፍ በማሳደግ አገልግሎቱን ማጠናከር እንደሚችልም ፕሮፌሰር ጣሰው መጠቆማቸውን ኢዜአ ዘግቧል ።

# በኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የሥርዓተ ምግብ አመራር መፍጠር እንደሚገባ ተገለጸ

ሞገስ ተስፋ



ፎቶ - ኢዮብ ተፈራ

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የሥርዓተ ምግብ አመራር የምግብና ሥርዓተ ምግብ ሥራን ለማሳደግ ሚናው የጎላ መሆኑ ተገለጸ። በትናንትናው ዕለት አራተኛው የኢትዮጵያ ሥርዓተ ምግብ መሪዎች ኔትወርክ ጉባኤ ተካሂዷል።

‹‹የሥርዓተ ምግብ አመራር ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የምግብ ሥርዓትና ሥርዓተ ምግብ በኢትዮጵያ›› በሚል መሪ ቃል ትናንት በተከበረው አራተኛው የኢትዮጵያ ሥርዓተ ምግብ መሪዎች ጉባኤ የሰቆጣ ቃልኪዳን ስምምነት ትልቅ ተሞክሮ የታየበት ነው ተብሏል።

በጤና ሚኒስቴር የእናቶችና ሕጻናት ዳይሬክተር ዶክተር መሠረት ዘላለም እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በምግብና ሥርዓተ ምግብ የራሷ ፖሊሲ ቀርጻ ወደ ሥራ ከገባች አራት ዓመት አስቆጥራለች ። ከፖሊሲው በመነሳት የ10 ዓመት የምግብና ሥርዓተ ምግብ ስትራቴጂ ተነድፎ እየተሠራ ነው። ለውጤታማነቱም በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች በቅንጅት እየተሠራ ነው።

ዶክተር መሠረት፤ መንግሥት የተለያዩ መሥሪያ ቤቶችንና አጋር አካላትን በማስተባበር ወደታች ለማውረድ የሚከተላቸው ስልታዊ አካሄዶች አሉ ያሉት ዶክተር መሠረት፤ለአብነት በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራው የሰቆጣ ቃልኪዳን አንዱ እንደምሳሌ የሚጠቀስ ነው ብለዋል።

ሁሉም መሥሪያ ቤቶች ለምግብና ሥርዓተ ምግብ የራሳቸው አስተዋጽዖ የሚያደርጉበት እስከ ታች ወርደው ለኅብረተሰቡ የሚያስፈልገውን በደንብ በመለየት እቅድ አቅደው በፋይናንስ እንዲደግፉ የሚያደርጉበት አሠራር መፍጠር ወሳኝ ነው ብለዋል።

ባለፉት ዓመታት በተለይም የእናቶችንና ከአምስት ዓመት በታች ያሉ የሕጻናት ሞት በመቀነስና የሥርዓተ ምግብ ላይ በመሥራት መቀንጨርን ከነበረበት ዝቅተኛ ደረጃ 37 በመቶ እንዲደርስ ተደርጓል። ከተወሳሰበ የምግብ እጥረት ችግር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮችን በመፍታት በርካታ ውጤቶች መመዝገባቸውን ዳሬክተሯ ገልጸዋል።

እንደ ጤና ሚኒስቴር ሌሎች አጋር አካላትን በማስተባበር የማኅበረሰቡን ችግርና ፍላጎት መሠረት በማድረግ አቅዶ መሥራት ያስፈልጋል ያሉት ዶክተር መሠረት፤ በሰቆጣ ቃልኪዳን የማኅበረሰቡን ፍላጎት መሠረት ያደረገ ሥራ በመሠራቱ ውጤታማ እንዲሆን አድርጓል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሥርዓተ ምግብ መሪዎች ኔትወርክ መሥራችና ሊቀመንበር እስራኤል ኃይሉ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ የሥርዓተ ምግብ ኔትወርክ ከተቋቋመ ወደ አራት ዓመት አስቆጥሯል። የሥርዓተ ምግብ መሪዎች ወቅታዊ የሆነ ስልጠና በመስጠት በተለይም ኮቪድን ለመከላከል በተደረገው ጥረት አጋዥ የሆኑ ስልጠናዎች መስጠታቸውን ገልጸዋል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት በተከሰቱት ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ማኅበረሰቡን ተደራሽ ያደረገ ሥራ መሠራታቸውን የገለጹት ሊቀመንበሯ፤ እያንዳንዱ አባል በወር ስምንት ሰዓት ነጻ አገልግሎት ይሰጣል ብለዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት በሥርዓተ ምግብና አመጋገብ ላይ ተጨባጭ ለውጥ እያስመዘገበ ነው። ለውጤቱ የአመራሩ ቅንጅታዊ አሠራር ከፍተኛ ነው። የሰቆጣ ቃልኪዳን በዓለም አቀፍ ደረጃ ሌሎች ሀገራት እንዲተገብሩት ትልቅ ተሞክሮና ማሳያ ነው። በመናበብና በመቀናጀት ከተሠራ ከምግብና ሥርዓተ ምግብ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ዜሮ የምናደርግበት ጊዜ ቅርብ ነው። በአቅም ግንባታው ዘርፍ የወጣቶች ኔትወርክ በመቋቋም ወጣቶችን ተደራሽ የሚያደርግ ሥራ እየሠሩ ነው ብለዋል።

ሊቀመንበሯ፤ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የሥርዓተ ምግብ አመራር የምግብና ሥርዓተ ምግብ ሥራን ለማሳደግ በቁርጠኝነት መሥራት ያስፈልጋል። ጉባኤው የሥርዓተ ምግብ አመራር ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የምግብ ሥርዓትና ሥርዓተ ምግብ በኢትዮጵያ ለውጥ በሚያመጣ መልኩ ውጤታማ ይሆናል ብለዋል።

የተለያዩ ዓለም አቀፍ የሥርዓተ ምግብ ተወካዮች ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የሥርዓተ ምግብ አመራር መፍጠር ወሳኝ መሆኑን ጠቁመው፤ ኢትዮጵያ በሰቆጣ ቃልኪዳን ያሳየችውን ውጤታማ ሥራ በሌሎች ሀገራት ጭምር ማስፋት ያስፈልጋል ብለዋል።

# በትግራይ ክልል ከ7 ሺህ 364 ሜትሪክ ቶን በላይ ምግብ እና መድኃኒት ተሰራጭቷል

በጋዜጣው ሪፖርተር





አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል 7 ሺህ 523 ሜትሪክ ቶን ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ እቃዎች እንዲሁም 364 ሜትሪክ ቶን መድኃኒት መሰራጨቱን የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታውቋል።

ኮሚሽኑ የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ ወደ ትግራይ ክልል የሚገቡ የተለያዩ የሰብዓዊ እርዳታ አቅርቦቶች ተጠናክረው መቀጠላቸውን አንስቷል። በዚህ መሠረት እስከ ኅዳር 12 ቀን 2015 ዓ.ም በ198 ተሽከርካሪ 6 ሺህ 93 ነጥብ 4 ሜትሪክ ቶን ምግብና አልሚ ምግብ በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች መሰራጨቱ ተጠቁሟል።

ከዚህ ባለፈም 364 ሜትሪክ ቶን መድኃኒት በክልሉ ችግር ውስጥ ለሚገኙ ዜጎች መሰራጨቱ ነው የተገለጸው።

በተመሳሳይ 105 ሺህ 159 ሊትር ነዳጅ እና 1 ሺህ 74 ነጥብ 6 ሜትሪክ ቶን ምግብ ነክ ያልሆኑ እቃዎች መሰራጨታቸውን ኤፍቢሲ ዘግቧል። የሰብዓዊ እርዳታውን በማሰራጨቱ ሒደት ከኮሚሽኑ ጋር 11 አጋር አካላት መሳተፋቸውም ነው የተገለጸው።

ስምምነቱን ተከትሎ በትግራይ ክልል የተጀመረው ያልተገደበ የሰብዓዊ እርዳታ ስርጭትም በመንግሥትም ሆነ በአጋር አካላት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተጠቁሟል።

የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን በኢትዮጵያ ሰሞኑን ይፋ ባደረገው መረጃ፤ መቀሌ የገቡት ተሽከርካሪዎች መድኃኒት እና የወደሙ መኖሪያ ቤቶችን መልሶ ለመጠገን የሚያስችሉ ቁሳቁሶችን የጫኑ ናቸው። በኮሚሽኑ የተላከው ርዳታ ካለፈው ነሐሴ ወዲህ የመጀመሪያው መሆኑን አስታውሷል ።

በተመሳሳይ በመንግሥት እና በሕወሓት መካከል ከተፈረመው የሰላም ስምምነት ወዲህ የመጀመሪያ ሰብዓዊ ድጋፉን ሰሞኑን ትግራይ ማስገባቱን የተባበሩት መንግሥታት ዓለም አቀፍ የሕጻናት አድን ድርጅት (ዩኒሴፍ) አስታውቋል።

ዩኑሴፍ ይፋ ባደረገው መረጃ መሠረትም ከስምምነቱ ወዲህ ወደ ትግራይ ያስገባው የመጀመሪያው ሕይወት አድን ድጋፍ በተለይም ለሕፃናት እና ሴቶች ወሳኝ መሆኑን አስታውቋል። ዩኒሴፍ በዚሁ መረጃው በግጭቱ ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው የአፋር እና አማራ አካባቢዎችም ተጨማሪ ርዳታ እንደሚያደርስ ገልጿል።

ዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ማኅበርም ወደ ሽሬ በረራ ማድረጉንና እርዳታ በአየርም በየብስም ለማድረስ እየሠራ መሆኑን መግለጹ አይዘነጋም።

በኢትዮጵያ መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረሰውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ በተለይ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በግጭት የተጎዱ የትግራይ፣ አማራና አፋር አካባቢዎች የሰብዓዊ ድጋፍ እንዲደርስ በማድረግ ረገድ በመንግሥትና በሰብዓዊ ድጋፍ ሰጪ አካላት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት እየተሠራ መሆኑም ይታወቃል።

# ጦርነቱ ቤተሰቦቼን ቢነጥቀኝም በሰላም ስምምነቱ ተስፋዬ ለምልሟል

**ሞገስ ጸጋዬ**

በሰሜን ኢትዮጵያ በነበረው ጦርነት በስነልቦና ከመጎዳት አልፎ ሦስት የቤተሰቦቹን አባላት በጦርነት አጥቷል። በርካቶች ያለአሳዳጊ ሲቀሩም መመልከቱን ይናገራል። የነበረው ንብረት ቢወድምም በአፍሪካ ኅብረት መሪነት በደቡብ አፍሪካ የተደረሰው የሰላም ስምምነት ግን ትልቅ ተስፋ እንዲሰንቅ አድርጎታል። ለአስር ዓመታት ያህል በመከላከያ ሠራዊት አገልግሎት በክብር የተሰናበተ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በቆቦ ጤና ጣቢያ ውስጥ ተቀጥሮ በመሥራት ላይ ይገኛል። "የጦርነትን አስከፊነት ከኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ጀምሮ አውቀዋለሁ፤ ጦርነት አውዳሚ በመሆኑ ሁሉም ለሰላም እጁን ሊዘረጋ ይገባል" ይላል የቆቦ ከተማ ነዋሪ የሆነው ሞገስ ደስታ።

የሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ የጦርነትን አስከፊነት አይቻለሁ የሚለው ሞገስ፤ የሰላምን ቦታ ጦርነት በመንጠቁ ሶስት ቤተሰቦቹን ማጣቱን ይናገራል። ልጁን፣ የልጅ ልጁንና የልጁን ባለቤት ጦርነቱ ወስዶብኛል። ጦርነት አስከፊ በመሆኑ ምንም የማያውቁ እናቶችና ሕጻናት ሕይወታቸው አልፏል። ንብረትም ወድሟል። ዳግም የሰው ሕይወት እንዳይጠፋና ንብረት እንዳይወድም ሁሉም ያለፈውን ይቅር ብሎ የመጣውን የሰላም ስምምነት ሊቀበለው እንደሚገባም ያነሳል። ለዚህም አሁን የተደረሰው የሰላም ስምምነት እንደ ሕጻን ልጅ ተንከባክቦ ለውጤት ማብቃት የሁሉም ኃላፊነት መሆን ይገባዋል ይላል።

የጦርነትን አስከፊነት ከእኔ በላይ የሚናገር የለም የሚለው ሞገስ፤ ልጄን ቀብሬ ቤቴ ማደርና መጽናናት አልቻልኩም። ስለሆነም ለጦርነት ሳይሆን ለሰላም ሁሉም ዜጋ ዋጋ ሊከፍል ይገባል። ጦርነቱ ቤተሰቦቼን ቢነጥቀኝም በሰላም ስምምነቱ ተስፋዬ ለምልሟል ሲልም ይናገራል።

ጦርነት ቤተሰብን ከቤተሰብ ይለያል። እንኳን ዓመት ወራትና ቀናትን ይቅርና ሰዓታትን ለማሳለፍ ይከብዳል። የጦርነት ትርፉ ኪሳራ በመሆኑ ሁሉም ዜጋ ለተጀመረው



ፎቶ፡- ሳሙኤል ተስፋዬ

የሰላም ስምምነት ዋና ተዋናይ መሆን አለበት። ያለፈ ጉዳትን እያሰቡ መኖር ትርፉ ዳግም ጉዳት ብቻ ነው። ስለሆነም ቂምን ሽሮ እርቅን ማምጣት ይገባል ይላል።

እንደ ሞገስ ገለጻ፤ የሰላምን ዋጋ የምናውቀው ስናጣው ብቻ በመሆኑ ዳግም መሰል ጉዳት እንዳይደርስ ችግሮችን በሰላምና በንግግር መፍታት አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው። ከሰሞኑ የተደረሰው ስምምነትና በሂደት ላይ ያለው ሰላም የማምጣት ጅምር በፍጥነት ወደ ተግባር መቀየር አለበት። ባለፈው ጦርነት ሕይወት ቢጠፋም ንብረት ቢወድም እርቅ መፈጠር ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መሆን ይኖርበታል። አብዛኛው ጦርነት በመጨረሻ የሚቋጨው በስምምነት ነው፤ አሁንም ተጨማሪ ኪሳራ ሳይደርስ ስምምነቱን ሁሉም ወገን ሊተገብረው እንደሚገባ ያነሳል። እየነፈሰ ባለው የሰላም አየር ሁሉም የቆቦ ነዋሪ ንጹሕ አየር እየተነፈሰ ነው፣ ስምምነቱንም የቆቦ ሕዝብ ይደግፈዋል።

ሰላምን ለማምጣት የመንግሥት ጥረት መደነቅ አለበት ያለው ሞገስ፣ ኅብረተሰቡ መንግሥትን ሊደግፍና ለስምምነቱ ድጋፉን አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል ይላል። የቆቦ ሕዝብና ከተማዋ በደልና ጉዳት ቢደርስባቸውም የሚያዋጣውና ቀጣዩ መፍትሔ ቂም ወይም ዳግም ጦርነት ሳይሆን ሰላም መሆኑን በመገንዘቡ በሰላም ስምምነቱ አብዝቶ ተደስቷል። አገርን እየወደዱ በጦርነት መኖር ስለማይቻል በሚፈለገው ልክ የሰላም ስምምነቱን መደገፍ ተገቢ ነው። ጦርነት እንኳን የዓመት ቀለብንና ልብስን መያዝ ይቅርና የእለት ጉርስ ለመያዝ ጊዜ የማይሰጥ በመሆኑ ሊወገዝና በሰላም ሊተካ እንደሚገባ ሀሳቡን አጋርቶናል።



አቶ አክሊሉ ታደሰ

# የሰላም ስምምነቱ ኢንቨስተሮችን እያነቃቃ ነው

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የሰሜኑን ግጭት ለመፍታት የተጀመረው የሰላም ስምምነት በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ያሉ ኢንቨስተሮችን እያነቃቃ ነው ሲል የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ። ኮርፖሬሽኑ በአግሮ ፕሮሰሲንግ ላይ ከተሠማራው ሀገር አቀፍ ኩባንያ ጋር ተፈራርሟል።

ፓሮን ትሬዲንግ የተሰኘው ሀገር በቀል ኩባንያ በባህርዳር ኢንዱስትሪ ፓርክ ገብቶ ምርት ለማምረት ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር ትላንት ተፈራርሟል። በሁነቱ ላይ የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አክሊሉ ታደሰ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ በሰሜኑ አካባቢ የነበረውን ሁኔታ በሰላም ለመቋጨት ስምምነት ላይ መደረሱ አምራች ኢንዱስትሪዎችንና ኢንቨስተሮችን እያነቃቃ ነው። በአጎዋ ምክንያት ሠራተኞቻቸውን የቀነሱና ከገበያ የመውጣት ፍላጎት የነበራቸውም አሁን ላይ ውሎቻቸውን እያደሱ ይገኛሉ።

በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ያሉ አምራቾች ከአጎዋ ውጭ የገበያ አማራጮችን እንዲፈልጉ በማድረግ በትኩረት መሠራቱን የገለጹት አቶ አክሊሉ፤ ከዚህ ቀደም በአጎዋ ምክንያት ሠራተኞቻቸውን ቀንሰው የነበሩ አምራቾች በሰላም ስምምነቱ ምክንያት ከገበያ የመውጣት ፍላጎታቸውን ትተዋል ሲሉ ገልጸዋል። የሰላም ስምምነቱ በዘርፉ ላይ የነበረውን ትርክት በመቀየር ኢንቨስተሮችን እያነቃቃ እንዳለ ነው የተናገሩት።

እንደ አቶ አክሊሉ ገለጻ፤ አምራቾቹ ከተፈጠረው ወቅታዊ ሁኔታ ጋር ራሳቸውን አስተካክለዋል። አዳዲስ ኢንቨስተሮች ወደ ሥራ ለመግባትም በሂደት ላይ ሲሆኑ፤ ነባሮቹም ከገጠማቸው ችግር ወጥተው በመነቃቃት ላይ ይገኛሉ።

በኢትዮጵያ በሰሜኑ አካባቢ የነበረውን ሁኔታ በሰላም ለመቋጨት ስምምነት ላይ በመደረሱና መንግሥት ባለው ቁርጠኝነት የሰላም አየር መኖሩ የራሱን ለኢንቨስመንቱ ምቹ ሁኔታን እንደፈጠረ አቶ አክሊሉ ገልጸዋል። አምራቾችም ጭምር በአንድ ገበያ ላይ ብቻ ጥገኛ መሆን እንደሌለባቸው ግንዛቤ ወስደዋል ብለዋል። የተለያዩ አማራጭ ገበያዎችን እንዲፈልጉ መደረጉንና አጎዋ ችግር ቢያጋጥመውም ከአጎዋ ውጭ ለአሜሪካ ገበያም ጭምር ምርቶቻቸውን የሚያቀርቡበት መንገድ መመቻቸት ችለዋል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ለአገሪቱ ማክሮ ኢኮኖሚ መነቃቃት አስተዋጽዖ እያበረከቱ እንዳሉ የጠቆሙት አቶ አክሊሉ፤ ለሥራ እድል ፈጠራ፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የኤክስፖርት ምርትን የማሳደግና የውጭ ምንዛሪ ግኝትን የማሳደግ ተልዕኮን በአግባቡ እየተወጡ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

አቶ አክሊሉ፤ ኢንቨስትመንት በዓለም አቀፍ ደረጃ የምንወዳደርበት ነው በማለት፤ በኢንዱስትሪ ፓርኮች አማካኝነት ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በመተካት ትልቅ ጥረት እየተደረገ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል። የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴውን የተነቃቃ እንዲሆን ኮርፖሬሽኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂና ተወዳዳሪ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት ጥረት እያደረገ እንዳለም አመላክተዋል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን በመላው አገሪቱ በሚያስተዳድራቸው 13 የኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የውጭና ሀገር በቀል ባለሀብቶችን በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች በማስገባት ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ጥቅም እያስገኘና ለወጣቶች የስራ ዕድል እየፈጠረ ይገኛል ነው ያሉት።

ፓሮን አገር በቀል ኩባንያ በግማሽ ቢሊየን ብር ካፒታል የሚንቀሳቀስ ሲሆን በኢንዱስትሪ ፓርኩ ሲገባ በተለይም ለምግብና ለመጠጥ ፍጆታ የሚውሉ ጥሬ እቃዎችን በማቅረብ ለአንድ ሺ ዜጐች የሥራ ዕድልን እንደሚፈጥር ተገልጿል።

# ብዝኃነታችን ለጋራ እድገታችን መሠረት እንደሚሆን ምክር ቤቱ አስታወቀ

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- ብዝኃነታችን ለሁላችንም የጋራ እድገት መሠረት ሊሆኑ የሚችሉ አባቶቻችን ያቆዩልን ጌጦቻችን መሆናቸውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አማካሪ አቶ አለምነው ጌትነት በተለይ ለኢፕድ እንደተናገሩት ብዝኃነታችን ለሁላችንም እድገት መሠረት የሚሆን ትልቅ ጌጣችን ነው።

በሀገራችን አሁን ያለው የፌደራሊዝም ሥርዓት በተፈጥሮ የተሰጠን ብዝኃነት፣ በቋንቋ፣ በባህል፣ በታሪክ እና በተለያዩ ማኅበራዊ ትስስሮቻችን በልዩነቶች እና አንድነቶቻችን በጋራ የሚስተናገዱበት መሆኑን ገልጸዋል።

17ኛው የብሔር ብሔረሰቦች በዓል ኅዳር 29 ሲከበር ለሰላም ልዩ ትኩረት በመስጠት መሆን አለበት ያሉት አቶ አለምነው በተለይ ልዩነቶቻችንን የአንድነታችን ማገር አድርገን መውሰድ አለብን ብለዋል።

አንዱ የሌላውን ማክበር ብቻ ሳይሆን አንዱ የሌላውን ሕመምና ብሶት የራሱ አድርጎ በመውሰድ የጋራ አድርገን በመሥራት ፍቅራችን፣ አንድነታችን እና አብሮነታችን እየተጠናከረ መቀጠል እንደሚገባውም አመላክተዋል።


ኅብረ-ብሔራዊነት ሲባልም ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች የራሳቸውን፣ ቋንቋ፣ ታሪክ፣ እሴት፣ ማንነት የሚያሳድጉበት ነው ያሉት አቶ አለምነው፤ እነዚህም እያንዳንዳቸው ተደምረው የሀገር እሴትና ውጤት የሚሆኑበት ነው ሲሉም ተናግረዋል።

በሌላ በኩል ሕብረብሔራዊ አንድነት ሲባል ተናጥላዊ ያሉን ልምዶች፣ ዕውቀቶች፣ ቋንቋዎች እና ባህሎች ወደ አንድ ሲደመሩ የሚፈጥሩት አገር የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ ነው የሳሉት አቶ አለምነው፤ በመሆኑም ይሄንን ማደራጀት የሚቻልበትን ነገር መፍጠር ትኩረት ያሻዋል ብለዋል።

አንዱ ለግጭት መነሻ ሲሆን የሚታየው የተሳሳተ



አቶ አለምነው ጌትነት



አቶ ፍስሐ ቀለመወርቅ

እይታም አንድነት ማለት ለአሀዳዊነት የተሰጠ ትርጓሜ ነው ያሉት አቶ አለምነው አንድነት ማለት የተለያዩ ፍላጎቶች እና የተለያዩ ቁሶችን ወደ አንድ ጠቃሚ የተደራጀ አቅምና ጉልበት ማሻገር ማለት እንጂ አንዱን በመንጠቅ ሌላውን በመድፈቅ መሄድ አንድነት አለመሆኑን ገልጸዋል።

ፌደራሊዝም በራሱ የፍልስፍና ሳይንስ ነው ያሉት አቶ አለምነው በመርሕ ደረጃ የተቀመጡት መቻቻል፣ ነፃነት፣ አንዱ የሌላውን ችግር እንደራሱ አድርጎ መውሰድ መገለጫዎቹ መሆናቸውን ጠቁመዋል። እንዲሁም የእያንዳንዱን ፍላጎት፣ ብሔራዊ ማንነት፣ ታሪክ፣ እውቅና መስጠት እና መከባበር አስፈላጊ መሆኑንም ጠቁመዋል።

እንደ አቶ አለምነው ገለጻ፤ የፌደራል ሥርዓቱን በተዛባ መንገድ መተርጎም የተለያዩ ችግሮችን እያስከተሉ ናቸው።

ሕገ መንግሥቱ ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች መኖራቸውን ያስታወሱት አቶ አለምነው በሕገመንግሥቱ አንቀጾችም መሻሻል አለባቸው ተብለው የሚነሱ ሀሳቦች የመመካከር አጀንዳዎቻችን እንጂ የልዩነት እና የግጭት መነሻ መሆን የለባቸውም ብለዋል።

የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ምክር ቤት ጸሐፊ አቶ ፍስሐ ቀለመወርቅ በበኩላቸው፣ በሲዳማ ክልል አዘጋጅነት የሚከበረው 17ኛው የብሔርብሔረሰቦች በዓል ልዩነታችን ምን ዓይነት ውበት እንዳላቸው ለሀገራዊ ዕድገታችን ያለውን ሚና በመረዳት ልጆቻችን በምን መልኩ መማር እንዳለባቸው በማስገንዘብ መሆን አለበት ብለዋል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ሲረጩ የነበሩ የጥላቻ ንግግሮችን ሳይሆን ልዩነቶቻችንን እንደ መልካም አጋጣሚ እና የቱሪዝም ምንጭነት መጠቀም እንዳለብንም ጠቁመዋል።

# መንግሥት እያደረገ ያለው ያልተገደበ የሰብዓዊ ድጋፍ የሚበረታታ መሆኑን አሜሪካ ገለጸች

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መንግሥት በትግራይ፣ አፋርና አማራ ክልል እያደረገ ያለውን ያልተገደበ ሰብዓዊ ድጋፍ የማቅረብና መሠረተ ልማቶችን የመመለስ ጥረት የሚበረታታ መሆኑን አሜሪካ ገለጸች።

የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን ከኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ጋር ፍሬያማ የስልክ ውይይት ማድረጋቸውን አስታውቀዋል።

ከውይይታቸው በኋላ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባወጣው መግለጫ መንግሥት በትግራይ እና አጎራባች የአማራና አፋር አካባቢዎች ያልተገደበ የሰብዓዊ ድጋፍ ለማድረግ እያደረገ ያለውን ጥረትና መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለማስጀመር እያከናወናቸው ያሉ ሥራዎች እውቅና የሚሰጠው ነው ብሏል።

አሜሪካ በአፍሪካ ኅብረት ጥላ ስር የተፈረመውን የሰላም ስምምነትና ስምምነቱን ለመቆጣጠር ኅብረቱ የሚያከናውነውን ተግባር በቁርጠኝነት እንደምትደግፍ አስታውቃለች።

ከፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት በኋላ ወደ ትግራይ በርካታ የሰብዓዊ ድጋፍ እየተላከ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፤ ከአንድ ሳምንት በፊት (ኅዳር 7 ቀን 2015 ዓ.ም) ኢፕድ ከኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ባገኘው መረጃ መሠረት በዚያን ዕለት ውስጥ ብቻ ሰብዓዊ ድጋፍ የጫኑ 67 ተሽከርካሪዎች ወደ ትግራይ መጓዛቸው መገለጹ ይታወሳል።

ተሽከርካሪዎቹ ወደ ሽሬ፣ ሽራሮና አክሱም ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎችን የሚያደርሱ ሲሆን፤ ከ67 ተሽከርካሪዎች መካከልም መድኃኒትና የሕክምና ቁሳቁስን የያዘ ተሽከርካሪም ተካትቷል።

በተመሳሳይ ከናይሮቢው ስምምነት በኋላ ለመገናኛ ብዙኃን መግለጫ የሰጡት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ መከላከያ ሠራዊት በትግራይ ክልል ለሚገኙ አርሶ አደሮች ሰብል በማጨድ እያገዘ መሆኑን፤ በመከላከያ አንቡላንስም ሲቪሎች ሳይቀር ወደ ሕክምና እየተጓጓዙ መሆኑን መግለጻቸው ይታወቃል።

# የኢትዮጵያ አየር መንገድ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

መሆኑን ጠቅሰው ፤ዳግም በረራ ለመጀመር መዘጋጀቱ ዘርፍ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው ተናግረዋል።

በመንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረገው ሰላም ስምምነት አየር መንገዱ ሲሰጣቸው የነበሩ መደበኛ አገልግሎቶችን ከመስጠት ባለፈ የሰብዓዊ ድጋፍ ተደራሽነትን ለማፋጠን ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው አብራርተዋል።

በክልሉ ከሚገኙ ኤርፖርቶች መካከል የመቀሌ እና የሽሬ አየር ማረፊያ በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኙ በመሆኑ ለበረራ ምቹ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የአክሱም ኤርፖርት ግን በግጭቱ ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ ለበረራ በሚመች መልኩ ማስተካከያ የሚጠይቅ ስለመሆኑ ጠቅሰዋል።

እንደ ኢዜአ ዘገባ፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ ትግራይ ክልል የተለያዩ መዳረሻዎች ዳግም በረራ ለመጀመር መዘጋጀቱ በክልሉ በተለይም ሰብዓዊ ድጋፍን በስፋት ተደራሽ ለማድረግ የሚያግዝ መሆኑን ዋና ሥራ አስፈፃሚው ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በተለይም የአፍሪካ አህጉርን በአየር ትራንስፖርት የማስተሳሰር ሰፊ ራዕይ ሰንቆ በመሥራት ላይ መሆኑ ይታወቃል።

አየር መንገዱ አሁን ላይ ያሉትን 207 አጠቃላይ መዳረሻዎች እኤአ በ2035 ወደ 271 ለማሳደግ እየሠራ ይገኛል።

# በክልሉ የዘንድሮ ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ሲሆን ከዚህም 400 ሺህ ኩንታል ምርት ይጠበቃል ብለዋል። እስከ አሁን ድረስ በተሠራው ሥራ 8ሺህ 877 ሄክታር መሬት በጂፒኤስ በመለየት አንድ ሺህ ሄክታሩ መታረሱን ገልጸዋል።

በአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር በክልሉ አንድ ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል ታቅዶ 873 ሚሊዮን ችግኞች ተተክለዋል ያሉት ኃላፊው እስከ አሁን ድረስ በተደረገው ክትትል 84 ነጥብ አራት በመቶው በመጽደቅ በክልሉ ምቹ የአየር ንብረት እንዲኖር በማድረግ የሚመረቱ ምርቶች ላይ አዎንታዊ ለውጥ በማሳየት ላይ ይገኛል ብለዋል።

ከአረንጓዴ አሻራ ልማት ጋር የቡና ልማት እየጨመረ በመሄድ እስከ አሁን ድረስ 161 ሺህ ሄክታር መሬት በቡና ተክል ተሸፍኗል፣ 131 ሺህ ሄክታሩ ላይ ያለው ደግሞ ምርት በመስጠት ላይ ይገኛል ሲሉም ጠቁመዋል።

ይህ ደግሞ የአርሶ አደሩ ተጠቃሚነት እንዲጨምር በማድረግ በአሁን ሰዓት አንድ ኪሎ እሸት ቡና በ50 ብር በመሸጥ የአከባቢውን ንግድ እንቅስቃሴ በማነቃቃት እንደሀገርም የውጪ ምንዛሪ ገቢ ማስገኛ አቅምን እያጠናከረ ይገኛል ሲሉም ተናግረዋል።

እንደቢሮ ኃላፊው ገለጻ ፤ በ2014 ዓ.ም ብቻ ቡና 109 ሚሊዮን ዶላር ገቢ በማስገኘት በሀገር ግንባታ ውስጥ ትልቅ አስተዋጽዖ እያበረከተ ነው።

የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ምርቶች በተመሳሳይ ጭማሪ እያሣዩ መሆኑን ጠቁመው ምርቶቹ ለይርጋለም የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ግብዓት በመሆን ሁለት ፋብሪካዎች ሥራ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ አስችሏል ብለዋል። ከዚህም አኳያ አምስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማስገኘት ተችሏል ፣ ከመኸር ሰብሎችም አንጻር በደጋውና በቆላው በሚመረቱ ሰብሎች በተመሳሳይ ጭማሪ በማሳየት ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል ።

በቤተሰብ ደረጃ ብልጽግናን ለማረጋገጥ ባለድርሻ አካላትም ሆኑ ሁሉም ኅብረተሰብ በትጋት በመሥራት በዘርፉ የተጀመሩ መሻሻሎችን እንዲያስቀጥሉ ጥሪ አቅርበዋል።

# ‹‹የሕወሓት ታጣቂ በአጭር ጊዜ ትጥቅ ፈትቶ ወደ ካምፕ እንዲሰባሰብ እየተሠራ ነው‹‹

- ሌተናል ጀኔራል ታደሰ ወረደ

ውብሸት ሰንደቁ



አዲስ አበባ፡- የሕወሓት ታጣቂ በአጭር ጊዜ ትጥቅ ፈትቶ ወደተዘጋጀለት ካምፕ የሚሄድ መሆኑን አዛዡ ሌተናል ጀኔራል ታደሰ ወረደ አስታወቁ።

የቡድኑ አዛዥ ከትናንት በስቲያ በሰጡት ማብራሪያ፤ ጦርነቱ የትግራይን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገርም ችግር የፈጠረ መሆኑን ተናግረው፤ “በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም የትግራይ ሕዝብ ከጦርነት ወደ ሰላም የሚያደርገው ሽግግር ላይ ከእኛ የሚጠበቀውን ሚና እንወጣለን” ብለዋል፡

የሰላም ስምምነቱ አተገባበር ላይ ያተኮረው ውይይት በናይሮቢ ከተካሄደ ጀምሮ በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ስምምነት የተደረሰባቸውን ነጥቦችን እያከናወኑ እንደሚገኙም አብራርተዋል።

ማንኛውም በትግራይ የሚገኝ ታጣቂ ትጥቅ እንደሚፈታ እና በስምምነቱ መሠረት በስልጠና መስጫ ካምፖች በመሰባሰብ የመልሶ ግንባታ ሥራ እንደሚሠራ፤ ለዚህም በቁርጠኝነት እየሠሩ መሆኑን ገልጸዋል። ይህንን ለመፈጸምም በቀጣይ የትግራይ ኃይል የሚባል እንደማይኖር የገለጹት አዛዡ፤ በዚህ መሠረትም የሰላም ስምምነቱን እያንዳንዱ አባል እንዲያውቀው እየተደረገ ነው ብለዋል።

በትግራይ የበላይ አዛዦች እስከ ታች ያሉ የቡድኑ አባላት ስለሰላም ስምምነቱ ግንዛቤ መፈጠሩንና መግባባት ላይ እየተደረሰ መሆኑን ጠቁመው፤ በሁለት ቀናት እስከ ታች ድረስ ይህ ተግባር እንደሚጠናቀቅ ተናግረዋል።

የቡድኑ ትጥቅ መፍታት በፕሪቶሪያው ስምምነት በግልጽ በተቀመጠው አግባብ የሚፈጸም መሆኑ ተጠቁሟል።

ተግባራዊ የሚደረገው ትጥቅ የማስፈታት ሂደት እንደ ቅጣት ሳይሆን እንደ አንድ የሰላም ሂደት የሚታይ መሆኑን ጠቅሰው፤ ታጣቂው በአጭር ጊዜ ትጥቅ ፈትቶ ወደተዘጋጀለት ቦታ እንደሚገባ አብራርተዋል።

ከዚህ ቀጥሎ ታጣቂው ካለበት የውጊያ ቦታ ተንቀሳቅሶ ወደተዘጋጀለት ቦታ እንደሚሄድ የተናገሩት አዛዡ፤ ይህ የሎጅስቲክስ አቅም እስከ ፈቀደ ድረስ በጥቂት ቀናት የሚሠራ ይሆናል ብለዋል።

ስምምነቱ ጦርነቱን እስከወዲያኛው ለማስቀረት ዕምቅ አቅም አለው ያሉት ሌተናል ጀኔራል ታደሰ፤ የኢፌዲሪ መከላከያ ሠራዊትም የትግራይ ሕዝብን መጠበቅን እንደ አንድ ኃላፊነት መውሰድ እንደሚኖርበት አሳስበዋል።

ከኢፌዲሪ መከላከያ ሠራዊት ጋር ጦርነት ውስጥ የቆየው አካል መክፈል የሚገባውን መስዋዕትነት መክፈል አለበት እንጂ መክፈል የማይገባውን መስዋዕትነት እንዲከፍል እንደማይፈልጉ የተናገሩት ሌተናል ጀኔራሉ፤ ጦርነት እርሳቸው ሲመሩት በቆዩት ታጣቂም ሆነ በሕዝቡ ላይ የሚፈጥረውን ፍዳ በመገንዘብ ስምምነቱን ፈጽመናል እንጂ ማንንም ለማስደሰት አልያም ለማስከፋት ብለን ያደረግነው አይደለም ብለዋል።

በመንግሥት እና በሕወሓት ተደራዳሪዎች መካከል የነበረው የሰላም ውይይት በጣም ጥሩ፤ መንፈሱም መልካም እንደነበር ገልጸዋል። በሂደቱ አተገባበር ላይ የታዩ ክፍተቶችን ለማየትና ለመፍታት ችግር እንዳልነበረ ጠቅሰዋል።

ትግበራው ላይ ከጦርነት ወደ ሰላም የሚደረገውን ሽግግር ሊጎዱ የሚችሉ በርካታ ነገሮች ይኖራሉ ያሉት ሌተናል ጀኔራሉ፤ ከጦርነት ወደ ሰላም የሚደረገው ሽግግር የተለየ ስክነት የሚጠይቅና ወደ ኋላ የሚመልሱ ነገሮችን እያስወገዱ መሄድን የሚጠይቅ በመሆኑ የተገኘውን ሰላም እያንዳንዳችን ስትራቴጂክ ግብ አድርገን መሥራት ይጠበቅብናል ሲሉ ተናግረዋል።

# የሕዝብ እምባ ጠባቂ ተቋም 1 ሺህ 270 የበደል ቅሬታዎችን መቀበሉን አስታወቀ

## - በሦስት ወራት ውስጥ ለ277 መዝገቦች ዕልባት ተሰጥቷል

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ 1 ሺህ 270 የሕግና አስተዳደር በደል ቅሬታዎችን መቀበሉን የተቋሙ የሕግና አስተዳደር በደል ምርመራ ዳይሬክተር አቶ መንግሥቱ ቀኘ አስታወቁ። ተቋሙ በበጀት ዓመቱ በሦስት ወራት ውስጥ 528 ያህል መዝገቦችን መርምሮ 277 ለሚሆኑት ዕልባት መስጠቱንም አስታውቋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የሕግና አስተዳደር በደል ምርመራ ዳይሬክተር አቶ መንግሥቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ተቋሙ ባዘጋጀው የነፃ የስልክ መስመር በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በአማርኛ፣ ኦሮምኛና ትግሪኛ ቋንቋዎች 1 ሺህ 270 ያህል ቅሬታዎችን ተቀብሏል።

ሕዝቡ ከዚህም በላይ ቅሬታዎች ቢኖሩትም በሦስት ባለሙያዎች ብቻ እየተቀበለ ስለነበር መጨናነቆች ነበሩ ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በርካታ ቅሬታ አቅራቢ መኖሩን ጠቁመው የተቋሙ የመቀበል አቅም ግን ውስን መሆኑን ተናግረዋል።

በተጨማሪም የቅሬታ አቅራቢው ጉዳይ በዝርዝር መደመጥ ስላለበት እያንዳንዱ ቅሬታ አቅራቢ ረጅም ሰዓት ይወስዳል። ለዚህም ወደፊት እየታየ አቅምን ማሳደግ እንደሚያስፈልግ ገልጸው፤ ተቋሙ በየአካባቢው ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ያሉት በመሆኑ እነዚህን አማራጮች በመጠቀም ዜጎች የደረሰባቸውን ሕጋዊ እና አስተዳደራዊ በደል እንዲያቀርቡ እንደመፍትሔ ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በአዋጅ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር ያሉት መሆኑን ያነሱት ዳይሬክተሩ፤ ከቀረቡት ቅሬታዎች ውስጥ በተቋሙ ሊታዩ የሚችሉትን በመለየት እንዲታዩ ይደረጋል ብለዋል።

በበጀት ዓመቱ በአለፉት ሦስት ወራት 711 ቅሬታዎች መቅረባቸውን እንደ አብነት ያነሱት አቶ መንግሥቱ ከነዚህ ውስጥ 518 ያህሉ መዝገቦች በተቋሙ ሥር ሊታዩ የሚችሉ በመሆናቸው ምርመራ መካሄዱን ተናግረዋል። ከታዩት መዝገቦች ውስጥም 277 ያህሉ ዕልባት ማግኘታቸውን ተናግረዋል።

በተቋሙ ሊታዩ የሚችሉ ጉዳዮች ላይ ምርመራ በማድረግ ከተቋሙ ሥልጣን ውጪ ቅሬታዎች ላቀረቡ ዜጎች ደግሞ ተገቢው የሕግ ምክር አገልግሎት እየተሰጠ ወደሚመለከታቸው ተቋማት እንዲሸጋገሩ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

ለአብነትም የሰብዓዊ መብት አልያም የሙስና ጉዳዮች ለተቋሙ እየቀረቡ መሆኑን አንስተው፤ ጉዳዮቹን ወደሚመለከታቸው አካላት እንደሚላኩ አስታውቀዋል።

የመንግሥት ሥርዓት ባለበት እና አገልግሎት በሚሰጥበት ሁኔታ አስተዳደራዊ በደሎች እንደሚኖሩ የተናገሩት አቶ መንግሥቱ፤ እነዚህን ቅሬታዎች በአግባቡ ተቀብሎ በሥርዓት ማስተናገድ እና ምላሽ መስጠት ይጠበቃል ብለዋል።

ሆኖም የሚቀርቡ አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ ቅሬታዎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ጥረት ብቻ ሊፈቱ እንደማይችሉ ገልጸው፤ ሁሉም አካል ትብብር ሊያደርግ እንደሚገባ ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሰላም ስምምነቱን ለመተግበር እየተደረገ ያለው ጥረት የሚበረታታ ነው!

በሃገር መከላከያ ሰራዊት ሰሜን እዝ ላይ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ሌሊት በተፈጸመው ጥቃት ምክንያት የኢትዮጵያ በተለይም የሰሜኑ ክፍል ላለፉት ሁለት ዓመታት በጦርነት ውስጥ ዘልቋል። ምንም እንኳን ጦርነቱ ኢትዮጵያውያን ተገድደው የገቡበት እና ስለ ኢትዮጵያ ህልውናና ሉዓላዊነት ሲባል የተካሄደ ቢሆንም፤ በወንድማማቾች መካከል የተከናወነ እንደመሆኑ ጉዳቱ ከፍ ያለ ነው። በዚህም በርካቶች ህይወታቸውን፣ አካላቸውን፣ ሃብት ንብረታቸውን አጥተዋል። ሃገርም እንደ ሃገር የበዛ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ስብራቶችን አስተናግዳለች። ከምንም በላይ ደግሞ ዜጎች ለከፋ ሰብዓዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች ተዳርገዋል።

መንግስት ደግሞ ኃላፊነት እንደሚሰማው አካል፤ ሕግን የማስከበር ግዴታውን ከመወጣት ጎን ለጎን የዜጎችን ሁለንተናዊ ደህንነትና ሰላም ለማረጋገጥ የሚያስችሉ በርካታ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል። ለዜጎች ሰላም እና ለሰብዓዊነት ቅድሚያ በመስጠት ተደጋጋሚ የተናጠል ተኩስ አቁሞችን አድርጓል፤ ያለመታከት የሰላም ጥሪዎችን አስተላልፏል፤ ያለምንም ቅድመ ሁኔታና በማንኛውም ቦታ ስለ ሰላም ለመነጋገር ያለውን ቁርጠኝነት ደጋግሞ አሳውቋል። ይሁን እንጂ የአንድ ወገን የሰላም ፍላጎት ብቻውን ለፍሬ ሊበቃ አይችልምና የሰላም ሂደቱ ከሁለቱም ወገን እስኪመነጭ ድረስ ጊዜ መውሰዱ፤ ሁለት ዓመታትም በጦርነት ማለፋቸው የግድ ሆነ።

በመጨረሻም ጊዜው ሲደርስ በመንግስት በኩል የቀረበውን ተደጋጋሚ የሰላም ጥሪ በመቀበል ሕወሓት ለሰላም ድርድር መዘጋጀቱን አሳወቀ። ይሄ ውሳኔ በራሱ ለዜጎች በተለይም ለትግራይ እና አጎራባች ክልሎች ህዝቦች ትልቅ የሰላም ተስፋን የሰጠ ነበር። በኋላም ተስፋው ወደ ተጨባጭ እውነትነት የተቀየረበት በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የተካሄደውና በመንግስትና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት እውን ሆነ። ይሄን ስምምነት ተከትሎም በኬንያ የተካሄደው እና የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት እና በሕወሓት ታጣቂ ኃይሎች አዛዦች መካከል የተደረሰው ስምምነት ደግሞ በኢትዮጵያ ምድር የሚፈለገው ሰላም መምጣቱ አይቀሬ መሆኑን ያስረገጠ ነው።

ይሄን ተከትሎ ስምምነቱን የመተግበር ኃላፊነትን መወጣት በመንግስትም ሆነ በሕወሓት በኩል የሚጠበቅ ነበር። በዚህም የፌዴራል መንግስት ከስምምነቱ ማግስት አንስቶ ግጭት ቀስቃሽ መልዕክቶች እንዳይተላለፉ ከማድረግ ጀምሮ እስከ ሰብዓዊ ድጋፍና መልሶ ግንባታ ስራዎች በሙሉ አቅሙና በትኩረት መስራት ጀምሯል። መገናኛ ብዙሃንም ሆኑ ሌሎች አካላት ከግጭት ቀስቃሽና ጥላቻን ከሚያሳድሩ ዘገባዎችና መረጃ ማሰራጨት ተግባራቸው እንዲታቀቡ አድርጓል። የመልሶ ግንባታ ስራዎች በሁሉም ጉዳት በደረሰባቸው አካባቢዎች በፍጥነት እንዲከናወኑ እና አገልግሎት መስጠት የሚገባቸውም በተጠናቀቁበት ቅጽበት ወደ አገልግሎት እንዲገቡ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ይገኛል። ለዚህም እንደ መንገድ፣ ቴሌ፣ መብራት፣ ባንክና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።

ከዚህ በተጓዳኝ በትኩረት እየተሰራበት ያለው ተግባር የሰብዓዊ ድጋፍን፣ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ማድረስ ሲሆን፤ በተለይ በትግራይ ክልል ምግብ ነክ፣ ምግብ ነክ ያልሆኑ፣ የመድሃኒትና ህክምና መስጫ ቁሳቁሶችን ጨምሮ በርካታ ድጋፎች መቐሌን ጨምሮ በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች እንዲደርሱ ተደርጓል። በአፋር እና በአማራ ክልሎችም መሰል ድጋፎችን የማድረስ ጥረቱ ተጠናክሮ ቀጥሏል። እነዚህና መሰል በመንግስት በኩል ያሉ የሰላም ስምምነቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚታዩ ብርቱ ጥረቶች ደግሞ መንግስት ለዜጎች ዘላቂ ሰላም ምን ያህል ቁርጠኛ እንደሆነ እና ዋጋ እየከፈለ እንዳለ የሚያሳዩ ናቸው።

በተመሳሳይ በሕወሓት በኩል ለሰላማዊ ንግግር ራስን ከማዘጋጀት፤ በሰላም ዙሪያ ለመነጋገር ደቡብ አፍሪካና ኬንያ ተጉዞ የሰላም ስምምነት ከመፈራረም፤ የተፈረሙ የሰላም ስምምነት ይዘቶች ለህዝቦች ሰላም ያላቸውን ከፍ ያለ ፋይዳ ተቀብሎ ለህዝቡ ለማስረዳት የሄደበት ርቀት፤ እንዲሁም ለህዝቦች ሰላም ሲባል ታጣቂዎችን ትጥቅ ለማስፈታት እንቅስቃሴ የጀመረበትና ሌሎችም ስምምነቱን ለመተግባር ያለውን አዎንታዊ እንቅስቃሴዎች መመልከት ተችሏል። ይሄም በጎ ጅምር ነውና ለሕዝቦች ሰላም ሲባል ስምምነቱን ለመተግበር ያለውን ቁርጠኝነት ከዚህም በላይ አጠናክሮ ማስቀጠል ይኖርበታል።

በአንጻሩ በውጪም በውስጥም ያሉ ሰላም ጠል ኃይሎች ከግጭት የሚያገኙትን ትርፍ በማስላት የሰላም ስምምነቱ ተግባራዊ እንዳይሆን ዘርፈ ብዙ ጥረቶችን ሲያደርጉ ይስተዋላል። እነዚህ ኃይሎች ስምምነቱን ሲቃወሙም ሆነ ስምምነቱ ወደተግባር እንዳይለወጥ በሚችሉት ሁሉ ጫና ለማሳደር ሲጥሩ የመታየታቸው መሰረታዊ ምክንያት፣ የትግራይ ወይም እንደ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ከሰላሙ ያለውን ተጠቃሚነት ተሰውሮባቸው አይደለም።

ይልቁንም የሰላም ስምምነቱ ተተግብሮ አገር ሰላም ከሆነችና ህዝቦች በፍቅር አብረው መኖር ከጀመሩ እነሱ በግጭት ምክንያት የሚያገኙት ጥቅም ይቀርብናል ከሚል መነሻ ነው። ይህ ደግሞ ሊሆን የማይገባው ከሕዝብ ይልቅ ለራስ ጥቅምና ፍላጎት የመገዛት የከፉዎች አካሄድ በመሆኑ በቃ ሊባል ይገባል። ስለሆነም ለህዝቦች ዘላቂ ሰላም ሲባል የሰላም ስምምነቱን ተግባራዊ ማድረግ ብቸኛው አማራጭ መሆኑን ተገንዝበው፤ በመንግስት በኩል ያሉ ጥረቶችን ማገዝ፤ በሕወሓት በኩል የተጀመሩ አዎንታዊ እንቅስቃሴዎችንም ማበረታታት በእጅጉ አስፈላጊ መሆኑ ሊተኮርበት ይገባል!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ:- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከትናንት በስትያ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርበው ከምክር ቤቱ አባላት ለተነሱ ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ የሰጡት ማብራሪያና ምላሽ፤**

## የምንጠብቀው የተጀመረው ሰላም ዘላቂ እንዲሆን ነው

**አልማዝ አያሌው**

ከብዙ መውጣት መውረድና ድካም በኋላ የሰሞኑ የሰላም ወሬ በዚህም በዚያም ሲነፍስ መንፈሴ ሁሉ አረፍ አለ። አየሩ ሁሉ ተቀየረ። ጥሩ ጥሩ መዓዛ ሸተተኝ። ሰላም ነዋ፤ የምንሻው ሰላም። ዋጋው ተመን የማይወጣላት ሰላም አይደል። የሰው ልጆች ሁሉ፣ በምድር ላይ የሚኖሩ አእዋፋት፣ እንስሳት እጽዋት በአጠቃላይ ህይወት ያላቸው ሁሉ የሚሹት ዋናው ጉዳይ ነውና ሁሌም «ሰላም... ሰላም... ሰላም ይሁን ለሰው ልጆች ሁሉ ሰላም» የሚለው ቢዘመር ብሰማው ምኞቴ ነው ። ምክንያቱም ካለሰላም ምንም ነገር የለም። ሰላም ከሌለ ወጥቶ መግባት፤ ዘርቶ መብላት፤ ነግዶ ማትረፍ፤ ወልዶ መዳር... ሁሉ ተረት ተረት ይሆናሉ። አይደለም ይሄ የበሰለ ምግብ ጠቅልሎ መጉረስ ያለ ሰላም ሊሆን አይችልም።

በእርግጥ የጦርነትን አስከፊነት በቦታው ላይ ሆኜ አላየሁም። በአካል ተገኝቼ አልተሰቃየሁም። ነገር ግን የወገኖቼን ስቃይ እዚሁ ሆኜ አይቼዋለሁ። በአእምሮዬ ኖሬዋለሁ። ቤት የነበራቸው ከቤታቸው ተፈናቅለው። ሰርተው የሚበሉ ተመጽዋች ሆነው። ሀብታም ያልናቸው ንብረታቸው ወድሞ፣ ቤታቸው ተቃጥሎ፣ ተዘርፎ የሞቱት ሞተው የተረፉት ሲያነቡ አይቻለሁ። ለቅሶም በማዕረግ ሰላም ሲኖር ነው። ካልሆነ ለቅሶ በአይን በእንባ መሆኑ ቀርቶ አንጀት እያረረ ወደ ውስጥ ይሆናል። አንዳንድ ቦታዎችም ይሄ አልሆነም ለማለት ያስቸግራል። ብዙ አስከፊና አሰቃቂ ነገሮች አጋጥመዋል።

ይሄ ተረት ተረት አይደለም። በሀገራችን የሆነ በየመገናኛ ብዙሀኑ የተዘገበ ነው። የሰብአዊ መብት ተቋማት ያረጋገጡትና የመሰከሩት እውነት ነው። በእኛ ዘመን ባለፉት ሁለት ዓመታት የገጠመን ነው። የጦርነት አስከፊነት በሶሪያ፣ በሊቢያ፣ በየመን፣... እያልኩ ለመጥቀስ አይደለም። ወቅታዊውን ሩሲያና ዩክሬንን እያነሳሁ አይደለም። ያነሳሁት በዘመናችን በአገራችን ያየነውን አስከፊ ጦርነት ነው። ልጅን ከእናት የሚለይ፣ ሰዎችን ከቀያቸው የሚያፈናቅልና የሚያሰድድ፣ ንብረት የሚያወድም፣.... በቅርብ ርቀት ያየነው ነው። በራሳችን ወገን ራሳችን ላይ ሆኖ ስናየው ደግሞ ህመሙ ዘልቆ ወደ ልባችን ይገባል። አንጀት ያላውሳል። እናም ደጋግሜ ደጋግሜ ያንን ሳስብ ጦርነት አይበጅም! ለማንም አይሆንም! ኪሳራ እንጂ ትርፍም የለውም እንድል አገደዳለሁ።

ምክንያቱም ጦርነትን በተለያየ መንገድ አይቼዋለሁ። በማህበራዊ ህይወት፣ በኢኮኖሚ፣ በስነልቡና፣... እንድንፈተን አድርጎናል። እናም ሰው እንዴት ሰላምን ይጠላል ስል ለራሴ ደጋግሜ ሰላምን ሰበኩ። ሁሉም ሰው ወደደም ጠላም የሚያስፈልገው ሰላም ነው። ሰላም አስፈላጊ መሆኑ ማንም ለማንም ሊነግረው አይገባም። ሆኖም ደግሞ የግጭት አትራፊዎች፣ ተቀጣሪና ተገዢዎች አይጠፉምና ከሰላም ይልቅ ጦርነት ሲሰብኩ ይውላሉ፤ ያድራሉ። በፊትም አሁንም ምናልባትም ወደፊት ከሰላም ይልቅ ጦርነት ለእኛ ይሆናል ብለው እጃቸውን የሚያወጡ አይኖሩም ብሎ ማሰብ አይቻልም።

ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፓርላማ ማብራሪያቸው፣ «ሰላምን የሚጠሉ የጦርነት ነጋዴዎች አሉ፤ ጦርነት የሚጠሉ የሰላም አምባሳደሮች አሉ። ግራ የሚያጋባው ሰላምም ጦርነትም የማይፈልጉት ላይ ነው» ያሉትን ደጋግሜ አዳመጥኩ። እርግጥ ነው ሰላምን የማይፈልጉ በመኖራቸው እኮ የሰላም ድርድር ተካሂዶ እንኳን አርፈው አልተቀመጡም። በውጪ ሆነው ቀዝቃዛውን አየር እየተነፈሱ፣ በርገራቸውን አማርጠው እየገመጡ፣ በተንፈላሰሰ ኑሮ ሆነው ልጆቻቸውን እያስተማሩ፣ ወጣቶቹም እየተማሩ፣ ረሀብን ሳያዩ፣ የጥይት ድምጽ ሳይሰሙ ውለው እያደሩ ጦርነት ይቀጥል ሲሉ አደባባይ ወጥተዋል። ምክንያቱም ትርፍ አለዋ። ዶላር ይሰበሰቡበታላ። ደሀው እየሞተ እነሱ በግጭት ይነግዳሉ።

ሀገራችን ግን የሚያስፈልጋት ሰላም ነው። ልማት ነው። መስራት መለወጥ ነው። ከተመጽዋችነት መውጣትና መጽዋች መሆኑ ነው ግባችን። ለዚህ ደግሞ ሰላም ያስፈልጋል። ይሄንኑ በማሰብ መንግስት የሰላም እጆቹን የዘረጋው ገና ከለውጡ ማግስት ነው። ለሀገራችን ግጭት ጦርነት አያስፈልጋትም፤ የሚያስፈልገን ሰላም ነው፤ አንድነት ነው። እናም ችግሮችን በራሳችን መንገድ በውይይት መፍታት፣ ጥፋቶችን በይቅርታና በምህረት መተላለፍ ለነገዋ ኢትዮጵያ መሰረት መጣል ነው ብሎ የሰላም እጁን በየአቅጣጫው ዘርግቶ ነበር።

ለዚህም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሹመታቸው ማግስት በየአካባቢው በመዘዋወር ችግሮችን ለማድመጥ ጥረት አድርገዋል፤ መፍትሄ ያሉትንም ለማስቀመጥ ሞክረዋል። በዋነኛነት ግን ለሁሉም የሚሆነው ሰላምና አንድነት ነውና ይሄንኑ እናስቀድም ሲሉ ደጋግመው ተናግረዋል፤ መክረዋል። ባህላዊ በሆኑ ሃይማኖታዊ በሆኑ ልምምዶቻችን ችግሮቻችንን እንፍታ ሲሉ ነበር ደጋግመው ተማጽነዋል።

በዚህም አላቆሙም እኔ ሰላም ብሆን ጎረቤት ሰላም ውሎ ሰላም ካላደረ ሰላም የለምና እኛ ብቻም ሳንሆን ከጎረቤቶቻችን ጋር ፍቅር እንሁን ብለው ጥረት አደረጉ። ከኤርትራ ጋር 20 ዓመት ላላነሰ ጊዜ የቆየውን ችግር በሰላማዊ ጉርብትና በመቀየር የሰላምን ሀያልነት ለአለም አሳዩ። ይሄም ለትልቅ ሽልማት ያበቃቸው ሀገራችንንም በዓለም አደባባይ ደምቃ እንድታይ የዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሀን አጀንዳ እንድትሆን ያደረገ ክስተት ሆኖ አልፏል። ይሄ በእያንዳንዳችን ልብ ደግሞም በታሪክ መዝገብ ታትሞ ይኖራል።

ሰላም በቀላሉ የማይገኝ ከተገኘም ጉልበቱ ሀያል ነውና ይሄንኑ ሀያልነቱን ለማስቀጠል በተለይም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የነበረውን ሁኔታ ወደ ሰላማዊ መንገድ ለማምጣት ብዙ ጥረት ተደርጓል። ታዋቂ ሰዎችን፣ የሰላም እናቶችን ወደ ክልሉ ሄደው የሕወሓት አመራሮችን እንዲያነጋግሩ ሰፊ ጥረት፣ ተደጋጋሚ ሙከራ ተደርጓል። ሆኖም ግን በወቅቱ የተገኘው ምላሽ ሰላምን የሚያመጣ ሳይሆን ለብዙዎች ሞት፣ አካል መጉደል፣ መፈናቀል፣ መራብና መጠማት፣ ስቃይና እንግልት ምክንያት ሆኗል።

አባቶች አንድን የሞተ ሰው ጉዳይ ሊያነሱ ሲሉ «ሙት ወቃሽ አያድርገኝ እና» ብለው ይጀምራሉ። እናም እላለሁ ያለፈውን በማንሳት ጊዜና ጉልበት ማባከን አያስፈልገም። መጸጸትም አይበጅም። ይልቅ አሁን ለተጀመረው የሰላም አየር መዝለቅ አጋዥ መሆን ያስፈልጋል። ምንም ቢሆን ከትናንቱ ጥፋት የነገው መልካም ነገር ይበልጣል ብሎ ማመን ይሻላል። ለዚህም መስራት ይጠቅማል። መንግስትም ቀደም ሲል ሲለው የነበረውን አሁንም ወደፊትም የሚለውን የሰላም መንገድ አጥብቆ ከመሻት ወደ ኋላ አላለም።

የሀገራችንን ችግሮች በሀገራችን ሽምግልና እንፍታ ብሎ ባይሳካ ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄ የሚለው ውጤት አምጥቷል። ይሄ የራስን ችግር በራስ የመፍታት ራዕዩን አሳክቷል። የአፍሪካ ህብረት አደራዳሪነት በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ከተማ የተደረሰው የሰላም ስምምነትም የመንግስት የቀደመው የሰላም ፈላጊነቱ ውጤት ነው። ለሰላም የዘረጋው እጁንም እስከ ሰላም ስምምነቱ አድርሷል። ይሄ የሰላም መሻት ውጤት አምጥቶ ዛሬ የሰላም አየር በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል፣ የሰላም አየር በሀገራችን መተንፈስ ጀምረናል። አሁን የምንጠብቀው ዛሬ የተጀመረው የሰላም አየር ዘላቂ እንዲሆን ነው። ቁስል ጠባሳ እያየን ሳይሆን ቂምና ቁርሾን ትተን በአንድነት ሰላማችንን ማስጠበቅ የጎደለብንን በጋራ መሙላትን መለማመድ አለብን። መቼም በምን ውስጥ ምን አይጠፋም እንደሚባለው ሁሉ በሰላም መሻት ውስጥ ጦርነት ናፋቂ አይጠፉምና ጆሮ እንንፈገው!።

# ነፃ ሃሳብ



**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፅሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ዴንግ ዣውፒንግ፡-
## ቻይናን ከድህነት አረንቋ አውጥተው ከኃያላን ተራ ያሰለፉ ታላቅ መሪ፤

ትውልድ የሚታነጸውና የሚቀረጸው በአርዓያና በምሳሌ ጭምር ነው ብዬ በብርቱ ስለማምን ከዚህ በቀደመው መጣጥፌ ስለ ብራዚሉ ፕሬዚዳንት ሉላ ዳ ሲልቫ አስነብቤ ነበር ። ዛሬ ደግሞ በሌላ አርዓያና ምሳሌ በሚሆን መሪ ተመልሻለሁ። እንደ አምላኬ ፈቃድ በቀጣይ መጣጥፎቼ በየጣልቃው ከአፍሪካም ከሀገራችንም መሪዎች ጋርም አስተዋውቃችኋለሁ ። በዚሁ አጋጣሚ ለልጆቻችንና ለትውልድ ምሳሌና አርዓያ እንድንሆን እጠይቃለሁ ። በነገራችን ላይ ሁላችንም መሪዎች ነንና በየአለንበትና በየተሰማራንበት ኃላፊነታችንን እንወጣ። ኃላፊነታችንን ስላልተወጣን የዘራነውን እያጨድን እንገኛለን።

የቻይና ጉዳይ በተነሳ ቁጥር ዛሬ ድረስ እንደ ትንቢት ወይም ንግርት/forshadow/ ሆኖ የሚወሳ የናፓሊዎን ቦናፓርት አባባል አለ። “ቻይናን ተዋት ። ትተኛ ። አትቀስቅሷት ። ስትነቃ አለምን ስለምትገለባብጠው፤ ብሎ ነበር ። እንደተነበየው አልቀረምም “ቻይናም ናፓሊዎን ያለውን አምና የተቀበለች ይመስል ፤ “ለ200 አመታት በሯን ጠርቅማ ለሽ አለች ፤ “ይለናል የCNN GPS አዘጋጅና የዋሽንግተን ፖስት አምደኛ ፋሪድ ዘካሪያ፡፡ በ1979 ዓ.ም የቻይናም የአለምም ታሪክ ላይመለስ የተቀየረበት አመት ነው። ሶቪየት አፍጋኒስታንን በመውረር የቁልቁለት ጉዞዋን አሀዱ ስትል ፤ ቻይና በምንጊዜም ባለውለታዋ ፕሬዝዳንት ዴንግ ዣውፒንግ አማካኝነት የኢኮኖሚ ማሻሻያን አወጀች ። ከዚህ በኋላ ለ30ና 40 ተከታታይ አመታት በተመዘገበ ዕድገት በመቶ ሚሊየኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ከድህነት አረንቋ ወጡ ። ቻይናም ከአሜሪካ ቀጥላ 2ኛዋ ኃያል ሀገር ለመሆን በቃች ። በጥቂት አመታት አንደኝነቱን ከአሜሪካ ትረከባለች ተብሎ ይጠበቃል።

በ2ኛው የአለም ጦርነት አሜሪካ ከጃፓን ጋር ጦርነት ላይ ስለነበረች ፤ የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው በሚል ስሌት የቻይና ወዳጅ ሆነች። የጸጥታው ምክር ቤት አባል እንድትሆን ደገፈቻት ። ሆኖም ይህ ያልተቀደሰ ጋብቻ ብዙ አልዘለቀም ይለናል ፋሪድ፤ ኮምኒስት ፓርቲው በ1949 ወደ ገዥነት ሲመጣ የሁለቱ ሀገራት እህል ውሃ አለቀ ። ሆኖም ከማኦ ዜዱንግ ሞት በኋላ የሀገራቱ ግንኙነት እንደገና ታደሰ ። ዴንግ ቻይና ከርእዮተ አለም ይልቅ ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት ቅድሚያ ትሰጣለች፤ ድመቷ ነጭ ትሁን ጥቁር ዋናው ቁምነገር አይጥ መያዟ ነው ሲሉ በዘመናዊ ቻይና ታሪክ ሲዘከር የሚኖር ንግግር አደረጉ።

ከዚህ በኋላ በቻይና የተስተዋለው ዕድገትና ብልጽግና ተአምር ነው ይለናል ፋሪድ ፤ THE POST-AMERICAN WORLD በተሰኘው ማለፊያ መጽሐፉ ፤ በሰው ልጆች ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የቻይና ኢኮኖሚ ለ30 ተከታታይ አመታት በየአመቱ 9 በመቶ ዕድገት አስመዝግቧል። በእነዚህ አመታት ከ400 ሚሊየን በላይ (አንዳንድ ምንጮች 1ቢሊየን ያደርሱታል) ቻይናውያን ከከፋ የድህነት አረንቋ ወጥተዋል ። የአብዛኛው ቻይናዊ ገቢ በሰባት እጥፍ አድጓል ። ቻይና በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት የሚጎመጁለት ዕድገት እያስመዘገበች ነው ።

የ”The economist”ጸሐፊ ጄፍሪ ሳቸስ “በአለም የእድገት ታሪክ ቻይና ያስመዘገበችውን ብልጽግና የሚስተካከል የለም፤” ይለናል ። ባለፉት ጥቂት አመታት በቻይና የተመዘገበው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የሚታመን አይደለም ። ለ30 ተከታታይ አመታት በየስምንት አመቱ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በእጥፍ አድጓል ። በ2008 ዓም ቻይና 200 የአየር ማቀዝቀዣዎችን ታመርት ነበር ሲል ፋሪድ ያስታውሰናል ። በ2005 ዓ.ም ግን 48 ሚሊየን ኤይር ኮንዲሽነሮችን አመረተች ። ቻይና ዛሬ ላይ ይሄን በአንድ ቀን ታመርተዋለች ። ፋሪድ ዘካሪያ በ1993 ዓም ሻንጋይን ስጎበኝ ምስራቁ የከተማው ክፍል ፑዶንግ ያለማ ገጠር ነበር ። ዛሬ ግን የፋይናንስ መናኸሪያ ፤ የሰማይ ጠቀስ ፎቆች ከተማ ነው ። በምሽት እንደ ገና ዛፍ የሚያበሩ ህንጻዎች የተገጠገጡበት ይለናል ። ከለንደን የፋይናንስ መናኸሪያ ካናሪ ኋርፍ ስምንት እጥፍ የሚበልጥ ፤ ከቺካጎ አነስ ያለ ከተማ ሆኗል። ቾንግኪንግ በቺካጎ አምሳል እየተገነባ ያለ ሌላ ከተማ ሲሆን፤ በየአመቱ 300ሺህ ሰዎች ለመኖሪያነት ይጎርፉበታል።

በአለማችን በፈጣን ዕድገት የሚያስመዘግቡ 20 ከተሞች በሙሉ በቻይና የሚገኙ ናቸው ። ምዕራባውያን ለንግድ መናኸሪያዋ ሻንጋይ ቢያደሉም ፤ የፖለቲካ ፣ የባህል ፣ የስነ ጥበብና የኢኮኖሚ መዲና የሆነችው የቤጂንግ ዕድገትም ለማመን የሚከብ ነው ። ከተማዋ የ2008 ኦሎምፒክን ለማስተናገድ እንደገና ፈርሳ ተሰርታለች በሚያስብል ሁኔታ ተለውጣለች ። ትነጻጸር ከተባለ የሀውስማን የእጅ ስራ ከሆነችው ፓሪስ ጋር ነው የምትነጻጸር ይለናል ፋሪድ ፤ በቤጂንግ ኦሎምፒክ ሰበብ በአለማችን ትልቁ የአውሮፕላን ማረፊያ ፤ ስድስት የመሬት ውስጥ የባቡር መስመር ፤ 43 ኪሜ የሚረዝም የቀላል ባቡር መስመር ፤ አዳዲስ የመኖሪያ መንደሮች ፤ 125 ኪሜ የሚረዝም የአረንጓዴ ቀበቶ ፤ 12 ስኩየር ኪሜ የሚሰፋ የኦሎምፒክ ፓርክ ገንብታለች ። የአዲሷን ቤጂንግ ፕላን ለተመለከተ ቀድሞ ወደ አእምሮው የሚመጣው የአልበርት ስፒር የእጅ ስራ የሆነችው የድህረ ጦርነቷ በርሊን ናት ። የአልበርት ልጅ አልበርት ስፒር ጁኒየር በቤጂን ኦሎምፒክ ፓርክ የ8 ኪሜ ሰፊ መንገድ ዲዛይን ላይ ተሳትፏል ። ቤጂንግን አባቴ ዲዛይን ካደረጋት በርሊን ጋር ማነጻጸር የሰማይና የምድር ያህል ልዩነት አለው ይለናል ።

ቻይና በአለማችን በድንጋይ ከሰል ፣ በብረትና ሲሚንቶ ምርት የሚወዳደራት የለም ። በ2005 ዓም በቻይና 28 ቢሊየን ስኩየር ፊት ስፋት ባለው ስፍራ ግንባታ ይካሄድ ነበር ። ይህ ከአሜሪካ ጋር ሲነጻጸር በአምስት እጥፍ ይበልጣል ። ባለፉት 15 አመታት ወደ አሜሪካ የምትልከው ኤክስፖርት በ1600 በመቶ አድጓል ። በዘመነ የኢንዱስትሪ አብዮት እንግሊዝ የአለም የስራ ቦታ(ወርክሾፕ)ነበር የምትባለው ። ይሄ ስያሜ ዛሬ ለቻይና ተሰጥቷል ። የአለማችንን ሁለት ሶስተኛ የፎቶኮፒ ማሽን ፣ ማይክሮዌቭ አቨን ፣ የዲቪዲ ማጫዎቻና ጫማ ቻይና ታመርታለች ። በአለማችንም በአሜሪካም ግዙፉ ወልማርት በየአመቱ 18 ቢሊየን ዶላር የሚያወጡ ሸቀጦችንና ምርቶችን ከቻይና ያስገባል ። የቻይና ንግድ ከሀገር ውስጥ ጥቅል ምርቷ የ70 በመቶ ድርሻ መያዙ ኢኮኖሚዋ ለአለም ገበያ ምን ያህል ክፍት እንደሆነ ያሳያል ይለናል ፋሪድ ዘካሪያ። ባለፉት 15 አመታት ከአሜሪካ የምታስገባው ሸቀጥና ምርት በሰባት እጥፍ አድጓል። ፕሮክተርና ጋምብል ናው የተባሉ የአሜሪካ ኩባንያዎች ከቻይና በየአመቱ 2ነጥብ5 ቢሊየን ዶላር ገቢ ያገኛሉ። ስታርባክስ ከአሜሪካ ይልቅ በቻይና ያሉ የካፌ ቅርንጫፎቹ ቁጥር ብልጫ አላቸው ። ቻይና ለአለማቀፍ ብራንዶች በሯ ክፍት ነው።

የሚያማምሩ ሕንጻዎቿም በውጭ አርክቴክቶች ዲዛይን የተደረጉ ናቸው ። የቤጂንግ ኦሎምፒክ የመክፈቻ ስነ ስርዓትን እንዲያማክር የመረጠው ታዋቂውን አሜሪካዊ የፊልም ዳይሬክተር ስቴቨን ስፒልበርግን ነው። ቻይና ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ያካበተች ሀገርም ናት ። 3.13 ትሪሊየን ዶላር አላት ። ከአውሮፓ ሕብረት ሶስት እጥፍ ፤ ከጃፓንና ጀርመን ደግሞ የ50 በመቶ የሚበልጥ፤ ይህ ቻይና ለየትኛውም የኢኮኖሚ ቀውስ የማትበገር ሀገር መሆኗን ያረጋግጣል ። ቻይና የአለማችን ታላቋ ሀገር ናት ። ይህ ብቻ አይደለም ። ቻይና ባለፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ፣ ግዙፍ ማኑፋክቸረር ፣ 2ኛው ግዙፍ ሸማች ፣ ግዙፍ ቆጣቢና ከአሜሪካ ቀጥላ ለጦሯ ከፍተኛ በጀት የምትመድብ ሀገር ናት።

ቻይና በመቶዎች ለሚቆጠሩ አመታት በድህነትና ኋላቀርነት ፣ በንጉሳዊ አገዛዝ ፣ በእርስ በርስ ጦርነት ፣ ደም አፋሳሽ በሆነ አብዮት ማቅቃለች ። በማኦ ዜዱንግ “ታላቁ እመርታ” የሕብረት ስራ ማህበራትን ለማስፋፋት በተካሄደ የባህል አብዮት 38 ሚሊየን ቻይናውያን አልቀዋል። በሚሊየኖች የሚቆጠሩ ባለሙያዎች፣ ልሒቃንና ተመራማሪዎች በዚሁ የባህል አብዮት ተጨፍጭፈዋል ። ከዴንግ ዣውፒንግ የማሻሻያ መርሀ ግብር በኋላ ግን ቻይናውያን እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆኑ ይለናል ፋሪድ ዘካሪያ ፤ ዛሬ የቻይና መሪዎች ፣ የንግዱ ማህበረሰብ አባላትና የሕዝቡ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ፍላጎት የተጀመረውን ተአምራዊ እድገት ማስቀጠል ነው ። ላለፉት 30ና 40 አመታት እየተመዘገበ ያለው ፈጣንና የኢኮኖሚ ዕድገት ፣ ብልጽግናና መረጋጋት ለአፍታ እንዲስተጓጎል አይፈልጉም።

አሜሪካ ስታስነጥስ የተቀረው አለም ጉፋን ይይዘዋል የሚለው አባባል ዛሬ ዛሬ ቻይና ስታስነጥስ የተቀረው አለም ጉፋን ይይዘዋል ወደሚል እየተቀየረ ነው ። የቻይና የተጽዕኖ አድማስ ወሰን ፣ ባህር ፣ ውቅያኖስና አህጉር አይወስነውም ። እንዲህ ያለ ተጽዕኖ ያላቸው ሀገራት ድንገት አይፈጠሩም ። ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ወታደራዊ ተጽዕኗቸው በአንድ ጀምበር አልተፈጠረም። በአንድ ጀምበርም አይጠፋም ። ይህ ተጽዕኖ አሜሪካ፣ ብሪቴን ፣ ፈረንሳይ ፣ ጀርመንና ራሽያ ላለፉት 200 አመታት ከፍ ዝቅ እያለ መቀጠሉን ፋሪድ ያስታውሳል። “DENG XIAOPING: THE MAN WHO MADE MODERN CHINA”የሚለው መጽሐፍ ደራሲ ማይክል ዲሎን ደግሞ፤ ዴንግ ዣዋፒንግ ከ1970ዎቹ ጀምሮ በአራቱ አዘማኞች ማለትም በግብርና ፣ በኢንዱስትሪ፣ በወታደራዊ ሳይንስ፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ 1ቢሊየን ሕዝብ ከድህነት አረንቋ ከማውጣት ባሻገር ቻይናን ከኃያላን ተራ አሰልፈዋል። ይህ የዴንግ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ለዘመናዊ ቻይና ወሳኝ መታጠፊያ ነው ። ዛሬ ከአሜሪካ ቀጥላ ግዙፍ ኢኮኖሚ ገንብታለች። የአሜሪካ ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት ከ25 ትሪሊየን ዶላር በላይ ሲሆን የነፍስ ወከፍ ገቢዋ ደግሞ ከ76 ሺህ ዶላር በላይ ነው ።

የቻይና የሀገር ውስጥ ጥቅል ምርት ወደ 20 ትሪሊየን ዶላር የሚጠጋ ሲሆን የነፍስ ወከፍ ገቢዋ ደግሞ ወደ 15 ሺህ ዶላር ይጠጋል ። በ1989 ዓም በቻይናሚን አደባባይ የተቀሰቀሰውን አመጽ በኃይል ለማክሸፍ የሔዱበት ርቀት የፕሬዚዳንት ዴንግን ስም ክፉኛ አጠልሽቶታል ይለናል ማይክል ፤ ዴንግ ዣውፒንግ ሲሹዋን ጠቅላይ ግዛት ከሚገኝ አናሳ ማህበረሰብ የተገኙ ፤ በግል ጥረታቸውና በትምህርት ለቻይና ኮምኒስት ፓርቲ ከፍተኛ አመራርነት የበቁ ናቸው በማለት ይነግረናል ። ዴንግ ዣውፒንግ ራሳቸውን ለኮምኒዝም አሳልፈው የሰጡና ከ1958 እስከ 1961 ዓም ታውጆ የነበረው ታላቁ እምርታ/Great Leap/ አካል የነበሩ መሪ ናቸው ይለናል ማይክል፤ ከማኦ ዜዱንግ ጋር በተፈጠረ የመስመር ልዩነት በባህል አብዮቱ ወቅት ለስደት ተዳርገው ነበር ሲል ያስታውሰናል።

ሾጌል እዝራ ደግሞ፤”DENG XIAOPING AND THE TRANSFORMATION OF CHINA” በተሰኘ ማለፊያ መጽሐፉ ፤ ማኦ በአንድ ወቅት ዴንግን የቻይናን ኢኮኖሚ የሰፋ መርፌ ሲሉ ይገልጹታል። ዴንግን የቻይናን ተአምራዊ የኢኮኖሚ ማሻሻያ በጥብቅ ዲሲፕሊን የመሩ ፣ ማኦ ዜዱንግን የማምለክ አባዜን የሞገቱ ይላቸዋል ። የቻይናን የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፖሊሲዎችን ለቀቅ በማድረግ ለእድገት ያመቻቹ ፤ ኢኮኖሚውን ለምዕራባውያን የከፈቱ መሪ ፤ የዴንግ ዣውፒንግ የኮምኒስት ፓርቲ አባልነት መሠረት የተጣለው በ1920ዎቹ በሀገረ ፈረንሳይ ትምህርት ላይ እያለ ነው ። ግማሽ ክፍለ ዘመን የተሻገረው የዴንግ የፖለቲካ ህይወት ብዙ ውጣውረድ አሳልፏል ይለናል ሾጌል። በ1978 ወደ ስልጣን እስኪመጡ ድረስ ዘለፋን ፣ መገፋትንና ስደትን አስተናግደዋል። ወደ አገዛዝ ከመጡ በኋላ የተሳሳተውን የማኦ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በመቀየር የቻይናን ገበያ ለአለም ከፍተዋል ።

ዴቪድ ሻምባው “CHINA AND THE WORLD”በተሰኘው መጻፉ ቻይና የቀጣዩን አለም አሰላለፍ ከሚወስኑ ኃይላት ግንባር ቀደሟ ናት ይላል ። የትኛውም ሀገር ፣ ማንኛውም ማህበረሰብ የቻይናን ጉልህ ስፍራና ተጽዕኖ ባላየ ባልሰማ ሊያልፈው አይችልም ። ቻይና ከ30 አመት በፊት አይደለም በአለማቀፍ መድረክ በጎረቤቶቿ እንኳ ይሄ ነው የሚባል ተጽዕኖ መፍጠር የማትችል ፤ ጂኦፖለቲካዊ ጠቀሜታዋም ዝቅተኛ ነበር ሲል ያስታውሰናል ። ዛሬ ግን ይለናል ዴቪድ ሻምባው ባስመዘገበችው ፈጣንና ተከታታይ የኢኮኖሚ ዕድገት የተነሳ ተጽዕኖዋን የማታሳርፍበት ሀገርና ዘርፍ የለም ። በማዕድን ፍለጋ ፣ በውጭ ምንዛሬ ገበያ ፣ በመካከለኛው ምስራቅ ነዳጅ ፣ በላቲን አሜሪካ የግብርና ውጤቶችና በሩቅ ምስራቅ ፋብሪካዎች ሳይቀር ተጽዕኖዋ የጎላ ነው። በኢኮኖሚዋ ፣ በወታደራዊ ኃይሏ ፣ እያደገ በመጣው ባህላዊ ተጽዕኖዋ፣ በዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴዋና በገነባቻቸው ተቋማት ወደፊት እየመጣች ነው። ቻይና የሆሊውድን ፊልም ስክሪፕት ከመመርመር አንስቶ ቻይናን አዋርደዋል ያለቻቸውን ተዋንያን እስከማገድ ደርሳለች።

ስለቻይና እና ቲቤት የሰብዓዊ መብት አያያዝ የተቹት ማት ዲመን ፣ አንጀሊና ጆሊና የዳላይ ሌማ አድናቂው ሪቻርድ ጌሬ ለቻይና ሲባል ከሆሊውድ ገለል እየተደረጉ ነው ። የወል ስትሬት ጆርናሉ የምርመራ ጋዜጠኛ ሰሞኑን ለንባብ ባበቃው “The red carpet” በተሰኘው መጽሐፉ ፤ ሆሊውድም ሆነ ሌሎች የመዝናኛው አለም ኩባንያዎች የቻይናን ሰፊ ገበያ ላለማጣት ሲሉ ራሳቸውን ለቅድመ ምርመራ አሳልፈው ሰጥተዋል ይለናል ። “Seven years in Tibet”እና “TRANSFORMERS 4”የተሰኙ ፊልሞች ከኮምኒስት ፓርቲው የቻይናን ገጽታ ያጎድፋሉ የሚል ቅሬታ ስለቀረበባቸው እንደገና ተከልሰዋል።

ለዚህ ትውልድ የቻይና ፈጣን ዕድገት እንደ ዋዛ የሚታይ ሳይሆን ሌት ተቀን ትኩረት ሰጥቶ የሚከታተለው ጉዳይ ነው ። ባለፉት 40 አመታት እንደቻይና በፍጥነት ያደገና የዘመነ ሀገር የለም ። ከኋላቀርነትና ከድህነት ተላቅቃ በአለማችን 2ኛውን ኢኮኖሚ ገነባች ። በአጭር ጊዜ ውስጥ አንደኝነቱን ከአሜሪካ ትረከባለች ይለናል ዴቪድ ፤ በአለማቀፍ መድረክ የሚኖራት ተጽዕኖም የዛኑ ያህል ያድጋል ።

ከአሜሪካ ፣ ከራሽያ ፣ ከአውሮፓ ሕብረትና ከጎረቤቶቿ ጋር ያላት ግንኙነት በእነሱ ፍላጎትና ጥቅም ብቻ የተመሠረተ መሆኑ ከቀረ ሰነባበተ። ኢኮኖሚዋ አለማቀፋዊ እየሆነ ነው። ከአንታርቲካ እስከ ህዋ እየሰፋ ነው ይላል ዴቪድ ፤ ፈጣኑና ዘመናዊው ወታደራዊ ዕድገቷ በጎረቤቶቿ ላይ ፍርሀትና ስጋት እየፈጠረ ነው። እንደ ጃፓንና ፊሊፒንስ ያሉ የደቡብ ምስራቅ እስያ ሀገራት ለዚህ ጥሩ ማሳያ ናቸው ። እስከ ቀደሙት 20 አመታት ደቡብ ምስራቅ እስያ በአሜሪካ ተጽዕኖ ስር ነበር። የቻይናን ፈጣን ዕድገት ተከትሎ ግን ቀጣናው የሁለቱ ኃያላን መፎካከሪያ እየሆነ ነው ። የጂኦፖለቲክስ ስበቱ ወደ ቻይና እያመዘነ ይገኛል ።

ፈጣሪ የሀገራችንን ሰላም ያጽናልን! አሜን፡፡

# ወቅታዊ

# ‹‹ባህላዊ ጨዋታችን ማድረግ ያለብን ሰላምን ነው››

*- ዶክተር ዮናስ አዳዬ*
*የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር*

**አስቴር ኤልያስ**

*ሁሌም ቢሆን ጦርነት መጥፎ ነገር፣ ሰላም ደግሞ የሁሉም ነገር መሠረት ነው። የሰላም መስፈን ትርጉሙ ሰፊ ነው። ሰላም በሌለበት ቀጣና የሚታቀድም የሚተገበርም ሥራ ስንኩል ነው። ሰላም ጠፍቶ በጦርነት ጎዳና ከዓመታት በላይ መዝለቅ ደግሞ እንደ ሰው መሰደድ፤ እንደ አገር ደግሞ መፍረስን ያስከትላል።*

*ምንም እንኳ ለሰላም መስፈን የፌዴራል መንግሥት አስቀድሞም ቢሆን ጽኑ አቋም የነበረው ቢሆንም እንደዋዛ ተገዶ በገባው ጦርነት ለሁለት ዓመት ያህል ዋጋ ሲከፈል መቆየቱ ይታወቃል። በቅርቡ ግን በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶርያ ብሎም በኬንያ ናይሮቢ የሰላም ስምምነት ላይ የተደረሰ መሆኑ እርግጥ ነው። ይህን የሰላም ስምምነት ወደመሬት ለማውረድ ምን መደረግ አለበት በሚልና በሌሎችም ወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሰላም ጥናት ተባባሪ ፕሮፌሰር እንዲሁም በአሁኑ ወቅት በአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ውስጥ የኮሙኒኬሽንና ሚዲያ ክፍል ኃላፊ ሆነው እያገለገሉ ከሚገኙት ኮሚሽነር ዶክተር ዮናስ አዳዬ ጋር አዲስ ዘመን ያካሄደውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አጠናቅሮ አቅርቧል።*

**አዲስ ዘመን፡- ሰላም ምን ማለት ነው? የሰላም ፋይዳስ እንደምን ይገለጻል ከሚለው ነጥብ ቃለ ምልልሳችንን እንጀምር?**

**ዶክተር ዮናስ፡-** መልካም፤ ሰላም የውስጥ እርካታ ነው፤ ሰላም እረፍት ነው። ሰላም ከራስም ከፈጣሪ ጋርም መስማማት ነው። ሰላም ከሰውም ከተፈጥሮ ጋርም መስማማት ነው። ብዙዎች ሰላምን ከግጭት እና ከጦርነት ጋር በተቃራኒ ያለ ብቻ አድርገው ይቆጥሩታል፤ ሰላም ግን ከአስተሳሰባችንም ከአመለካከታችንም ጋር የሚያያዝ ነው። ከዚያም ቀጥሎ ወደባህሪ ይመጣል፤ ይህ ግን የሚጀምረው ከአስተሳሰብ ነው። ይህ አስተሳሰብ ለቃላት፣ ለአነጋገር ቦታ ይሰጠዋል። ያ ንግግር ደግሞ ወደተግባር ሲተረጎም የሚደረገው ድርጊት ወይ ሰላማዊ ነው፤ አሊያም ደግሞ ኢ-ሰላማዊ ነው።

ስለዚህ የሰላም ትርጉም ብዙ ጊዜ ከውስጥ ሰላም ጋር የሚያያዝ ነው። የውጭ ሰላማችን በጣም ውስንነት አለው። ለምሳሌ የውጭ ሰላም ስንል ከሌሎች ጋር ያለንን ግንኙነት ሲሆን፣ ይህም የሚመነጨው ከውስጥ ሰላም ነው። ነገር ግን አንድ ሰው ገና ‹እንደምን አደርክ?› ሲል ምላሹ ‹ምን አገባህ!› ወይም ‹እንደምን አደርክ?› ሲባል፣ ምላሹ ‹እንደሰው› ወይም ‹እንደምን አደርክ?› ተብሎ ሲጠየቅ፣ ‹ተኝቼ› ብሎ ከመለሰ ያስደነግጣል። ነገር ግን ያ ሰው የውስጥ ሰላሙን ቢያገኝ ‹እግዚአብሔር ይመስገን› ወይም መልካም የሆነ ምላሽ ይሰጥ ነበር።

ስለዚህ ብዙ ጊዜ የውስጥ ሰላም ለውጪው ሰላም መሠረትም ወሳኝም ነው። የውስጥ ሰላም ሲጠናከር ለአገርም ሆነ ከውጭ ጋር ላለን ግንኙነት ትልቁን ሚና ይጫወታል። የውስጥ ሰላም ጥንካሬያችንና ኃይላችንም ስለሚሆን የውጪው ጉዳይ ሰላም እንዲሆን ያደርጋል። በውስጣችን ያለው መተሳሰር በጣም ከፍተኛ የሆነ ኃይል ይሰጣል። ስለዚህም የሰላም መሠረቱ የውስጥ እርካታ ብሎም የውስጥ አንድነት ነው። አንድነት ብዬ ስል አዕምሮ እና አካል ማለት ነው። ይህ የአዕምሮ እና የአካል መግባባት ሲኖር ውስጣዊ አንድነት ይኖራል።

**አዲስ ዘመን፡- መንግሥት ከሰሜኑ ጦርነት በፊት ሰላም እንዲኖር የአገር ሽማግሌዎችን ብሎም ታዋቂ ሰዎችንም በመላክ አበክሮ ሲሠራ ነበር፤ መንግሥት ለሰላም የነበረው ቁርጠኝነት ደቡብ አፍሪካ ላይ ለተደረሰው የሰላም ስምምነት ፋይዳ አለው ይላሉ?**

**ዶክተር ዮናስ፡-**የሰላም ጥናት መምህርም ተመራማሪም ብሎም በዚሁ ዘርፍ ተባባሪ ፕሮፌሰርም ሆኜ የሦስተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን በማማከር ላይ ስሠራ ሁሌ እንደማስተውለው እያንዳንዷ ወደሰላም የምታደርሰን እንቅስቃሴ ለአጠቃላይ ሰላማችን ትልቅ አስተዋጽኦ አላት። ሁሌም እንደምንለው መጥፎ ሰላም የለም። በዚህ ጉዳይ ለፓርላማ ጠቅላይ ሚኒስትራችን በሰጡት ምላሽና ማብራሪያ ላይ ‹የሰላም መጥፎ የጦርነት ጥሩ የለውም›› ያሉት ነገር በጣም ትክክል ነው። ምክንያቱም እርሳቸው እንዳሉት፤ ጥሩ ጦርነት የለም፤ ይልቁንም በጦርነት ብዙ ነገር እናጣለን እንጂ አናተርፍም።

ስለዚህ በደቡብ አፍሪካ የተከናወነው የሰላም ስምምነት የተመሠረተው በድርድር ነው። በድርድር ላይ የተደረገው ስምምነትና በተጨማሪም ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች የአፍሪካ ችግር በአፍሪካ መፍትሔ በሚል መርህ ላይ ተመስርቶ በጣም በምናከብራቸው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሰላም ጥናት እኛ በምናካሂደው ጣና ፎረም ቦርድ ሰብሳቢ የነበሩ የቀድሞ የናይጄሪያ ፕሬዚዳንት ኦሊሴንጉን አባሳንጆ ዋና አደራዳሪነት የሰላም ስምምነት ተፈርሟል። ሰላም ስምምነቱ እኛም አፍሪካውያን አንድ ላይ ስንተባበር የአፍሪካ አንድነት፣ ሰላምና ደህንነት ብሎም የአፍሪካ ልማት ለአፍሪካ ችግሮች ራሳችን ስንነሳ ትልቅ ተምሳሌታዊ የሆነ ስኬት ነው ማለት ይቻላል።

የመጣው ሰላም ዝም ብሎ ሰላም ብቻ አይደለም፤ አንደኛ አፍሪካውያን ማሰብ እንደሚችሉ አመላካች ነው። አፍሪካውያን ሁሌ እንዲህ እና እንዲያ አድርጉ እየተባለ የሚነገራቸውና የተባሉትን ብቻ የሚፈጽሙ ሳይሆን የራሳቸውን ችግር በራሳቸው መፍትሔ አምጪነት መፍታት የሚችሉ እንደሆነም ያሳየ ነው። አፍሪካ በዚህ መልኩ ያካሄደችው ተግባር ትልቅ ግብ ነው ብሎ ማስቀመጥ ይቻላል። ሁለተኛው ደግሞ በተለይ ለእኛ ለአገራዊ ምክክር ኮሚሽን እያንዳንዷ የሰላም እንቅስቃሴ ትልቅ ፋይዳ አላት። እኛ ድርድርን የምናየው እንደ አንድ የምክክር አካል አድርገን ነው። ምክክር ብዙ ቅርንጫፎች አሉት። ድርድር፣ ሽምግልና፣ አፈርሳታ፣ አውጫጪኝ፣ ሙግት፣ ክርክር እየተባሉ በስፋት ያሉ ናቸው፤ ድርድር ከእነዚህ አንዱ ነው። ስለዚህ ለምክክሩ ሒደትም ከፍተኛ ፋይዳ አለው።

ቢያንስ ቢያንስ ጦርነትን በገንዘብ ሲደግፉ የነበሩና ሰላም እንዳይኖር የሚፈልጉ አካላት አፍሪካውያን በተሳካ መንገድ የሰላም ስምምነት ማከናወን በመቻላቸው ‹ይህም አለ እንዴ!› ሊያሰኛቸው የሚበቃ መሆኑን መረዳት ችለናል። ቀደም ሲል በባሪያ ንግዱ፣ በቅኝ አገዛዙና በጦርነቱም ቢሆን ሲከፋፍሉን የቆዩ ቢሆኑም አሁን ግን በዚህ መንገድ መከፋፈል እንደማያስችላቸው እየተረዱ እንዲመጡም ያደረገ ስምምነት መሆን ችሏል።

እንዲያውም አሁን አሁን ከአፍሪካውያኑ ሰላም ተጠቃሚ መሆን የሚያስችላቸው ሁኔታ መኖሩን የሚያመላክት ነው ብዬ አስባለሁ፤ ለምሳሌ የእኛ በኢኮኖሚ ዝቅተኛ መሆን የተሻለ ፍሊጋ የሚያስኬደን ወዴት ነው ቢባል ወደአደጉት አገር ነውና በሰላም እጦት ከሚደርስብን ችግር የተነሳ ወደእነርሱ እንዳንሰደድ የእኛን ሰላም መሆን መደገፉ አዋጪ ነው የሚል አተያይ አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከሰላም ማትረፍ እንደሚቻል ተናግረዋል፤ ይሁንና ስምምነቱ ከተካሄደ በኋላ ከመጣው ሰላም በተቃራኒ የቆሙ አካላት ተስተውለዋልና ይህ ሰላም ስኬታማና ዘላቂነት እንዲኖረው ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

**ዶክተር ዮናስ፡-** እንደ አለመታደል ሆኖ እንጂ ገና ስንፈጠር በየትኛውም አገር ያለ የሰው ዘር ነጬም ሆነ ጥቁሩ ሰው በተፈጥሮ ሰላማዊ ነው። በብዙ አስተምህሮ ውስጥ እናያለን፤ የሚነገረው ሰው በአምላኩ አምሳል የተፈጠረ ነው ተብሎ ነው። አዳምና ሔዋን በኤደን ገነት ውስጥ በነበሩበት ጊዜ (አደምና ሐዋ) እርቃናቸውን ሆነው ሳለ አይተፋፈሩም ነበር። ከጊዜ ጋር ተያይዞ በመጣው ሒደት ሰው ወንድሙን ገድሎ በወንድሙ ደም ላይ መመላለስና ራሱን ከፍ ማድረግ እንዲሁም በወንድሙ ትከሻ ላይ ተንጠላጥሎ ወደስልጣን ማማ መፈናጠጥን ልማድ አድርጎ ቆይቷል። በዚህም አካሄድ ከሰላም ሳይሆን ከጦርነት አትራፊዎችን እናገኛለን።

በሌላ በኩል ደግሞ የጦር መሣሪያ ፋብሪካዎች አሉ፤ እነዚህ የጦር መሣሪያ ፋብሪካዎች ማትረፍ የሚችሉት እኛ ስንባላ ነው። በተመሳሳይ ደግሞ ውጭ አገር ሆነው ኢትዮጵያ ውስጥ ብሎም አፍሪካ ውስጥ የሚካሄደውን ነገር ከጉዳይ የማይቆጥሩም አሉ፤ እነርሱ የሚፈልጉት ምናልባትም ጦርነቱ የሚጠናከርበትን ሁኔታ ነው። ምክንያቱም ከጦርነት ማትረፍ ስለሚችሉ ነው። ጦርነት


ፎቶ፡- ፀሐይ ንጉሴ

ባለበት ቀጣና ሁሉ እነርሱ አትራፊነታቸውን እንጂ ለሰው ልጆች ሞት ምንም ያህል ርህራሔ የሌላቸው ናቸው። ከጦርነቱ የተነሳ ለሚደርሰው አካል መጉደልም ሆነ ከኢኮኖሚው መድቀቅ የተነሳ ለሚሰደደው ሕዝብ አዘኔታ የማያሳዩ ናቸው።

እነዚህ አካላት የሚያስቀድሙት የእነርሱን አትራፊ መሆኑንና ምቾት ነው። የእነርሱን ተደላድሎ መኖርን ብቻ ነው። እነዚህ አካላት ስለሌላው ስቃይም ሆነ መሰደድ በጭራሽ አይመለከተንም ብለው ራሳቸውን ያሳመኑ ናቸው።

በአጭሩ ለመናገር ለምሳሌ ብዙ ጊዜ የማንተማመንባቸው የምዕራባውያኑ ሚዲያ ከሰላም ስምምነቱ በኋላ የተፈጠረው ነገር 13 እና 15 ሺ ብር የነበረው የአንድ ኩንታል ጤፍ ዋጋ ወደ ስድስት እና ሰባት ሺ ወርዷል ሲሉ ዘግበዋል፤ ይህን ለሚሰማ ሰው በጣም ልብን የሚያሳርፍ ነው። ይህ መረጃ የተላለፈው በአሜሪካ ድምጽ ነው።፡ ታዲያ ይህን የመሰለ መልካም ዜና የሚሰማ ሰው ይህንን ሰላም አጥብቆ ይይዛል እንጂ እንዴትስ ነው በሰላም ስምምነት በተቃራኒው ለመቆም የሚፈልገው። ይልቁኑ ወገኔ ብሎ የሚያስበው ሰው ከመከራና ከግጭት ሲወጣ ማየት ያስደስት ይሆናል እንጂ ስለምንስ ነው መከራው እንዲቀጥል የሚመኘው የሚል ምልከታ አለኝ።

ነገር ግን እውነት ነው የግል ጥቅምን ለሚያስቀድሙ አካላት፣ ፍላጎትን ጦርነት ማድረግ በእነርሱ ዘንድ ይቻላል። የሰላማዊነት ዓይኖቻቸው እስከተጨፈኑ እና ለጦርነት ብቻ እስከተከፈቱ ድረስ እርግጥ ነው ለእነርሱ ዓይነቶቹ ይቻላል። የወንድሞቻችን፣ እህቶቻችን፣ እናቶቻችንና አባቶቻችን ጭንቀት አንዳች ሳያሳስበን የምናገኘውን ጥቅማጥቅም ብቻ ለምንመርጥ አካላት አዎ! በሰላም ተቃራኒ መቆም ይቻላል። በእነዚህ አካላት ዘንድ የሰላሙ ሁኔታ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ነው። ነገር ግን እርግጠኛ ሆኜ የምናገረው የፈጣሪ ፈቃድ እና የሕዝቡ የጸሎት ውጤት እንዲሁም የመከላከያ ሠራዊታችን ጥረትና የመንግሥት ቁርጠኝነት እስካለ ድረስ የሰላም ስምምነቱ መሬት የሚወርድ ይሆናል የሚል ሙሉ እምነት አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎ እንዳሉት ይህን ሰላም ወደመሬት በማውረድ እያንዳንዱ ሕዝብ ከሰላሙ ተጠቃሚ ማድረግ የሚቻለው እንዴት ነው?**

**ዶክተር ዮናስ፡-** ሕዝቡን እንዴት የሰላሙ ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል ያልሽው በጣም መሠረታዊ ጥያቄ ነው። በመጀመሪያ በአንድ እጅ ማጨብጨብ እንደማይቻል የታወቀ ነው። ሁሉም ለሰላሙ ዘብ መቆም አለበት። በተለይ ደግሞ ከማንም በላይ ሕዝቡ ከሰላሙ በተቃራኒ የቆሙ አካላትን በሰላማችን ላይ አትምጡብን ማለት አለበት። ይህ በብዙ ጥረት ያገኘነውን ሰላም ዳግም ማጣት አንፈልግም ሊሉ ይገባል። ከዚህ በፊት የተካሄደው ጸብና ግጭት አይደገም ማለትም ያስፈልጋል። በጠብና ግጭት ያተረፍነው ነገር ቢኖር የሰው ልጅ እልቂትን ብሎም በኢኮኖሚውም ቢሆን የበለጠ መንኮታኮትን ነው። እንዲሁም በማህበራዊ ሕይወትም ቢሆን እርስ በእርስ መገፋፋትን ነውና ከጦርነት አትራፊ የሆኑ አካላትን ገለል በሉልን ማለት ተገቢ ነው። ይህ የሰላም ስምምነት ወደመሬት ወርዶ ዘላቂ መሆን እንዲችል ዋናው የሕዝቡ ተነሳሽነት ነው። በትግራይ፣ በአማራ፣ በአፋር ብሎም በተቀረው የኢትዮጵያ ክፍል ያለው ሕዝብ ሰላሙ ዘላቂ እንዲሆን ድርሻው ከፍ ያለ ነው። ይህ ሕዝቡ ከመንግሥት ጎን ለጎን ለሰላሙ ቁርጠኝነቱን ማሳየት አለበት። ይህ እንዳልኩሽ አንዱ ለሰላሙ ዘላቂነት ወሳኙ የምለው ጉዳይ ነው።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ



ሁለተኛው ደግሞ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን በእርግጥ ሥራውን በአግባቡ በማከናወን ላይ ይገኛል። ኮሚሽኑ በቀጣይ ወደትግራይም የሚጓዝ ይሆናል። የኮሙኒኬሽንና ሚዲያ ክፍል ኃላፊ እንደመሆኔም ማውጣት የሚቀረን ስትራቴጂ ብቻ ነው። ዳግም ይህ ጦርነት እንዳይከሰት ምን እናደርግ? ይህንንስ ሰላም ከሕዝቡ ጋር በመሆን እንዴት ወደመሬት እናውርድ? ዳግም ይህ ጦርነት እንዳይከሰትስ ምን እናድርግ? ይህንን ሰላም እንዴት የእያንዳንዱ ሰው እንዲሆን እንዳርግ? በሚለው ዙሪያ ከሕዝቡ ጋር መመካከር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከላይ እንዳስቀመጡትም ከወራት በፊት ባደረግነው ቃለ ምልልስም ኮሚሽኑ በሰሜኑ ክፍል የተቀሰቀሰው ጦርነት እንዳበቃ ወደትግራይ ክልል ለማምራት ዕቅድ አለው፤ ወደዚያ የማምራታችሁ ሁኔታ በቅርቡ ይከናወናል ተብሎ ይጠበቃል?**

**ዶክተር ዮናስ፡-** በዚህ ጉዳይ በኮሚሽናችን እየተወያየን እንገኛለን። በእርግጥም ከዚህ በኋላ የምንወያየው ስለእሱ ጉዳይ ነው። በተለይ የሰላሙን ሁኔታ እንዴት እንደምናደርግና እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል በተለይ የሽግግር ሁኔታዎች ባልተስተካከሉበት ሁኔታ ምን መሆን አለበት የሚለውም አለና የተለያዩ ስትራቴጂዎችን መጠቀማችን የማይቀር ነው።

እኔም አስታውሳለሁ፤ ቃለ ምልልሱን ያደረግነው ከአራት ወራት በፊት ጦርነቱ እየካሄደ ባለበት ጊዜ ነበር። በእርግጥ ጦርነቱ እንኳ እየተካሄደ ባለበት ጊዜም ቢሆን ለሰላሙ ጉዳይ ላይ ታች ማለት የሚቻል ነው። በመሠረተ ሐሳቡ ደግሞ የሰላም ግንባታ ንግግሮች በዓለም አቀፍ ደረጃም ያሉ ልምዶች ናቸው። እኛም እንዲሁ ወደትግራይ ለመሄድ ስትራቴጂ እያወጣን እና እሱን እንዴት እንደምናደርግ እያመቻቸን እንገኛለን።

**አዲስ ዘመን፡-አንዳንዶች የፌዴራል መንግሥት እንዴት በአንድ ወቅት በአሸባሪነት ከተፈረጀው ሕወሓት ጋር ይስማማል ሲሉ ይደመጣሉ፤ መንግሥት ለሰላም ካለው ቁርጠኝነት የተነሳ ሰላምን ለማምጣት ይህን ማድረጉ እርስዎ እንዴት ያዩታል?**

**ዶክተር ዮናስ፡-** አንዳንዶች ‹‹የሚያደርጉትን አያውቁምና ፈጣሪ ይቅር ይበላቸው›› የሚለውን ሐሳብ መጠቀም እሻለሁ። ይህ በአንድ ወቅት ከነበረው መግለጫ በመነሳት በፓርላማ በአሸባሪነት ከተፈረጀ አካል ጋር ለሰላም ሲባል በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጦ መወያየትና ሲሳካ ደግሞ ወደስምምነት መምጣት የተጀመረው አሊያም የሚካሄደው ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ አይደለም። እንዲህ ዓይነቱን አካሄድ ሌሎች አገራትም አድርገውት አልፈዋል። በአንዳንዶቹ ዘንድ ኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ ጦርነቱ በአንድ በኩል እየተካሄደ ባለበት ውይይት ደግሞ በአንድ በኩል ሲካሄድ ነበር። እንዲህ ዓይነት በርካታ ማሳያዎችን መጥቀስ ይቻላልና እንዲህ ማድረጉ በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያ የመጀመሪያ እንዳልሆነች የሚያሳይ ነው። በመሆኑም ይህ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ እንዳሉት ለሰላም ሲባል የሚከፈል ዋጋ ነው።

ደግሞም የተደራዳሪዎቹ ቁርጠኝነት በተለይ አስቀድሞ አጀንዳውን የሚያስቀምጥ እና በጉዳዩ ዙሪያ እንነጋገር የሚለው አካል ምን ያህል ለሰላሙ የተጠማ እና ሰላምን አጥብቆ ፈላጊ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፤ ለምሳሌ በፌዴራል መንግሥት በኩል ብልጽግና ስለጉዳዩ ገና ከመነጋገሩ አስቀድሞ በመጀመሪያ አካባቢ ያለው ነገር ቢኖር በይቅርታ እንሻገር፤ በሰላም እንደመር ነበር።

ሰላሙንም ሆነ ብልጽግናውን አንፈልግም፤ በፍቅርም አንደመርም፤ የሚያዋጣን ጦርነት ነው፤ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ጭራሽ አናውቃትም፤ ሌላም ሌላም ለዚህ ጋዜጣ አንባቢ የማይመጥኑና አንባቢም ዘንድ መድረስ የሌለበት ነገር ሁሉ ሲነገር መቆየቱ የማይካድ ሐቅ ነው። ስለዚህ ከዚያ የተነሳ በሕግ የተወከለው፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ተቀባይነት ያለው፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ደግሞ ለዘመናት የራሱ ስልጣኔ ያለው ነው። እንግዲያውስ ይህ ለሰላም ግድ የሌለው አካል ስለሆነና ኢትዮጵያን የሚፈታተን በመሆኑ በሚል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በወቅቱ ሕወሓትን አሸባሪ ብሎ መፈረጁ ይታወቃል።

በዚህ ውስጥ አስቀድመውም ጠቅላይ ሚኒስትራችን እንዳሉት፤ ይህ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለ ልምድ ነውና አትደራደሩ ማለት አይቻልም። በጣም በርካታ ቦታ በተለይ በገዥ ፓርቲዎች አማካይነት ሰላም ባህል እንዲሆን እና በሰላማዊ መንገድ ወደሰላም መምጣት እንዲቻል ይሠራል። በመሆኑም ይህ አዲስ የመጣ ሒደት አለመሆኑና በሌሎችም አገሮች ሊካሄድ የሚችል መሆኑን ልብ ሊባል ይገባል።

የሰላም ፍልስፍና እንደሚለው ለሰላም መንገድ የለውም፤ ሰላም ራሱ መንገድ ነው። ስለዚህ ሰላም ራሱ መሄጃ መንገድ ነው፤ ሰላም መድረሻም መንገድ ነው። ስለዚህ ሰላም መሄጃም መድረሻም መንገድ ስለሆነ በጦርነት አሊያም በቅጣት ብቻ ሳይሆን በፍቅርም በመነጋገርም ሰላምን ማምጣት ይቻላል ብሎ ማመን የግድ ነው የሚሆነው። ስለዚህም አካሄዳቸውም ከዚህ የተነሳ ስለሆነ ሳይገባቸውና ሳያውቁ የሚተቹ አካላት ካሉ ከዚህ አንጻር መረዳት ቢችሉ መልካም ነው። የሰላሙ ድርድር አሁንም መቀጠል አለበት። አሁን ከድርድሩ በኋላ ወደሰላም ስምምነቱ ሲመጣ ከጦርነት የማያንስ ተግዳሮቶች ደግሞ ይጠብቁናል።

**አዲስ ዘመን፡- ወደሰላም ስምምነቱ ከተመጣ በኋላ ከጦርነት የማያንስ ተግዳሮት ደግሞ ሊጠብቀን እንደሚችል አንስተዋል፤ ከእነዚህ ውስጥ ምን ምን ዓይነት ተግዳሮቶች እንደሆኑ ቢጠቅሱልንና መፍትሔውንም ቢያመላክቱ?**

**ዶክተር ዮናስ፡-** ለምሳሌ ቀደም ሲል ሲዋጋ የነበረውን አዋጊና ተዋጊ ኃይልን ወደ አምራች ኃይል መቀየር አንዱ ነው። ዲስአርሚንግ፣ ዲሞብላይዚንግ ሪኢንቲግሬትግ (DDR) ወይም (ትጥቅ ማስፈታት፣ ማሰባሰብ እና እንደገና መቀላቀል) የሚባል ነው። ከዚያ በኋላ ትጥቅ ማስፈታት ነው። መሣሪያ ይወሰድ እንጂ አሁንም በጦርነት ማመን አለ። ስለዚህ በዚህ ዙሪያ በመጀመሪያ መነጋገርና ማሳመን ተገቢ ነው። በዚህ ዙሪያ አካሄዱን በአግባቡ ተነጋግረን በመስማማት ካደረግን በኋላ ያንን ትጥቅ የፈታውን አካል እንገደና ወደካምፕ ማስገባቱ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም እንዳልኩሽ ምንም እንኳ በእጅ ላይ ምንም ዓይነት የጦር መሣሪያ ባይኖርም አሁንም ድረስ በጦርነትና በጦርነት ብቻ የማመኑ አመለካከት ስለሚኖር ያንን አመለካከት በመነጋገር ከወዲሁ መፍታት መቻሉ ወሳኝ ነው።

ጦርነትን አማራጭ እንደሌለው መፍትሔ የሚያስብ አካል አለ፤ መሣሪያን ደግሞ ልክ እንደ ቀኙ እጁ የሚመለከት አለ። መሣሪያ ስለተወሰደባቸው ብቻ ከሰውነታቸው አንደኛውን አካል እንዳጡ የሚሰማቸው አካላት አሉ። መሣሪያ ስለተወሰደባቸው ብቻ ልክ እጅ እግራቸው እንደተቆረጠባቸው አድርገው የሚያስቡ ሰዎችም አሉ። ስነ ልቦናቸው ከመሣሪያ ጋር ስለተያያዘ የሚቸገሩ አካላት አሉ። ስለዚህ እነዚህን አካላት ሙሉ በሙሉ ነፃ አድርጎ ወደ ኅብረተሰቡ ከማቀላቀል በፊት አስቀድሜ እንደጠቀስኩልሽ ትጥቅ ማስፈታት፣ ማሰባሰብ እና እንደገና መቀላቀል የሚባል ነገር አለና እሱን መተግበር ነው። ስለዚህ ወደየመጡበት ከመመለሳቸው በፊት የአዕምሮ ተሃድሶ መደረግ መቻል አለበት ባይ ነኝ። እንዲሁም የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲያመጡ መደረግ አለበት።

እንደዛ የሚደረግ ካልሆነ ግን ይህ አካል ደም ሲፈስ አይቷል፤ በተመሳሳይ ደግሞ ደም አፍስሷል። በውስጡ እጅግ አስደንጋጭ እና አሰቃቂ ገጠመኝ (Trauma) አለ። ይህ የስነ ልቦና የስነ አዕምሮ ሐኪሞችን ማነጋገር ብሎም ማወያየትን ይጠይቃል። ከዚያ በኋላ ያለው ቁስል እንዲሽር ለተወሰነ ጊዜ ለምሳሌ በተለያዩ አገራት እንደሚደረገው ቢያንስ እስከ አምስትና ስድስት ወራት ያህል መቆየቱ መልካም ይሆናል፤ ይህ ከተደረገ በኋላ ወደየቤተሰቡ መሄድ ይቻላል ያልኩት ከጦርነቱ ባልተናነሰ የሰላሙም ሥራ ከባድ መሆኑን ለማሳየት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የሰላም ስምምነቱ ተፈረመ ተብሎ ከተነገረበት ጊዜ ጀምሮ በውጭ አገር የሚኖሩ ጽንፈኞች እንዲሁም ሌሎችም የውጭ ጣልቃ ገቦች እያስተጋቡ ያለው ከሰላም በተጻራሪ የሆኑ ድምጾችን ነው። ለእነዚህ አካላት የሚያስተላልፉት መልዕክት ይኖርዎት ይሆን?**

**ዶክተር ዮናስ፡-** እነዚህ በውጭ አገር ያሉ ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን አንዳንዶቹ የምናውቃቸው ናቸው። አንዳንዶቹ የቅርብ ጓደኞቻችን፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ተማሪዎቻችን፤ ገሚሶቹም የሥራ ባልደረቦቻችን ናቸው። ሁላችንም ወንድሞችም ሆንን እህቶች የኢትዮጵያ ብሎም የትግራይ ሕዝብ በከፈለው ግብር ጭምር የተማርን ነን። ስለዚህም ብንችልም ያለውን ሳይሰስት እና ከራሱ አስቀድሞ ያስተማረንን ቤተሰብ እንዲሁም ሕዝብ ዛሬ ላይ ሆነን ከመቼውም ጊዜ በላይ ልንረዳው ይገባል። ነገር ግን በጦርነቱ መከሰት በብዙ ሲሰቃይ የነበረን ሕዝብ ከወጣበት ስቃይ መልሶ እንዲገባ ማድረግ ከጤነኛ አዕምሮ የሚመነጭ ሐሳብ አለመሆኑ የሚታወቅ ነውና ከዚህ ድርጊት መቆጠቡ መልካም ነው ባይ ነኝ። እኛ የምንፈልገው ብቻ መተግበር አለበት ወይም እኛ የምንለው ብቻ መሆን አለበት ማለቱ አግባብ አይሆንም።

እኔ እስከሚገባኝ ድረስ የእነርሱ እንደዛ መሆን ለሕዝቡ ጥቅም ታስቦ አይደለም። ሕዝቡ ከእኛ ዓይነቱ ተማርን ከምንል አካላት የሚጠብቀው የተሻለን ነገር ነው፤ ሕዝብን አገለገልን ብለን መናገር የምንችለው በተማርነው ትምህርት ያስተማረንን ሕዝብ ስቃይ ስንቀንስ እና ቢቻል ደግሞ ጨርሶ ስናጠፋ ነው። የራሳችንን ኑሮ ብቻ ማስተካከሉና ማቆነጃጀቱ ፋይዳ የለውም፤ ቢያንስ ሕዝባችን በልቶ ስለማደሩም ሆነ ስለሰላሙ ግድ ሊለን ይገባል። መኪና ላይ መኪና ብንገዛ፣ በቤት ላይ ሌላ የተሻለ ቤት ለመግዛት ብንሯሯጥ እሱ ሁሉ የድንጋይ ቁልልም ሆነ የቆርቆሮ ጋጋታ ነው፤ ደግሞም ያልፋል። መልካም የሆነ ሥራ ግን ምን ጊዜም ቢሆን አያልፍም፤ ስለዚህም ከተግባራችን በኋላ ጥለን የምናልፈው የታሪክ ጠባሳ እስከወዲያኛው ተወቃሽ የሚያደርገን ይሆናልና እዚህ ላይ የተቻለንን መልካምነት ማድረግ ከሕሊና ጸጸትም የሚያድን ነው። የማይሽር የሒሊና ቁስል ትተን ማለፍ ግን ማንንም የሚጠቅም አይሆንም። ትውልድ አይድንበትም፤ ትውልድ አይማርበትም።

እኔ በአሁኑ ሰዓት በትህትና የምጠይቃቸው ቆም ብላችሁ ሕዝቡን ለማዳመጥ ሞክሩ ብዬ ነው። ሕዝቡ የሚለው ምንድን ነው? የትግራይ፣ የአፋር ብሎም የአማራ ሕዝብ ምንድን ነው የሚለው? አጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚለው ምንድን ነው? የሕዝቡ ኑሮ ምን ይመስላል የሚለውንም ለማስተዋል ሞክሩ። እውን ይህ ሕዝብ በሰላሙ ተጠቃሚ ነው ወይስ በሰላሙ ተጎጂ ነው? ይህን ለመረዳት ያላችሁን አዕምሮ በቅንነት ተጠቀሙና ቆም ብላችሁ ለማሰብ ሞክሩ እላለሁ። ይህን በማድረግም ከሕዝቡ ጎን ለመቆም ሞክሩ። ብትችሉ ከመንግሥትም ጎን ለመቆም ሞክሩ። አብሮነታችሁን በማጠናከር ሰላም ለአገራችን እንዲመጣ የራሳችሁን ሚና ተጫወቱ። በየሰው አገር ወንጀል ሠርቶ እስከመታሰር ድረስ ከመሄድ ይልቅ ያንን ቆም አድርገን ወደሰላም ፊታችንን መለስ እናድርግ እላለሁ። ወደሕሊናችን በተመለስን ጊዜ ሰላም ይመጣል። ከሰላም ደግሞ ሁላችንም አትራፊዎች ነን። በጦርነት ደግሞ ሁላችንም ተጎጂዎች ስለመሆናችን የተለየ ጥናት የሚያስፈልገው አይደለም። አጥፍቶ ከመጥፋት ይልቅ ሁላችንም አሸናፊዎች መሆን የምንችለው ለሰላም ተሰላፊ መሆን ስንችል ነውና ሰላምን በሰላማዊ መንገድ ማምጣትን ባህላዊ ጨዋታችን እናድርግ እላለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- አገራዊ የምክክር ኮሚሽን ከሰላም ስምምነቱ ተጠቃሚ የሚሆንበት መንገድ እንዴት ይገለጻል?**

**ዶክተር ዮናስ፡-** የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ዓላማ አገራችን ዘላቂ ሰላም፣ ዘላቂ ልማት እንዲሁም ዘላቂ እድገት እንዲገኝ ነው። እነዛ መሠረታዊ የሆኑ ችግሮቻችን በሰላማዊ መንገድ ተወያይተን የኢትዮጵያን ከፍታ ማየት ትልቁ ዓላማችንም ሕልማችንም ነው። ስለዚህም እያንዳንዷ የሰላም ጠብታ ለኮሚሽኑ ሥራ በጣም ጠቃሚ ናት። እኛ ሕዝብን በማወያየት ረገድ ከትግራይ ክልል በስተቀር ሁሉንም የኢትዮጵያ ክልል አዳርሰናል። በየክልሎቹ ደግሞ ቅርንጫፎቻችንን ለመክፈት እየተዘጋጀን እንገኛለን። ቀጥሎም ወደ ዋና ውይይታችን በመግባት በመጨረሻም ለዘመናት የነበሩትን ጦርነቶች እንዲገቱ ማድረግ ነው፤ በዚህም ወጣቶቻችን ተስፋ የሚያደርጉበት ሁኔታ በመፍጠር ወደልማትና ሰላማዊ ወደሆነው ኑሮ ሕዝቡን መመለስ ዋናው ዓላማችን ነው። ወደ ሰላማዊ መንገድ መምጣትን ባህል ማድረግ፣ የምንጥረው በኢትዮጵያን የፖለቲካ ባህል ሁሉም አሸናፊ መሆን እንችላለን ወደሚለው ከፍታ ለማድረስ ነው። ስለዚህ በዚህ አካሄድ በተደረገው ስምምነት ሁላችንም ተጠቃሚዎች ነን። ምክንያቱም ጦርነት እንቅፋት ነው። ለምሳሌ እኛ ትግራይ እንዳንሄድ ያደረገን እዚያ የነበረው ግጭት ነው። ለዚህም ነው ለሰላም የሚደረገው እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ኮሚሽኑን የሚጠቅም ነው ያልኩሽ።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ አንድ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን የኮሙኒኬሽንና ሚዲያ ክፍል ኃላፊ ለሕዝቡ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለዎት?**

**ዶክተር ዮናስ፡-** እንደ ኮሚሽኑ ያለን መልዕክት አንደኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለታላቁ የዓባይ ግድብ ከልቡ እንደተባበረ ሁሉ ለሰላሙም መስፈን ቁርጠኛ ሆኖ እንዲነሳሳ በአክብሮት መጠየቅ እፈልጋለሁ። ሁለተኛው አወያዩም ሆነ ተወያዩና አመቻቹም ከሕዝቡ ውስጥ ስለሆነ ይህም ራሱ በሕዝብ፣ ከሕዝብ፣ ለሕዝብ የተቋቋመ ኮሚሽን ስለሆነ የሕዝቡን ሁለንተናዊ ድጋፍ እንጠይቃለን። ሦስተኛው ምሁራንና የእናንተን የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትን ጨምሮ የሚዲያ ተቋማት በየቦታው ስላለው ሰላም በኢትዮጵያ ውስጥ ባህል በማድረጉ በኩል የየበኩላችሁን እንድትወጡ እንጠይቃለን። ልዩነቶቻችንን በንግግር መፍታትን ልማድ ማድረግ፤ ጦርነት ባህላዊ ጨዋታችን አይደለም። ባህላዊ ጨዋታችን መሆን ያለበት ሰላም ነው። ስለዚህ ይህን አስተሳሰብ በመገንባቱ ረገድ ሁላችንም የየራሳችንን ሚና እንድንወጣ በታላቅ ትህትና መጠየቅ እወዳለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ሰፊ ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር ዮናስ፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የድህረ ጦርነት ኢንቨስትመንት ማነቃቂያ ሥርዓቶች

አንተነህ ቸሬ

በ2014 ዓ.ም በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ከነበረው ጦርነት ጋር ተያይዞ የተፈጠሩ ክስተቶች ለኢንቨስትመንቱ ዘርፍ መሰናክል እንደነበሩ በተደጋጋሚ ተገልጿል። የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንም በበጀት ዓመቱ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትንና የተገኙ ውጤቶችን አስመልክቶ ይፋ ባደረገው መረጃ፤ በአገሪቱ የነበረው አለመረጋጋትና ጦርነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው የኢትዮጵያ ከአጎዋ መታገድ እና የዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ጫና በበጀት ዓመቱ ካጋጠሙ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ተግዳሮቶች መካከል እንደሚጠቀሱ አመልክቷል። ለአብነት ያህል በበጀት አመቱ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ረገድ ማሳካት የተቻለው የዕቅዱን 64 ነጥብ አራት በመቶ (ከሦስት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ዶላር በላይ) እንደሆነ የኮሚሽኑ መረጃ ያሳያል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽንም በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የተከሰተው የሰላምና ፀጥታ መደፍረስ በኢንቨስትመንት ተግባራትና በኮርፖሬሽኑ ዓመታዊ እቅድ አፈፃፀም ላይ ተፅዕኖ እንዳሳደረ ማስታወቁ የሚታወስ ነው። ሰላምና መረጋጋት ከኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው በመሆኑ በተለይ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የነበረው የሰላምና ፀጥታ ሁኔታ በኮርፖሬሽኑ የእቅድ አፈፃፀም ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል። የፀጥታ መደፍረሱ በኮርፖሬሽኑ ውስጥ የነበሩ ትልልቅ አምራች ድርጅቶችን ትልቅ ጫና ውስጥ አስገብቷቸዋል። አለመረጋጋቱን ተከትሎ የመጣው የውጭ መገናኛ ብዙኃን እንዲሁም የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘመቻና ጫና አምራች ድርጅቶች ተረጋግተው እንዳይሠሩና አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች በቀላሉ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይመጡ ተፅዕኖ አሳድሯል። በተጨማሪም ኤምባሲዎች ዜጎቻቸው ከኢትዮጵያ እንዲወጡ ከፍተኛ ግፊት ሲያደርጉ ስለነበር አምራቾች በጫና ውስጥ ሆነው ለመሥራት የተገደዱበት ዓመት ነበር።

በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚሠሩና ምርቶቻቸውን ለዓለም አቀፍ ገበያዎች የሚያቀርቡ ኩባንያዎች ምርቶቻቸውን በረጅም ጊዜ የግዥ ውል ለገዢዎች ስለሚያቀርቡ ምርቶቻቸውን በሌሎች አገራት ወደሚገኙ ቅርንጫፍ ማምረቻዎች እንዲያዞሩ ጫናዎች ነበሩባቸው፤ ገዢዎችም ይሰርዙባቸው ነበር። በበጀት ዓመቱ አገራዊ የሕልውና ማስከበር ዘመቻ ስለነበር፣ አጠቃላይ የመንግሥት እንቅስቃሴ ቅኝት በሕግና ሰላም ማስከበር ተግባራት ላይ ያተኮረ ስለነበር፣ በልማት/ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ላይ ተፅዕኖ ነበረው። በኢንቨስትመንት ተቋማት ላይ የደረሰው ጉዳት የምርት አገልግሎትና አቅርቦት መቋረጥ፣ የምርት ሽያጭ ገቢ መቀነስ፣ የሥነ ልቦና ጫናዎችንና ሌሎች ችግሮችን አስከትሏል። ተጨማሪ ኢንቨስትመንት ወደ ኢትዮጵያ እንዳይመጣ እንቅፋት ሆኖ መቆየቱም ይታወቃል።

የኢንቨስትመንት ዘርፉ እንዲቀዛቀዝ ምክንያት ለነበረው የሰላም መደፍረስ መፍትሄ ይሆናል የተባለውና በቅርቡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሥት እና በሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) መካከል የተፈረመው የሰላም ስምምነት ለኢንቨስትመንት ዘርፉ መነቃቃትና ማንሰራራት ትልቅ ተስፋ ተጥሎበታል። የሰላም ስምምነቱ በተለያዩ ጫናዎች ሳቢያ ተቋርጠው የነበሩ የማምረት ሥራዎች እንዲጀመሩ፣ ተቀዛቅዘው የነበሩ ምርቶችን ለውጭ ገበያ የማቅረብ ሥራዎች እንዲያንሰራሩ እና አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች ወደ አገሪቱ እንዲመጡ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ተብሎ ይጠበቃል።

የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ የተቀዛቀዘው የኢንቨስትመንት ዘርፍ እንዲነቃቃ ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ የኢንቨስትመንት ማነቃቂያ አሠራር መተግበር እንደሚያስፈልግ የምጣኔ ሀብት ጥናት ባለሙያዎች ያስረዳሉ።

በጂግጂጋ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህር እና የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ጥናትና ምርምር ዘርፍ ኃላፊ ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ ግርማ፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በአገሪቱ የተፈጠሩት የሰላም መደፍረሶች የኢንቨስትመንት ፍሰቱ እንዲቀንስ ማድረጋቸውን ጠቁመው፤ የሰላም ስምምነቱ ለኢንቨስትመንትና ለሌሎች ዘርፎች ያመጣውን ተስፋ ገቢራዊ ለማድረግ ቁርጠኛ መሆን እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት በጦርነቱ ምክንያት የተዳከመውን የኢንቨስትመንት ዘርፍ ለማነቃቃት ሕዝብን ያሳተፈ እና የውጭ ፋይናንስ ድጋፍን ያማከለ አሠራር መተግበር ይገባል። የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት (Foreign Direct Investment) ሀብት ለመፍጠር ካለው ሚና በተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ምንጭም ሆኖ ስለሚያገለግል የተቀዛቀዘውን የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ዳግም በማነቃቃት የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግም ያስፈልጋል። በጦርነቱ ምክንያት የተፈጠረውን የኢንቨስትመንት መቀዛቀዝ ከችግርነቱ ባሻገር አገር በቀል አምራቾችን ለማነቃቃት እንደጥሩ አጋጣሚ መጠቀምም ይቻላል። የኢንቨስትመንት ማነቃቂያ እቅዶችም የአገር ውስጥ የማምረት አቅምን በሚያጠናክር መልኩ መታቀድ ይኖርባቸዋል። ከዚህ በተጨማሪም በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገራት የሚገኙ የገንዘብና የእውቀት አቅም ያላቸውን የማኅበረሰብ ክፍሎችን ማሳተፍ እንደሚገባም ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ ይገልፃሉ።

> **በኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሥት እና በሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) መካከል የተፈረመው የሰላም ስምምነት ለኢንቨስትመንት ዘርፉ መነቃቃትና ማንሰራራት ትልቅ ተስፋ ተጥሎበታል**

«የድህረ ጦርነት ምጣኔ ሀብት ግንባታ ራሱን የቻለ ስትራቴጂ ያስፈልገዋል» የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ፤ «የድህረ ጦርነት የምጣኔ ሀብት ግንባታ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ይፈልጋል። የውጭ ፋይናንስ ምንጭ አማራጮችን ማስፋትን ይጠይቃል። ለዚህ ደግሞ በጠንካራ የዲፕሎማሲ ሥራ በመታገዝ ለጋሽ አገራትንና ተቋማትን ማሳመን እጅግ አስፈላጊ ነው» ይላሉ።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የአውሮፓን ምጣኔ ሀብት ለማነቃቃት የተተገበረውን «የማርሻል እቅድ» (Marshall Plan) በምሳሌነት የሚጠቅሱት ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ፤ ኢትዮጵያም ከነባራዊ ሁኔታዎቿ ጋር የሚጣጣሙ መሰል እቅዶችን በመተግበር የኢንቨስትመንት ዘርፉንም ሆነ አጠቃላይ ምጣኔ ሀብቱን ማነቃቃት እንደሚገባ ያስረዳሉ።

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህርና በ«ፍሮንቲየርአይ (Frontieri)» ጥናትና አማካሪ ድርጅት ከፍተኛ ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር ሞላ አለማየሁም መንግሥት የተዳከመውን የኢንቨስትመንት ዘርፍ ለማነቃቃት በልዩ ትኩረት መሥራት እንዳለበት ይመክራሉ። እርሳቸው እንደሚሉት፤ የታክስ እፎይታ መስጠትን ጨምሮ፣ ታክስ የመቀነስ፣ የብድር አቅርቦትን የማፋጠን አሠራሮችን በመተግበር የኢንቨስትመንት ዘርፉን ማነቃቃት ይገባል። ለአገር እድገት ወሳኝ ናቸው ለሚባሉ ዘርፎች ብድርና የውጭ ምንዛሬ ቅድሚያ መስጠትም ያስፈልጋል። ከፍተኛ የፕሮሞሽን ሥራ በመሥራት በአገሪቱ ሰላም ስለመስፈኑና ከፍተኛ የኢንቨስትመንት አቅም እንዳላት የማስተዋወቅ ሥራን በላቀ ትኩረት ማከናወን ያስፈልጋል። «ከሁሉም በላይ መተማመንን መፍጠር ያስፈልጋል» ይላሉ።

በድህረ ጦርነት ኢኮኖሚ ግንባታ ሂደት ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገቡ ጉዳዮች መካከል አንዱ ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ሊደረግ የሚገባው ድጋፍ እንደሆነ ባለሙያዎቹ ይናገራሉ። ዛሬ በምጣኔ ሀብታቸውና በፖለቲካ ተፅዕኗቸው የዓለም ኃያላን የሆኑት አገራት የአገር ውስጥ ባለሀብቶቻቸውን በመደገፍ ረገድ ትልቅ ተሞክሮ አላቸው። እንዲያውም ለአሁኑ የምጣኔ ሀብት ኃያልነታቸው መሠረት የሆናቸው ከውጭ ጥገኛነት ያላቀቃቸው የአምራችነት አቅማቸው ማደግ እንደሆነ ይታወቃል።

ኢትዮጵያውያን የአገር ውስጥ ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ዘርፍ ያላቸው ተሳትፎና ድርሻ በየጊዜው እየተሻሻለ እንደመጣ ባይካድም በቂ የሚባል ግን አይደለም። የአገር ውስጥ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ተሳትፎና ድርሻ እንዲሁም ተወዳዳሪነት ላቅ ያለ እንዳይሆን የሚጠቀሱት ምክንያቶች ዓይነተ ብዙ ናቸው።

ኢትዮጵያ ዘላቂ የምጣኔ ሀብት እንድታስመዘግብ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍና ተወዳዳሪ ማድረግ ይገባል። «የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ» እንዲሉ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት። የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን የመደገፍና ተወዳዳሪ የማድረግ ጉዳይ በምጣኔ ሀብት ትብብርና በእርዳታ ስም የሚደረግን የሀብታም አገራትንና ተቋሞቻቸውን ጣልቃ ገብነት በማስቀረት ሉዓላዊነትን እስከማስከበር ድረስ የዘለቀ ትርጉምና ፋይዳ አለው።

አምራችነቱን ያላሳደገ እና ፍላጎቱንና አቅርቦቱን በራሱ የማምረት አቅም ላይ ያልመሰረተ ምጣኔ ሀብት፣ ዘላቂ እድገትን ሊያስመዘግብ አይችልም። የአምራችነት አቅምን ለማሳደግና ፍላጎትን በማሟላት ከንግድ ሚዛን ጉድለትም ሆነ ጉድለቱ ከሚያስከትላቸው ምጣኔ ሀብት ዘለል ጫናዎች ለመላቀቅ አገራዊ አምራችነትን ማሳደግ ያስፈልጋል። አገራዊ የማምረት አቅምን በማሳደግ ምጣኔ ሀብታዊ እድገትን ዘላቂና አስተማማኝ ለማድረግ ደግሞ ሁነኛው መፍትሄ ደግሞ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን በመደገፍ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴው ዋነኛ ተዋንያን እንዲሆኑ ማድረግ ነው።

የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን የመደገፍ ጥረት በብዙ መልኮች ሊገለፅ ይችላል። የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን የሚያበረታቱ ምቹ የኢንቨስትመንት ፖሊሲዎችን በመቅረፅ፣ ፋይናንስን ጨምሮ ግብዓቶችን በማቅረብ፣ የመሠረተ ልማት አቅርቦትን በማሟላት እንዲሁም ቢሮክራሲያዊ የአሠራር ውጣ ውረዶችን በማቃለል ለባለሀብቶቹ ድጋፍ ማድረግ ይቻላል።

ዶክተር ሞላ የድህረ ጦርነት ኢንቨስትመንት ማነቃቂያ በይበልጥ የሚመለከተው የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን ነው» ይላሉ። እርሳቸው እንደሚሉት፣ የውጭ ባለሀብቶች ካላቸው የገንዘብ አቅም አንፃርም ሆነ ከሌሎች ነባራዊ ሁኔታዎች አንፃር ልዩ ትኩረቱና ድጋፉ መሰጠት ያለበት ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ነው። የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ ጥያቄ ሊነሳበት የማይገባ ጉዳይ እንደሆነና ተጨባጭ ምጣኔ ሀብታዊ ለውጥ እንደሚያመጣ የሚያስረዱት ዶክተር ሞላ፤ ባለሀብቶቹ ምርቶችንና አገልግሎቶችን በማቅረብ ከሚኖራቸው ሚና ባሻገር ለዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ ገቢ ምርቶችን በመተካት እና የወጪ ንግድን በመጨመር ትልቅ አስተዋፅዖ ስለሚኖራቸው ይህን ሚናቸውን የበለጠ እንዲያሳድጉ በመንግሥት ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ያስረዳሉ።

ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ፣ መንግሥት ቢሮክራሲያዊ የአሠራር ውጣ ውረዶችን በማቃለል ረገድ ትልቅ ሚና ሊኖረው እንደሚገባ ይናገራሉ። «መንግሥት አሰልቺ የሆኑ የአሠራር ሰንሰለቶችን በማሳጠርና አገልግሎትን በማቀላጠፍ እንዲሁም የንብረት ጥበቃ በማድረግ ለባለሀብቶቹ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል። በተጨማሪም ባለሀብቶቹ በኢንቨስትመንት ላይ የሚኖራቸው ተሳትፎ ዘላቂ እንዲሆን መንግሥት የኃይል አቅርቦትን፣ የመንገድና የሎጂስቲክስ አገልግሎቶችን ጨምሮ ለሌሎች የመሠረተ ልማት ችግሮችም መፍትሄዎችን ማበጀት ይጠበቅበታል። የውጭ ምንዛሬን በፍትሐዊነት ማቅረብም የመንግሥት ኃላፊነት ነው» ይላሉ።

ሰላምና መረጋጋት በሌለበት አገር የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴና እድገት ፈፅሞ የሚታሰብ አይደለም። የኢንቨስትመንት ሥራ ሰላም ይፈልጋል። ግጭትና ጦርነት ያለባቸው አካባቢዎች አዳዲስ የኢንቨስትመንት ዕድሎችን ማግኘት ይቅርና ቀደም ሲል በአካባቢዎቹ የነበሩ የኢንቨስትመንት መዳረሻዎችና ተቋማትም በነበሩበት የመቀጠል ዕድላቸው እጅግ ዝቅተኛ ይሆናል። እንኳን በተግባር የሚታይ የሰላም እጦት፣ ተጨባጭ ማስረጃ የሌለው ወሬም ኢንቨስትመንትን ያስደነግጣል። ለዚህም ነው ሰላም የኢንቨስትመንት መተንፈሻ ነው የሚባለው።

ኢንቨስተሮች የሰላም አየር በማይተነፍሱ አካባቢዎች ለመሰማራት ፍላጎት አያሳዩም። በእነዚህ አካባቢዎች ቀደም ሲል በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ተሰማርተው የነበሩ ባለሀብቶችም ሥራቸውን ለማቋረጥ ይገደዳሉ። የሰላም መደፍረስ የኢንቨስትመንት ተግባራትን በሚያሳልጡ መሠረተ ልማቶች ላይ ጉዳት እንዲደርስ ስለሚያደርግ የኢንቨስትመንት ተግባራትን በፍጥነት ለማከናወን የሚደረገውን ጥረት እንዲጓተት በማድረግ በጥቅል ምጣኔ ሀብታዊ እድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳርፋል።

ከዚህ በተጨማሪ የሰላምና ፀጥታ አለመኖር በኢንቨስትመንት ላይ ሊሰማራ የሚገባውን አምራች የሰው ኃይል ከኢንቨስትመንት በማራቅ የዘርፉ እድገት ፈጣን እንዳይሆን ያደርገዋል። ይህም የምርትና አገልግሎት ተግባራትን ፍጥነትና ጥራት በማዳከም ዝቅተኛ የምጣኔ ሀብት እድገት እንዲመዘገብ ምክንያት ይሆናል።

በአጠቃላይ፤ የሰላም መስፈን ለኢንቨስትመንት ማደግ የመጀመሪያውና ዋናው ቅድመ ሁኔታ ነው። ያለሰላም የሚታሰብም ሆነ የሚከናወን የኢንቨስትመንት ተግባር የለም። ሰላም ያልሰፈነባቸው አካባቢዎች፣ ቀደም ሲል የነበራቸውን ኢንቨስትመንት የተነጠቁና ተጨማሪ የኢንቨስትመንት ዕድሎችንም የማያገኙ እንደሆኑ ከዓለም ዙሪያ ያሉ በርካታ ነባራዊ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል። የሰላም መስፈን ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የላቀ ሚና እንደሚጫወት ሁሉ ኢንቨስትመንትም ሰላምን ለማስፈን ቀላል የማይባል አስተዋፅኦ እንዳለው ይገለፃል።

ሰላም ከኢንቨስትመንት ጋር ምን ዓይነት ቁርኝት እንዳለው ኢትዮጵያ ጥሩ ምስክር መሆን ከሚችሉ አገራት መካከል እንደምትመደብ አያጠራጥርም። በተለይ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የተከሰቱ አለመረጋጋቶች በኢንቨስትመንት ተቋማት ላይ ጉዳት አድርሰዋል።

በቅርቡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሥት እና በሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) መካከል የተፈረመው የሰላም ስምምነት ለኢንቨስትመንት ዘርፉ መነቃቃትና ማንሰራራት ትልቅ ተስፋ ተጥሎበታል። ይህ የሰላም ስምምነት የታሰበውን ውጤት እንዲያስገኝ ለሰላም ስምምነቱ ገቢራዊነት ቁርጠኛ ከመሆን በተጨማሪ፣ ለኢንቨስትመንት ዘርፉ መነቃቃትና ማንሰራራት ዋስትና ሊሆኑ የሚችሉ የድህረ ጦርነት የኢንቨስትመንት ማቃቂያ ስትራቴጂዎችን ማዘጋጀትና በብቃት መተግበር ይገባል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ጎሜ

# በህልም የተጻፈ ደብዳቤ - «እኛም ተኩስን ባል አሳገባን»

ሙሉቀን ታደገ

ይድረስ ጠላቴም፤ ወዳጄም ለነበርከው «ሞረሽ»፤ ዛሬ የጻፍኩልህ ደብዳቤ በህልሜ ከአንድ ፈላስፋ ጋር ስለአንተ እና ስለቤተሰቦቻችን ያወራነውን ነው። አንተ ማን ነህ? ካልከኝ የእኔም ስም ሞረሽ ነው።

ማድረግ የማይችሉትን አደርገዋለሁ እያሉ ለሰዎች ተስፋ መስጠት ከባድ ደዌ መሆኑን በህልሜ ያወራሁት ፈላስፋ ነገረኝ። እውነቱን ነው! ሞረሽ ወንድሜ አንተ እና እኔም መርዝ ወጊው ሃኪም እና ምስር የገቡልንን ቃል መሰረት አድርገን ለዓመታት በማይጨበጥ ተስፋ ውስጥ ተዘፈቅን፤ ተቀዝፎ በማያልቅ የተስፋ ውቂያኖስ ውስጥ ስንዋኝ ኖርን። በከባድ የተስፋ ደዌም ተበላን። እኛ በተስፋ ደዌ መበላታችን ሳያንስ ለሰፈራችን ሰዎችም ሊተገበር የማይችል የተስፋ ቃል እየገባን የተስፋ ደዌ ታማሚ አደረግናቸው።

የተገባልንን ቃል አምነን እና ተስፋ አድርገን መርዝ ወጊው ሃኪም እና ምስር የሚሰጡንን ትዕዛዝ እየተቀበልን ወንድም እና እህቶቻችንን እንዲሁም እናታችንን ለግማሽ ምዕተ ዓመት ያህል ከጀርባቸው ስንወጋ ኖርን ። በተላላኪነትም ወደር የማይገኝልን ሎሌዎች ነበርን ።

እናታችን አንተንም ሆነ እኔን ያለመሰልቸት ጡት አጥብታ ከማሳደጓ ባሻገር እንደ ልጅ ምንም ሳይጎድልብን ተንከባክባ እንዳሳደገችን ታውቃለህ! ይሁን እንጂ የምስርን እና የመርዝ ወጊውን ሃኪም ምክር ሰምተን ይሁዳ ከፈጸመው ክህደት ቢበልጥ እንጂ የማያንስ ክህደት በእናታችን ላይ ፈጸም። መሬት ላይ አሉ የተባሉ በርካታ ግፎችንም ፈጸምንባት ።

በተለይ እኔ ያወቅኩኝ እና ከእኔ በላይ ጠንካራ የሌለ መስሎኝ መላ ቤተሰቤን ወጋሁ ፡ ፡ ጠብቼ ያደኩበትን የእናቴን ጡት ለመቁረጥ ያለ የሌለኝን ሃይል እና ዘዴ ተጠቀምኩ። ወንድሞቼ እና እህቶቼ ግን የእናታቸው ጡት እዳይቆረጥ እጅ ለእጅ ተያያዙ። የተሰጠኝን ተልዕኮ አንዱንም ሳልፈጽም እንደዱቄት በተኑኝ ።

መርፌ ወጊው ሃኪም እና ምስር የቱንም ያህል ቢረዱኝ እንኳን የታሰበውን የእናታችን ጡት መቁረጥ ሳልችል ቀረሁ ። የነበረኝ ሃይል ሙሉ በሙሉ በወንድሞቼ ጡጫ እንዳይሆን ሆነ ።

ጠላቴም ወዳጄም የነበርከው ሞረሽ አሁንም «እኛም ተኩለን ባል አላገባን! » አለች ዝንጀሮ የሚለውን አባባል ደግሜ ላስታውስህ እወዳለሁ ። ምክንያቱም እኔም የቱንም ያህል ከመርፌ ወጊው ሃኪም እና ምስር የተለያዩ ድጋፎች እየተደረገልኝ ብሰራም እንኳን ማንም ከወንድሞቼ ጡጫ ሊያስጥለኝ አልቻለም። የተረፈኝ ውርደት ብቻ ነው ።

ውርደት ስል ፈላስፋው የነገረኝ አንድ ነገር ትዝ አለኝ ። በእርግጥ አንተ የፈላስፋም ሆነ የአወቂ ንግግር አይገባህም ። ምናልባት ከገባህ ግን ፈላስፋው በተደጋጋሚ ከሚለው አንድ አባባል ልንገርህ በሚል እንጂ። «የትህትና ፍሬዋ ፍቅር ነው ። የትዕቢዕት ግን ፍሬዋ ጥላቻ እና ውርደት ነው።» እኔም በጥላቻና በትዕቢት ታውሬ ቤተሰቦቼን ላጠፋ ተነሳሁ። ግን ምን አገኘሁ! ውርደት ብቻ።

እናም! ሞረሽ ወንድሜ አሁኑኑ በጊዜ ከእኔ ስህተት ተምረህ ለፍቅር እና ለትህትና ቦታ ስጥ። መሬት ከስህተታቸው የማይማሩ ግብዞችን የምትቀጣ ፍርድ ቤት ስትሆን ፤ ከስህተታቸው ለሚማሩት ደግሞ የንስሃ ስፍራ መሆኗንም በደንብ ልትገነዘብ ይገባል ።

> **መሬት ከስህተታቸው የማይማሩ ግብዞችን የምትቀጣ ፍርድ ቤት ስትሆን፤ ከስህተታቸው ለሚማሩት ደግሞ የንስሃ ስፍራ መሆኗንም በደንብ ልትገነዘብ ይገባል**

ሞረሽ ወንድሜ፣ አሁንም «እኛም ተኩለን ባል አላገባን» አለች ዝንጀሮ የሚለውን አባባል ደግሜ እነግርሃለሁ። ከ80 ዓመታት በፊት ለምጣሞች የእናታችንን ቤት በማን አለብኝነት በወረሩበት ጊዜ አባቴ የለምጣሞች ፓስታ ቀቃይ ሆኖ ተቀጠረ። ከፓስታ መቀቀሉ ጎን ለጎን የባንዳነት ስራ ይሰራ ነበር። በወቅቱ የነበሩ የአባቶችን ወንድም እና እህቶች ለምጣሞችን አይቀጡ ቅጣት ቀጥተው ከእናታቸው ቤት አባረሯቸው። አባቴም ባንዳ የሚለውን ስሙን ብቻ ይዞ ቀረ። ይህን ተከትሎ በአጉል ተስፋ ተደልሎ የእኛን እናት መንካት ትርፉ ውርደት መሆኑን አባቴ በአንክሮ ነገሮኝ ነበር።

ነገር ግን ሞኝ በራሱ ብልህ ከሰው ይማራል ሆኖብኝ አባቴ የነገረኝን ምክር አልሰማ ብዬና ምስርን እና መርዝ ወጊውን ሃኪም ተማምኜ ራሴን እንደ ጉንዳን እናታችንን እና ቤተሰቦቻችን እንደ ትል ቆጥሬ ተዋጋኋቸው። ዳሩ ምን ይሆናል? እኔ የትል ያህል ጥንካሬ እንዳለኝ የተረዳነው ቆይቼ ነው ።

ጨዋ የሆነ ሰው ተሹሞ ከፍ ክፍ ያለ እንደሆነ ትሁት ይሆናል፤ አይታበይም ። ባለጌ ግን የተሾመ እንደሆነ ይታበያል ። በትዕቢት ታውሮም ግብዝ ይሆናል። ይህ አንደበቱ የማይጠግበው በህልሜ ያገኘሁት የፈላስፈው ቃል ነው ።

እኔም በስልጣን ላይ በነበርኩበት ጊዜ ምስር እና መርዝ ወጊውን ሃኪም በሚመሩኝ የክፋት መንገድ እየተጓዝኩ በትዕቢት ታውሬ ታበይኩ። የእናቴ እና የወንድሞቼን እንዲሁም እህቶቼን ጠባቂ በሆነው «ቅራት» ላይ ግፍ ፈጸምኩ። ይህ የሰራሁት ግፍ ይሔው ዛሬ ዋጋ እያስከፈለኝ ነው። እናም ሞረሽ አንተ ግን ገና ሳትሾም ግብዝነት አጥቅቶህ ለምን እንኳን እንደምትታዘዝ ሳታውቀው ከቆላ ከደጋ ስትንገላጀጅ እንኳንስ እናታችንን ይቀርና ተልዕኮ የሰጡህን እና የጥፋት አጋር ወንድምህ እኔንም እጅ እጅ ብለውኛል።

የሚገርመው ደግሞ አንተና መሰል ወንድሞችህ ግን በማን እንድምትመሩ እና ማን ተልዕኮ እንደሚሰጣችሁ እንዲሁም ዓላማችሁ ግልጽ አይደለም። እኔ እኮ በአንድ ዕዝ ሰንሰለት የምመራ፤ ትልዕኮዬንም ጠንቅቄ የማውቅ እና በእኛ ሰፈር ያሉትን ሰዎች ሙሉ በሙሉ ደጋፊ ማድረግ የቻልኩ ነበርኩ። እናንተ ግን በእኛ ልክ እንኳን አይደላችሁም ። ጭራሽ ተልዕኮ የሚሰጣችሁንም አካል ከሁለት እርምጃ በኋላ የምትረሱ ክንቱዎች መሆናችሁን ሰማሁ ።

ወንድሜ ሞረሽ እመነኝ! ምስርን ሆነ መርዝ ወጊውን ሃኪም እና ምስር የሚነግሩህ የተስፋ ቃል አንዱንም በፍጹም አትቀበላቸውም። እነሱ የማይጨበጥ ተስፋን ተጠቅመው የሚሰሩብንን ግፍ በአንድ የሮበርት ሙጋቤ ሁነኛ አባባል ላሳይህ ። ከአውሮፓ አንድ ነጭ ወደ አፍሪካ ከመጣ የውጪ ዜጋ ጎብኚ ይባላል። ከአፍሪካ አንድ አፍሪካዊ ወደ አውሮፓ ከሄደ ግን ህገ ወጥ ስደተኛ ይባላል። በቡድን ነጮች ወደ አፍሪካ ከመጡ ቱሪስት ይባላሉ። በብዛት አፍሪካውያን ወደ አውሮፓ ከሄዱ ደግሞ ረፍዩጂስ (ስደተኞች) ይባላሉ። ነጮች አፍሪካ ውስጥ መጥተው የአፍሪካውያን አሰሪ ይሆናሉ። አፍሪካውያን አውሮፓ ሄደውም የነጮች ሰራተኛ ነው የሚሆኑት። በቃ! እነሱ እንዲህ ናቸው።

ፈላስፋው እንዲህ ይላል... «ብልህ እና አስተዋይ የሆነ ሰው ውሸታም ሰው ቢወደው አይደሰትም። ምክንያቱም እወድሃለው የሚለው ሰው ውሸቱን እንደሆነ ስለሚረዳ።» እኔ እና አንተ ግን ጥበብ እና ማስተዋል ጎድሎን ውሸታሙ መርዝ ወጊ ሃኪም እና ምስር የነገሩንን ውሸት አምነን ተቀበልን። በቤተሰባችንም የሰው ልጅ ይሰራዋል የማይባል ግፍ ፈጸምን።

አሁን ላይ አንድ እንድትገነዘብልኝ የምፈለገው ነገር አለ። ይህም በእኔ እና በአንተ ሰበብ የተጎዱ ቤሰቦቻችንን ስነልቦና ለመጠገን መስራት እንዳለብን ነው። እስከመቼ ላልተገባ ሹመት እና ስልጣን በራሳችን ቤተሰብ ላይ ቁማር እንቆምራለን ? የውሸታሞች እኩይ ተግባር ማስፈጸሚያስ እንሆናለን ?

ወንድሜ ሞረሽ፣ በህልሜ ያገኘሁት ፈላስፋ በተደጋጋሚ ያሏትን አንድ አባባል ልንገርህ ፤ የነፍስ መከራዋ አለም እና ሹመትን መሻት ነው። ሹመትን በማይገባ መልኩ የሿት እንደሆነ ቅናትን ታመጣለች። ቅናት ሃሰትን ትወልዳለች፤ ሐሰት ሃሜትን ትወልዳለች ። ሐሜት ጥልን ትወልዳለች ። ጥል ግፍን ይወልዳል ። ግፍ ግድያን ይወዳል። መግደልም ሌላ መግደልን ይወልድና እልቂትን ይፈጥራል ።

ሹመትን በተገቢው መንገድ ያሿት እንደሆነ ግን ፍቅርን ትወልዳለች፤ ፍቅር ደግሞ ስምምነትን፣ መስጠትን እውነት መናገርን ትወልዳለች። የሹመት አፈላለግ እንዲዚህ የሆነ እንደሆነ ህግ ትጸናለች። ዓለምም ትታነጻለች።

እኔ እና አንተ ግን ሹመትን በማይገባ መልኩ ስንሻት ኖረናል። ይህ ደግሞ እኔ እና አንተን ጨምሮ በቤተሰቦቻችን ላይ አሰቃቂ ዕልቂትን አመጣች። ስለሆነም ሹመትን በተገቢው መልኩ በመሻት የቤታችንን መሰረት እናጽና!

የአንድ ዓመት ራዕይ ባለቤቶች አበባን አሳደጉ፤ የአስር ዓመታት የራዕይ ባለቤቶች ዛፎችን አሳደጉ፤ የዘላለም ራዕይ ባለቤቶች ደግሞ ሰዎችን ያሳድጋሉ። ይህ ምርጡ እና ተወዳጁ የሩቅ ምስራቅ ፈላስፎች አባባል ነው። ስለዚህ እኛም ከዚህ በፊት ከነበረን ስህተት ተምረን የዘላለም ራዕዮች ባለቤት በመሆን ሰዎችን እናፍራ አደራ!

የአጭር ጊዜ ባለራዕዮች አንሁን። ይህ እኛም ሆንን ቤተሰባችን የትም አያደርሰንም። ይልቁንም ሰፋ አድርገን እናልም ። ህልማችንም በተግባር እንደግፈው። እናታችን ከእኛ ማግኘት የሚገባትን ነገር እንስጣት ።

ይህን ያህል ጊዜ አጥፍቼ ልጽፍልህ የወሰንኩት በእኛ ሰበብ እድገት እና ሰላም ያጣውን ቤታችንን ወደ ትክክለኛው መንገድ ለመመለስ ብዬ ነው ። አይ የለም የምፈልገውን ስልጣን እስካገኝ ድረስ ሎሌነቱ ተመችቶኛል ካልክ አንተም እኔ እንደ ዱቄት መበተንህ አይቀርም ።

ፈላስፈው እንዲህ ይላል «ሰው ሁሉ ልብ ብሎ እንዲሰማህ አንደበትህን እውነት መናገር አስለምዳት ። በሁሉም ዘንድ እንድትወደድ ነፍስህን ሰው መውደድ አስለምዳት» ሞረሽ ወንድሜ ይህ ድንቅ ምክር ነው። በዚህ የፈላስፋው ምክር ምስር እና መርዝ ወጊው ሃኪም ቤተሰባችን ለማጥፋት ያቀዱትን የጥፋት እቅድ ማክሸፍ የሁላችንም ድርሻ ነው። ያልሆነ ተስፋ እና ውሸት ቤተሰብን አይገነባም። ይልቁንም ያጠፋናል እንጂ።

በመጨረሻም ለአይነ ስጋ እስኪያበቃን ሰላም ለሁላችን ይሁን ። እናታችንንም ሆነ እኛን ከክፋ ሁሉ ነገር እንዲጠብቅልን እመኛለሁ። የአንተው ውድ ወንድምህ ሞረሽ ።

# የዘመን ጥበብ

# ፈሊጣዊ አነጋገር ምንድነው?

**ዋለልኝ አየለ**

ባለፈው ሳምንት የስነ ጽሑፍ ባለሙያዎችን አስተያየትና ማብራሪያዎች መሠረት አድርገን ስለ ምሳሌያዊ አነጋገሮች አውርተናል። ስለ ፈሊጣዊ አነጋገሮች እንመለስበታለን ባልነው መሠረት እነሆ ዛሬ ስለ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ምንነት እናወራለን።

ለእንግሊዝኛ ቋንቋ የምንሰጠውን ትኩረት ያህል ለአገር ውስጥ ቋንቋዎች አንሰጥም። በዚህም ምክንያት ቋንቋዊ የሆኑ ነገሮች ልብ አይባሉም፤ የአገር ውስጥ ቋንቋ አለማወቅ እንደ አለማወቅ አይቆጠርም። እንደ አለማወቅ የሚቆጠረው እንግሊዝኛ አለማወቅ ነው። የእንግሊዝኛ አጻጻፍ የተሳሳተ ሰው ብዙ ይሳቅበታል፤ በአገር ውስጥ ቋንቋ መሳሳት ግን እንደምንም አይቆጠርም።

እርግጥ ነው ቋንቋ በራሱ እውቀት አይደለም፤ ዳሩ ግን የውጭ ቋንቋዎች በየዘርፉ የተብራራና የተደራጀ ማብራሪያ ሲኖራቸው የአገር ውስጥ ቋንቋዎቻችንም ሊኖራቸው ይገባል።

ፈሊጣዊ አነጋገር ብዙ ሰው ልብ የሚለው አይደለም። ፈሊጣዊ ንግግሮቹን በልማድ እንጠቀማቸዋለን፤ ፈሊጣዊ ንግግር ምንድነው? ቢባል ግን ለማብራራት እንቸገራለን።

ፈሊጣዊ ንግግር በእንግሊዝኛው «Idiom» የሚባለው ነው። Idiomatic Speech/ Expression ይሉታል። በእነዚህ ቃላት ላይ እጅግ ብዙ ማብራሪያዎችን እናገኛለን፤ በአማርኛው ሲሆን ግን አናገኝም።

በ1983 ዓ.ም በደራሲ ዳኛቸው ወርቁ እና አምሳሉ አክሊሉ የተጻፈ እና በኩራዝ አሳታሚ ድርጅት የታተመ «የአማርኛ ፈሊጦች» የሚል መጽሐፍ አለ። መጽሐፉ ከመግቢያው እንደሚነግረን በእንግሊዝኛ ቋንቋ ላይ እንጂ በአማርኛ ቋንቋ ፈሊጣዊ ንግግሮች ላይ የተጻፉ መጻሕፍትና ማብራሪያዎች የሉም። መጽሐፉን ለመጻፍ ያነሳሳቸውም ይህን ችግር ተረድተው ነው። ከዚህ መጽሐፍ እና ሌሎች የእንግሊዝኛ ማብራሪያዎች ባገኘነው መረጃ ፈሊጣዊ ንግግር ምንድነው? የሚለውን እንመልከት።




ፈሊጣዊ ሐረጋት ወይም ዓረፍተ ነገሮች የሚፈጠሩት ከሁለት ቃላት ጥምረት ነው። የፈሊጣዊ ንግግር ትርጉም በቃላቱ መሠረታዊ ትርጉም አይደለም። የቃላቱ መሠረታዊ ትርጉም ማለት እነዚያ ቃላት የቆሙለት የተለመደው (እማሬያዊ) ትርጉማቸው ማለት ነው። ፈሊጣዊ አነጋገር የሚፈጠረው ከእነዚህ ቃላት መሠረታዊ ትርጉም ባህሪ በመነሳት ሌላ ተደራቢ ትርጉም ለመስጠት ነው። ግልጽ ለማድረግ በምሳሌ ይሁን።

«የግንባር ሥጋ» የሚባል ፈሊጣዊ ንግግር አለ። ይህ ሐረግ የተፈጠረው ግንባር እና ሥጋ ከሚሉ ቃላት ነው። ሁለቱም ቃላት መሠረታዊ (የተለመደው እማሬያዊ ትርጉም ማለት ነው) አላቸው። ግንባር የጭንቅላታችን የፊት ክፍል ሲሆን ሥጋ ደግሞ የእንስሳትም ሆነ የሰው አጥንትን የሚሸፍነው ክፍል ማለት ነው።

ከእነዚህ ቃላት የተፈጠረው «የግንባር ሥጋ» የሚለው ፈሊጣዊ ንግግር «ደፋር፣ ጀግና፣ ግልጽ» የሚል መልዕክት የሚያስተላልፍ ነው። ይህ ትርጉም የተሰጠው ደግሞ ሐረጉን ከፈጠሩት ቃላት ባህሪ በመነሳት ነው። ግንባር ፊት ለፊት የሚገኝና ማንም በቀላሉ የሚያየው የሰውነት ክፍል ነው፤ የሚደበቅ አይደለም። ግንባር ላይ ያለ ሥጋ ጠንካራ ነው። ስለዚህ አንድ ግልጽ እና ደፋር የሆነ ሰው «የግንባር ሥጋ» ይባላል። ይሄ ማለት ግንባር ላይ ያለውን ሥጋችንን እየገለጽን ሳይሆን የሰውየውን ግልጽ ተናጋሪነትና ድፍረት እየገለጽን ነው ማለት ነው።

ፈሊጣዊ ንግግር ቃላት መጀመሪያ ከቆሙለት እሳቤ በመነሳት ተመሳሳይ ለሆኑ ሌሎች እሳቤዎች ይውላል ማለት ነው።

እዚህ ላይ ልብ ማለት ያለብን አንድ ነገር አለ። የምሳሌያዊ ንግግሮች እና ፈሊጣዊ ንግግሮች ባለቤት የጥንቱ ማህበረሰብ ነው። በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ የሚታሰቡ እሳቤዎች አንዳንዶቹ ልማዳዊ ናቸው፤ በሳይንስ ካሰብነው ላይመጣጠን ይችላል። ለምሳሌ ሆድ እና ልብ የማሰቢያ ክፍል ተደርገው ነው የሚታሰቡት። «ነገር በሆዱ ይዞ» ይላሉ። ሀሳብ የሚያብሰለስለው ሆዱ ውስጥ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ነው።

በዚህ መሠረት «ሆደ ሰፊ» የሚለውን ፈሊጣዊ ንግግር እንውሰድ። ሆደ ሰፊ የተባለበት ምክንያት ሰው የሚያስበው በሆዱ ነው ተብሎ ይታሰብ ስለነበር አስተሳሰቡ ሰፊ የሆነ፣ ቻይ፣ ታገሽ ለማለት ነው። በጥሬው እንተርጉመው ከተባለ ደግሞ «ሆደ ሰፊ» ሲባል ምናልባትም ሆዳም (ብዙ የሚመገብ) ለማለት ሊመስል ይችላል። በፈሊጣዊ ንግግር ግን ሆደ ሰፊ ማለት ቻይ ወይም ታጋሽ ማለት ነው።

በዚሁ እግረ መንገድ ስለ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ(ትርጉም) እናውራ። እማሬያዊ ትርጉም ማለት የአንድ ቋንቋ ቃል መጀመሪያ የታሰበለትና በመደበኛነት የሚያገለግልበት ትርጉም ማለት ነው። ፍካሬያዊ ፍቺ ማለት ደግሞ ከዋናው ቃል በመነሳት ሌላ ተደራቢ ትርጉም ሲሰጠው ማለት ነው። ለምሳሌ፤ እሳት የሚለው ቃል የሚገልጸው ለማብሰያነት፣ ለማቀጣጠል፣ ብርድን ለማስለቀቅ የምንሞቀው በአጠቃላይ የሚነደውን እሳት ይገልጻል። ከእሳት ባህሪ በመነሳት ግን እሳት የሚለው ቃል ሌላ ተደራቢ ትርጉም ይሰጠዋል። ይሄውም ኃይለኛ፣ አስፈሪ፣ የማይነካ ማለት ነው። ገበያ እንኳን ሲወደድ «እሳት ሆነ» ይባላል፤ የማይነካ ማለት ነው።

ከዚህ በመነሳት ፈሊጣዊ ንግግሮች ይፈጠራሉ። ለምሳሌ፤ ዓይን ያው ዓይን ነው፤ ለማየት የምንጠቀምበት የሰውነት ክፍል ማለት ነው። ከዚህ በመነሳት ግን የመርፌ ዓይን፣ የእንጀራ ዓይን የሚሉ ፈሊጣዊ ንግግሮች ይፈጠራሉ። መርፌም ሆነ እንጀራ ግዑዝ አካል ናቸው፤ አያዩበትም።

> **ወደ ውስጥ የሰውነት ክፍል እንኳን ብንገባ፤ ሀሞታም(ኀበዝ)፣ ሀሞተ ቢስ(ፈሪ)፣ ሀሞቱ የፈሰሰ(ሰነፍ) የሚሉትን እናገኛለን**

ቀደም ሲል እንዳልነው የፈሊጣዊ ንግግሮች ፈጣሪዎች የጥንቱ ማህበረሰብ ነው። ስለዚህ ቃላቱም የቆዩ እና ምናልባትም አሁን አገልግሎት ላይ የሌሉ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ «ቆሌ» የሚለው ቃል ያገለግል የነበረው የጣዖት አምልኮ (ውቃቢ) በነበረበት ጊዜ ነው። አሁንም ድረስ ግን «ቆሌዬን ገፈፈው!» የሚባል ፈሊጣዊ አነጋገር አለ። አስደነገጠኝ፣ ክብሬን አሳጣኝ፣ አቀለለኝ እንደማለት ነው። ቆሌ ቢስ ማለት ደግሞ ያልተረጋጋ፣ ችኩል፣ ቀላል ማለት ነው።

የፈሊጣዊ ንግግሮች አስፈላጊነትና ጥቅም ሀሳብን በተዝናና መንገድ ጥልቅ መልዕክት ማስተላለፍ ነው። ሰዎች በባህሪያችን በጣም ግልጽ ከሆነ ነገር ይልቅ ትንሽ ሽፈን ያለ ነገር መተርጎም እንወዳለን። ከስብሰባዎች እና ከመድረክ መልዕክቶች ይልቅ በኪነ ጥበብ መልክ የሚሠሩ መልዕክቶች አይረሴ የሚሆኑት ለዚህ ነው። ውስጠ ወይራ የሆኑ ነገሮች ወደ ሰዎች አዕምሮ ውስጥ ሰርስሮ የመግባት ኃይል አላቸው።

የቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎች እንደሚሉት፤ ፈሊጣዊ ንግግሮችን በቀላሉ የሚረዷቸው ቋንቋውን የተላመዱ ሰዎች ናቸው። አለበለዚያ በጥሬው (Literally) ሊተረጉሙት ይችላሉ። ለዚህም ነው አንድ በሌላ ቋንቋ አፉን የፈታ ሰው የአማርኛ ፈሊጣዊ ወይም የምሳሌያዊ ንግግር ቃላት ሲናገር «ቅኔ እየፈለጠ ነው» የሚባል። ከመደበኛዎቹ ቃላት አልፎ ፈሊጣዊ ቃላትን ከተናገረ ያ ሰው ቋንቋውን ተላምዶታል ማለት ነው። ያ ባይሆን ኖሮ «ሆደ ሰፊ» ሲባል ሆዱ ትልቅ የሆነ ወፍራም ሰው ይመስለው ነበር።

ፈሊጣዊ ንግግሮችን የሥነ ጽሑፍና የጥበብ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ፖለቲከኞችም በየመድረኩና በየመገናኛ ብዙኃኑ ይጠቀሟቸዋል። ንግግራቸውን ለዛ ስለሚያላብሰው እና መልዕክቱን በጥልቀት ስለሚያስተላልፍላቸው ነው። እገሌ ንግግር አይችልም ወይም ሲናገር ይዘባርቃል ከማለት ይልቅ «የምላስ ወለምታ» በሚል ሊገለጽ ይችላል። ሌባ ላለማለት የእጅ አመል ሊባል ይችላል።

የፈሊጣዊ ንግግሮች ቃላት በግልጽ እንደሚታየው የውስጥም ሆነ የውጭ የሰውነት ክፍሎቻችን ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። ይህ ነገር በአማርኛ ቋንቋ ብቻ ነው ወይስ በሌሎች ቋንቋዎችም ያለ ነው? የሚለውን ደራሲ ዳኛቸው ወርቁ እና አምሳሉ አክሊሉ በወቅቱ ዳሰሳ አድርገዋል። ልክ እንደ አማርኛው ሁሉ በኦሮምኛም ያገኙት ተመሳሳይ ነገር ነው። በሌሎች የውጭ አገራት ቋንቋዎች ላይ ተመሳሳይ ነገር ይኖር ይሆን? የሚለውን ለሌሎች አጥኚዎች ጥቆማ ሰጥተዋል።

የፈሊጣዊ ንግግሮች አካል ክፍል ላይ ማተኮር በውጭ አገራት ቋንቋዎችስ ምን ያህል ይታወቅ ይሆን ብዬ ሳስስ «Idiomatic expressions with body parts in English and French» በሚል ርዕስ በአውሮፓውያኑ 2020 የተሠራ ጥናት አገኘሁ።

በጥናት ትንታኔው ውስጥ፤ እግር፣ ክንድ፣ አንጎል፣ ጆሮ፣ ዓይን፣ ፊት፣ ጣት፣ ጫማ እግር(Foot)፣ ፀጉር፣ እጅ፣ ጭንቅላት(ራስ)፣ ልብ፣ ተረከዝ(Heel)፣ አንገት፣ አፍንጫ፣ ቆዳ፣ ጥርስ፣ ምላስ… የሚባሉት የሰውነት ክፍሎች ተጠቅሰዋል። እያንዳንዳቸው የተጠቀሱት ራሳቸውን ችለው ርዕስ ሆነው ነው። በአንዱ የሰውነት ክፍል ብቻ በእንግሊዝኛም በፈረንሳይኛም ብዙ ፈሊጣዊ ንግግሮች አሉ። ስለዚህ በውጭ ቋንቋዎችም ፈሊጣዊ ንግግሮች የሰውነት ክፍል ላይ ያተኩራሉ ማለት ነው።

በነገራችን ላይ የእነ ዳኛቸው ወርቁ መጽሐፍ የተጻፈው በ1979 ዓ.ም (የመጀመሪያው ዕትም) ነው። በዚህ ወቅት ደግሞ የበይነ መረቡ ዓለም አልነበረም።

ወደ አማርኛ ፈሊጣዊ ንግግሮች ስንመጣ ከላይ በእንግሊዝኛና ፈረንሳይኛ በተዘረዘሩት የሰውነት ክፍሎች ሁሉ ፈሊጣዊ ንግግር አለ። ለምሳሌ፤ እጄ ሰባራ (ሙያ የሌለው)፣ ፀጉረ ልውጥ (የአካባቢው ሰው ያልሆነ)፣ ልበ ደንዳና (ግደለሽ)፣ እግረ እርጥብ (ዕድለኛ)፣… እያልን ብንቀጥል በአንዱ የሰውነት ክፍል ብቻ ብዙ ፈሊጣዊ ንግግሮች አሉ።

ወደ ውስጥ የሰውነት ክፍል እንኳን ብንገባ፤ ሀሞታም(ኀበዝ)፣ ሀሞተ ቢስ(ፈሪ)፣ ሀሞቱ የፈሰሰ(ሰነፍ) የሚሉትን እናገኛለን።

ለምን የሰውነት ክፍሎቻችን ላይ አተኮሩ? ለሚለው ለጊዜው በጥናት የተደገፈ መረጃ አላገኘሁም። እስከዚያ ግን መገመት እንችላለን። የሰውነት ክፍሎቻችን ተግባራቸውን በቅርበት የምናውቃቸውና በየድርጊቱ የምናያቸው ናቸው። ስለዚህ ክስተቶችን ሁሉ በእነርሱ ለመመሰል ቀላል ነው። ቀደም ባለው ዘመን እንዲህ እንደ አሁኑ የረቀቀ ቴክኖሎጂ አልነበረም። ስለዚህ ነገሮችን የምናነፃፅረው አጠገባችን ባሉት እንስሳት እና ከራሳችን የሰውነት ክፍሎች ድርጊት ጋር በማመሳሰልና በማነፃፀር ነው።

ለእንግሊዝኛ ቋንቋ የምንሰጠውን ትኩረት ያህል ለአገራችን ቋንቋዎችም እንስጥ! የራሳችንን ቋንቋ ማወቅ እንግሊዝኛ እንዳናውቅ አይከለክልም፤ እንዲያውም የበለጠ ያቀርባል። «የቋንቋ ትምህርት ክፍል፣ የቋንቋ ተማሪ» ሲባል የግድ የአንድ ቋንቋ ማለት አይደለም። እንግሊዝኛ ቋንቋ ላይ መራቀቅ አማርኛን በቀላሉ እንድንረዳ ያደርጋል እንጂ እንዲከብደን አያደርግም። ምክንያቱም የቋንቋው ባህሪያት ተመሳሳይነት ይበዛቸዋል። ስለዚህ ለአገራችን ቋንቋዎችም ትኩረት እንስጥ!

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ተደራራቢ የአካል ጉዳትና ውጣ ውረዱ

**እፀገነት አክሊሉ**

የሥራሽ ምሕረት ከተወለደች ጀምሮ ዓይነሥውርና መስማት የተሳናት ናት፡፡ የሰራሽ አሁን የ15 ዓመት ታዳጊ ብትሆንም የኑሮ አለመመቸት ብሎም የሚረዳት ማጣት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ባለችበት ቁጭ ብላ እንድትውል አድርጓታል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ እግሮቿ እንደልባቸው እንዳይንቀሳቀሱ እንዲሁም የህይወት ክህሎት የሚባሉትን ራስን ችሎ መመገብ፣ መልበስ፣ መጸዳዳትና ሌሎችንም እንዳታውቅ አድርጓት ቆይቷል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ማንኛውንም የምታከናውናቸውን ነገሮች በሰዎች እርዳታ እንዲሆን አስገድዷል፡፡

የሥራሽን የሚፈታተናት የቤተሰቦቿ አቅመ ደካማነት ብቻ ሳይሆን ዓይነ ሥውርና መስማት የተሳናቸው (ተደራራቢ የአካል ጉዳት ያለባቸው) ምን ዓይነት ድጋፍ እንደሚሹ አለማወቃቸውም ጭምር ነው፡፡ ምግብና መጠጥ ስትፈልግ፣ መፀዳዳት ሲኖርባት ወይም ስትታመም የምትገልጽበትን መንገድ አይረዱላትም፡፡ ከቤተሰቦቿ ከእናቷና ታላቅ እህቷ ጋር ትግባባለች፡፡ነገር ግን ሰው ስላለመደች ሌሎች ሰዎች ሲቀርቧት ትፈራለች፡፡ ፍላጎቷን የሚገነዘብላት ስታጣ ራሷን ትነክሳለች፣ ዕቃም ትሰብራለች።

እናቷም ሆኑ ሌሎች ቤተሰቦቿ የሰራሽ ልጃቸውን የመሰሉ ተደራራቢ የአካል ጉዳት ያለባቸው እንዳሉ ባለማወቃቸው ምክንያት ፈጣሪያቸውን ያማርሩም ነበር፡፡ ችግሯን ተረድተው መርዳት መቸገራቸው ደግሞ ይበልጡኑ ያስከፋቸዋል ፡፡ ከዓይነሥውራን ወይም መስማት ከተሳናቸው አብዛኞቹ መማር ቢችሉም ተደራራቢ የአካል ጉዳት ያለባቸው በመሆኑ ዕድሉን አያገኙም፡፡ የሥራሽ ከልጅነቷ አንስቶ ብትደገፍ እንደሌሎች ልጆቻቸው ትሆን እንደነበር እናቷ ቢያምኑም በማንና እንዴት ልትደገፍ እንደምትችል ደግሞ እርግጠኛም ሳይሆኑ ኖረዋል ፡፡

ቢዘገየም የሰራሽ አሁን ላይ ዓይነሥውራንና መስማት የተሳናቸው ማኅበርን በመቀላቀሏ ብዙ ለውጦችን አምጥታለች፡፡ በበትር እየታገዘች መንቀሳቀስ፣ በራሷ መመገብና የምትፈልገውን መግለጽ የምትችልባቸው መንገዶች በሥልጠና በማግኘቷም የተወሰነ ለውጥ እየታየባት ነው ፡፡ ነገር ግን የሰራሽ የምታገኛቸውን ስልጠናዎች ከማዕከሉ ወጥታ ቤት በምትሄድበት ጊዜ ለመተግበር ትቸገራለች፤ ምክንያቱ ደግሞ የመርጃ መሳሪያዎቹን በቅርብ ማግኘት ስለማትችል ነው፡፡ ይህም ቢሆን ግን አሁን ላይ ከቀድሞ ሁኔታዋ የተለየ ሆናለች ፡፡

ዓይነሥውር ናትና የመስማት እክል ከውልደት አንስቶ ወይም ከጊዜ በኋላ ሊገጥም ይችላል፡፡ ጉዳቱ ሙሉ በሙሉ መስማትና መናገር የማይችሉ፣ ነገር ግን በከፊል የሚያዩ፣ በከፊል የሚሰሙና ሙሉ በሙሉ ማየት የማይችሉና በከፊል የሚያዩና በከፊል የሚሰሙትን ያካትታል፡፡ የተለያየ አካል ጉዳት ያለባቸውን ሰዎች የሚያሰባስቡ ማኅበራት ከተቋቋሙ አስርተ ዓመታትን ቢያስቆጥሩም ተደራራቢ የአካል ጉዳት ያለባቸው ማኅበር የተመሠረተው ግን በ1996 ዓ.ም ነው፡፡

ሰባ ደረጃ አካባቢ የሚገኘው የኢትዮጵያ ማየትና መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር የሥራሽን ለመሰሉ ሥልጠና ይሰጣል፡፡ ታዳጊዎች ራሳቸውን እንዲችሉ የሚረዳ የክህሎት ሥልጠናና አዋቂዎች የሙያ ሥልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል ፡፡ ሹራብና ብሩሽን የመሰሉ መገልገያዎች መሥራት ይማራሉ፡፡ ተደራራቢ የአካል ጉዳት ያለባቸው መሥራት አይችሉም የሚለውን የተሳሳተ አመለካከት ለመቅረፍ የሚያስችልም ስለመሆኑ በራሳቸው አንደበት ይናገራሉ፡፡

ወይዘሪት ሮማን መስፍን የማኅበሩ መሥራችና ዳይሬክተር ናቸው፡፡ ሮማን በቀኝ ጆሮአቸው በቅርበት ሲያነጋግሯቸው ይሰማሉ ፡፡ የአራት ዓመት ሕፃን እያሉ በመውደቅ ምክንያት ዓይናቸው ጠፍቶ ሰበታ የዓይነ ሥውራን ትምህርት ቤት እያሉ ደግሞ የጆሯቸው የመስማት ብቃት መቀነሱንም ይናገራሉ፡፡

ዓይነሥውራንና መስማት የተሳናቸው የሚገጥማቸው ውጣ ውረድ ለመቀነስ ማኅበሩን ከሌሎች ዓይነሥውራንና መስማት የተሳናቸው እንዲሁም ያልተጎዱ አጋዥ ግለሰቦች ጋር አቋቁመዋል፡፡ ከዓይነሥውራንና መስማት የተሳናቸው ልጆቻቸው ጋር መግባቢያ መንገዶችን የማያውቁ ቤተሰቦች በርካታ መሆናቸውና ዘመን አመጣሽ መሣሪያዎች በቀላሉ አለመገኘታቸው ተጎጂዎች በየቤታቸው እንዲቀሩ አድርጓቸዋል ይላሉ ፡፡

ተደራራቢ የአካል ጉዳት ያለባቸው ከሌሎች ከሚግባቡበት መንገድ አንዱ ታግ ታይል (በእጅ መዳሰስ) ነው፡፡ በተጨማሪ የብሬል ታግታይል (በእጅ ብሬል እየዳሰሱ) መግባባት ይቻላል፡፡ በከፊል ማየት የሚችሉ የምልክት ቋንቋ ይጠቀማሉ፡፡ ከአጋዥ መሣሪያዎች መካከል ፐርኪንስን ታይፕ (በአስተርጓሚ ታግዞ የሚነበብበትና ምላሽ የሚሰጥበት) አንዱ ነው፡፡

ሙሉ በሙሉ ዓይነሥውር የሆኑና መስማት የተሳናቸው ለመንቀሳቀስ የሚረዳቸው ሚኒ ጋይድ የሚባል መሣሪያ አለ፡፡ በአንድ እጃቸው በትር ይዘው ሲጓዙ አቅጣጫቸውን እንዲያስተካክሉ ሚኒ ጋይዱ ቫይብሬት እያደረገ ይመራቸዋል። ሮማን እንደሚሉት ፣ ከነጭ በትር፣ ብሬልና መስማት የሚያግዝ (ሒሪንግ ኤይድ) ውጪ ሌሎች መሣሪያዎች በቀላሉ አይገኙም፡፡

በቅርብ ወደ ኢትዮጵያ የመጣችው ኢትዮጵያዊት አሜሪካዊት ሀበን ግርማ የምትጠቀምበት ብሬል ዲስፕሌይ የተባለ መሣሪያ ነው፡፡ ሀበን ከሐርቫርድ ዩኒቨርሲቲ በሕግ የተመረቀች ዓይነሥውርና መስማት የተሳናት የአካል ጉዳተኞች መብት ተሟጋች ናት፡፡ ከሐርቫርድ ምርጥ 20 ሕግ ተማሪዎች አንዷም ናት፡፡ ሮማን እንደሚሉት ፣ እንደ ሀበን ዕድሉን ያገኙ በጣት የሚቆጠሩ ሲሆኑ፣ አጋዥ መሣሪያ ማግኘት አንዱ የለውጥ መጀመሪያ ነው ይላሉ፡፡ ማኅበሩ መሣሪያ በዕርዳታ ሲያገኝ በየክልሉ ቢያካፍልም የመሣሪያው ውድነት እንደሚፈለጉት እንዳይዳረስ ያግዳቸዋል፡፡

እንደ ዳይሬክተሯ ገለጻ፣ ማኅበሩ ሥራ ሲጀምር በየክልሉ ጉዳተኞችን ያሰባስቡ ነበር፡፡ ስለ ጉዳቱ የጠለቀ ዕውቀት ባለመኖሩ አንዳንዶች ቤት ውስጥ ታስረው ተቀምጠው ነበረ፡፡ ከእንቅስቃሴ ታግደው የነበሩ ልጆችን መሠረታዊ ክህሎት ለማስተማር ጊዜ ወስዷል፡፡ አሁንም ከየቤቱ የተደበቁ አካል ጉዳተኞች ዕርዳታ እንዳላገኙ ያስረዳሉ ፡፡ ዓይነ ሥውራንና መስማት የተሳናቸው ፍላጎቶቻቸውን ማሟላት እንዲሁም መደበኛ ትምህርትና ሥራ የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት የመንግሥትም ግዴታ ነው ይላሉ ፡፡

«እንደማንኛውም ሰው የሚያስፈልጋቸው ተሟልቶ ውላቸው በነፃነት የመኖር መብታቸው መጠበቅ አለበት፡፡ ከውልደትም ይሁን ከጊዜ በኋላ አደጋው ሲከሰት ማግለል ሳይሆን እንደማንኛውም ሰው ማኅበራዊ ሕይወታቸው በተመቻቸ መንገድ መምራት አለባቸው፤» ባይ ናቸው፡፡

ተደራራቢ የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ቤተሰቦች ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለባቸው አያይዘው የሚገልጹት ዳይሬክተሯ፤ ሁሉም የድርሻውን ከተወጣ ማህበሩም ያለበት የበጀት እጥረት ይፈታል የበጀት እጥረቱ ተወገደ ማለት ደግሞ በየክልሉ ቅርንጫፍ ከፍቶ ዕርዳታ መስጠት ይችላል በማለት ሁኔታውን ያብራራሉ፡፡

ተደራራቢ የአካል ጉዳት ያለባቸውን የሚወክልና ድምፃቸውን የሚሰማ የለም፤ማኅበሩን የሚደግፉ ተቋሞች ቢበራከቱ ቢያንስ መሠረታዊ የክህሎት ሥልጠና ለሕፃናት መስጠት ይቻላል ፡፡ አሁን የሚሰጠው አገልግሎት በአገሪቱ ካሉት ጉዳተኞች ቁጥር አንፃር አናሳ ነው፡፡

ዓይነሥውርና መስማት የተሳናቸው ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች ባለማወቅ ልጆቻቸውን መሠረታዊ የአኗኗር ክህሎት ሳያስተምሩ ይዘገያሉ፡፡ ይህ ሊቀረፍ የሚችለው በአፋጣኝ ወደ ባለሙያ በመሄድ ክህሎቱን እንዲማሩ በማድረግ ሲሆን ተደራራቢ የአካል ጉዳት የሚገባውን ያህል ሰፊ ትኩረት እንዳላገኘ በመግለጽ ስለ ሌሎች የአካል ጉዳቶች ያለው ግንዛቤ አነስተኛ ሆኖ ሳለ ብዙም ያልታወቀውን ተደራራቢ ጉዳት ለመቀበል ለኅብረተሰቡ ያዳግታል ይላሉ፡፡

የቀለም ትምህርት ለማግኘት በከፊል መስማት ወይም በከፊል ማየት የሚችሉ የተሻለ ዕድል አላቸው ፡፡ ተደራራቢ አካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ግን እንደማንኛውም ሰው መኖር እንዲችሉ የማኅበረሰቡ ቀና አመለካከት የግድ መታከል አለበት ፡፡

«ዓይነ ሥውራንና መስማት የተሳናቸው ተደራራቢ ጉዳታቸው ሕይወታቸውን ፈታኝ ያደርገዋል፡፡ በዳሰሳ ወይም በሌላ መንገድ የመግባባት ልምዱ ስለሌለ አንዳንዴ መፈጠራቸውን እስኪጠሉ ይማረራሉ፤ በአደባባይ ወጥተው ከሚታዩ ተደራራቢ የአካል ጉዳት ሰለባዎች ቁጥር ቤተሰቦቻቸው በየጓዳው የደበቋቸው ይበልጣሉ፡፡ ችግሩን የመቅረፍ ኃላፊነት የእያንዳንዱ ግለሰብ ነው፡፡ አካል ጉዳት አማክሮ አይመጣም በማንም ላይ ሊደርስ ይችላል፤» በማለት ነግ በኔ ብሎ ማሰብ ተገቢ እንደሆነ ያሳስባሉ፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ፈረንሳይ የቡርኪናፋሶ ኤምባሲዋ እና ሌሎች ተቋማት እንዲጠበቁላት ጠየቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ፈረንሳይ የቡርኪናፋሶ ኤምባሲዋ እና ሌሎች ተቋማት እንዲጠበቁላት ጠየቀች፡፡ የቶማስ ሳንካራ ሀገር ቡርኪናፋሶ በሀገሯ ያለው የፈረንሳይ ጦር ለቆ እንዲወጣ ተቃውሞ ያስነሱ ሲሆን፤ ቡርኪናዊያን በኡጋዱጉ በሚገኘው የፈረንሳይ ኤምባሲ ላይ ጥቃቶች በማድረስ ላይ ናቸው፡፡

ፈረንሳይ በቡርኪናፋሶ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ትገባለች በሚል የሚከሱት ቡርኪናዊያን በሀገራቸው የሚገኙ የፈረንሳይ ትምህርት ቤት፣ የዲፕሎማሲ እና ሌሎች ተቋማት ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን ሮይተርስ ዘግቧል፡፡ በተለይም ባለፉት 30 ቀናት ውስጥ ቡርኪናዊያን ከሶስት ጊዜ በላይ ጥቃቶችን በፈረንሳይ ተቋማት ላይ ተቃውሟቸውን ያሰሙ ሲሆን፤ በሀገራቸው ያለው የፈረንሳይ ጦር ሽብርተኞችን እየረዳ ነው፣ አምባገነኖችን ትረዳለች፣ ሀብታችንን እየመዘበረች ነው እና ሌሎችንም ክሶችን በፓሪስ ላይ አሰምተዋል፡፡

በዚህም መሰረት ፈረንሳይ ከቡርኪናፋሶ ለቃ እንድትወጣ የጠየቁ ሲሆን፤ በቅርቡ በመፈንቅለ መንግስት ወደ ስልጣን የመጡት ኢብራሂም ትራውሬ ከሩሲያ ጋር ወዳጅነት መመስረት እንደሚፈልጉ ተናግረዋል፡፡ በኡጋዱጉ የሚገኘው የፈረንሳይ ኤምባሲ ለቡርኪና ፋሶ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በጻፈው ደብዳቤ የሀገሪቱ ወታደራዊ መንግስት ጥበቃ እንዲያደርግላቸው ጠይቋል ተብሏል፡፡

ቡርኪናፋሶ በዓለም አቀፍ ህግ ስምምነት መሰረት የዲፕሎማቲክ ተቋማት ከማንኛውም ጥቃት የመጠበቅ መብት ህግን እንድታከብር ኤምባሲው በጻፈው ደብዳቤ መጠየቁ ተገልጿል፡፡በፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን የሚመራው የፈረንሳይ መንግስት በበኩሉ በምዕራብ አፍሪካ የተሰማራው ሰላም አስከባሪ ጦር በቀጣዮቹ ዓመታት ሙሉ ለሙሉ እንደሚያስወጣ አስታውቋል፡፡

ፈረንሳይ በምዕራብ አፍሪካ ሀገራት ተቃውሞ እየገጠማት ሲሆን የማሊ ወታደራዊ መንግስት ከወራት



**በቡርኪናፋሶ መዲና የሚገኘው የፈረንሳይ ኤምባሲ በተቃዋሚዎች ጉዳት ደርሶበታል፣**

በፊት ባቀረበው ጥያቄ መሰረት ጦሯን ሙሉ ለሙሉ ማስወጣቷ ይታወሳል፡፡ከፈረንሳይ ጋር የሰላም አስከባሪ ጦሯን ወደ አፍሪካ ከላኩ ሀገራት መካከል አንዷ የሆነችው ጀርመን በምዕራብ አፍሪካ ያሰማራችውን ጦር እንደምታስወጣ ከሰሞኑ ይፋ ማድረጓ እንደሚታወስ አል ዐይን ዘግቧል፡፡

## ቱርክ በከባድ ርዕደ መሬት ተመታች

ቱርክ በከባድ ርዕደ መሬት መመታቷ ተነገረ። የሀገሪቱን ዱዚያ ግዛት ክፉኛ ያንቀጠቀጠው ርዕደ መሬት እስካሁን ከ40 በላይ ሰዎች ላይ ጉዳት ማድረሱ እየተነገረ ነው፡፡ ርዕደ መሬቱ የሀገሪቱ ሰሜን ምዕራባዊ ግዛት ከሆነችው ዱዚያ ነው የተነሳው።የቱርክ የአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ባለስልጣን እንዳስታወቀው አደጋው በሬክተር ስኬል 5 ነጥብ 9 ሆኖ መመዝገቡን ቢቢሲ ዘግቧል፡፡

የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋው በርካታ ግዛቶችን እና ከተሞች ማዳረሱ የተነገረ ሲሆን፤ እስከ መዲናዋ አንካራ እና ኢስታንቡል ድረስ ንዝረቱ ተሰምቷል ተብሏል። ከባዱ የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ በዱስዜ ግዛት ትምህርት ቤቶች እንዲዘጉ ምክንያት ሆኗል።

ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስም የኤሌክትሪክ ስርጭት በፍጥነት እንዲቋረጥ መደረጉን ነው አናዶሉ ያስነበበው። አደጋው እስካሁን ያደረሰው ጉዳት ሪፖርት አልተደረገም ብለዋል። የቱርክ የሀገር ውስጥ ጉዳዮች ሚኒስትር ሱሌማን ሶይሉ። ቢቢሲ ግን እስካሁን ከ47 በላይ ሰዎች ጉዳት ደርሶባቸዋል የሚል መረጃን አጋርቷል።

ከቱርኳ ትልቅ የንግድ ከተማ ኢስታንቡል በ230 ኪሎ ሜትር ርቀት የምትገኘው ዱዚያ ከተማ በፈረንጆቹ 1999 የ845 ሰዎችን ህይወት የቀጠፈ ከባድ ርዕደ መሬት



ደርሶባታል። በርዕደ መሬት መለኪያ 7 ነጥብ 2 ሆኖ የተመዘገበው አደጋ የከተማዋን ህንፃዎች ማፈራረሱን ተከትሎ ከ80 በመቶ በላይ የከተማዋ ህንፃዎች አደጋን እንዲቋቋሙ በአዲስ መልክ ተገን ብተዋል።

ከ1999ኙ አስከፊ አደጋ ከወራት በኋላ ኢዝሚት በተሰኘችው ከተማ ከ17 ሺህ በላይ ሰዎችን የጨረሰ ርዕደ መሬት መከሰቱን መረጃዎች ያሳያሉ። ከሰሞኑ በተመሳሳይ በኢንዶኔዥያ በደረሰ የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ ከ200 በላይ ሰዎች ህይወታቸው ማለፉ ተገልጿል። በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ባቆሰለው አደጋ የተጎጂዎቹ ቁጥር አሁንም ድረስ እያሻቀበ መሆኑን የዘገበው አል ዐይን ነው።

# ስፖርት



## ፌዴሬሽኑ በዕድሜ ተገቢነት ላይ ጠንካራ እርምጃ እንደሚወስድ አሳወቀ

**ብርሃን ፈይሳ**

ኢትዮጵያን ጨምሮ በአብዛኞዎቹ የአፍሪካ አገራት ስፖርታዊ ውድድሮች ላይ እንደ ችግር ከሚነሱ ጉዳዮች መካከል አንዱ የዕድሜ ተገቢነት ነው፡፡ የዕድሜ ገደብ ባላቸው አህጉራዊም ሆነ ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ የሚስተዋል ችግርም በሳይንሳዊ መንገድ ተረጋግጦ በርካታ የአፍሪካ አገራትን ከጨዋታ ውጪ ሲያደርጋቸው በተደጋጋሚ ታይቷል፡፡ ኢትዮጵያም በዚሁ ችግር ውስጥ የምትገኝ አገር ስትሆን በውድድሮች ላይ በትክክለኛ ዕድሜያቸው የማይሳተፉ አትሌቶች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከተ፤ በጉዳዩ ላይ የሚደረገው ቁጥጥርም እንደላላ ቀጥሏል፡፡ በዚህም በትክክለኛ ዕድሜያቸው የሚወዳደሩ አትሌቶች ተጎጂዎች ሲሆኑ ስፖርቱም ተተኪ አልባ ሲሆን ተስተውሏል፡፡

ይህ አሳሳቢ የሆነ ጉዳይ በቅርቡ በተካሄደው 26ኛው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ትኩረት ከተሰጠባቸው አጀንዳዎች መካከል ቀዳሚው ነበር፡፡ የፌዴሬሽኑ የህክምና ባለሙያ ዶክተር አያሌው ጥላሁን በጉዳዩ ላይ ለጉባኤተኛው ገለጻ ሲያደርጉ፣ «የዕድሜ ተገቢነት ችግርን ሌላኛው የስፖርት አበረታች ቅመም ነው» በማለት የችግሩን አሳሳቢነት ተናግረዋል። በቅርቡ አሰላ ላይ በተካሄደው የታዳጊና ወጣት አትሌቶች ውድድር ላይ ከ95 በመቶ በላይ የሚሆኑ አትሌቶች ከዕድሜ በላይ የሆኑ እንደነበሩ የጠቆሙት ዶክተር አያሌው፣ የሚሊተሪ መሠረት ያላቸው የስፖርት ክለቦች ጭምር አትሌቶቻቸውን በእነዚህ ውድድሮች ላይ ማካፈላቸውን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በአትሌቲክስ ስፖርት እና በተተኪ ወጣቶች ቁጥር ከፍተኛ አቅም ያላት አገር ብትሆንም የዕድሜ ተገቢነት ግን አሁንም ችግር ሆኖ ቀጥሏል፡፡ ፌዴሬሽኑ ከ18 ዓመት እና ከ20 ዓመት በታች ዓመታዊ ውድድሮችን ሲያካሂድ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ያወጣበታል ነገር ግን ዓላማውን በትክክል ማሳካት አልቻለም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በዕድሜ ገደብ የሚካሄዱ ውድድሮች ላይ ክልሎችና ክለቦች ተገቢነቱን ሳይሆን ለሜዳሊያና የዋንጫ ተሸላሚነት ቅድሚያ ስለሚሰጡ መሆኑን ባለሙያው ጠቁመዋል።



**የዕድሜ ማጭበርበር ችግር ስፖርቱን፣ ተተኪ ስፖርተኞችንና አገሪቷን እየጎዳ ያለ ችግር ሆኗል፤**

እንደአገር በስፖርት ትምህርት ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ ባለሙያዎች ቢኖሩም በጉዳዩ ላይ ግን መፍትሄ የሚሆን ሃሳብ መሬት ማድረስም አልቻሉም፡፡ የሚመለከታቸው አካላትም ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው ምክንያትም ተተኪ አትሌቶች እንዲሁም አገር እየተጎዳች ስለመሆኗም ዶክተር አያሌው ይጠቁማሉ፡፡ ሁሉም ክልሎች ላይ ከ16፣ 18 እና 20 ዓመት በታች ፕሮጀክቶችና ማሰልጠኛዎች እያሉ ውድድሮች ላይ ግን በሚፈለገው ልክ ታዳጊዎቹ ተሳታፊ እየሆኑ አይደለም። ፌዴሬሽኑም ቢሆን ችግሩን ተመልክቶ ከማለፍ ባለፈ እርምጃ አለመውሰዱ ለዕድሜ አጭበርባሪዎቹ እንደማበረታቻ እየሆናቸው ነው፡፡ በመሆኑም ጠቅላላ ጉባኤው መፍትሄ ላይ መድረስ አሊያም ውድድሩን ማስቆም ተገቢ እንደሚሆን ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ምክትል ኮሚሽነር ጀኔራል ደራርቱ ቱሉም የዕድሜ ተገቢነት ሊቆም ያልቻለ አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑን ገልጻለች፡፡ ከዚህ ቀደም በታንዛኒያ ዳሬሰላም በተካሄደ ውድድር ላይ ኢትዮጵያ የተሻለ ውጤት ብታመጣም አትሌቶቹ ግን ከሌሎቹ የምሥራቅ አፍሪካ አገራት በዕድሜ ልቀው የታዩበት እንደነበር አስታውሳለች፡፡ ይህ ሁኔታ በሌሎች ውድድሮች ላይም የታየ እና ከስፖርታዊ አበረታች ቅመሞች ተነጥሎ ሊታይ የማይችል ማጭበርበርም ነው፡፡ ነፃ ስፖርት በእኩል ዕድሜና በዕኩል ዓይን መካሄድ ስለሚገባው ችግሩን መቅረፍ ተገቢ መሆኑንም አመላክታለች፡፡

ጉዳዩ በብሔራዊ ደረጃም ሆነ በምሥራቅ አፍሪካ፣ በአህጉርና ዓለም አቀፍ ደረጃ በሚካሄዱ ውድድሮች ላይ በስፋት የሚስተዋል መሆኑ በጠቅላላ ጉባኤውም ላይ አጀንዳ ሊሆን አስችሎታል፡፡ አትሌቶችን በውድድሮች ላይ የሚያሳትፉት ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ናቸው። እነዚህ አካላት ከፍተኛ ገንዘብ ወጪ አድርገው እና ረጅም ኪሎ ሜትሮችን አቋርጠው ለውድድር ከሄዱ በኋላ ማቋረጥና ወደመጡበት እንዲመለሱ ማድረግ ከባድ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ነገር ግን ከዚህ ዓመት ጀምሮ ችግሩ ካልተቀረፈ የፌዴሬሽኑ አቅጣጫ የሚሆነው ክለቦች የማይካፈሉበትን ውድድር፤ በአገሪቷ ባሉት ከ37 በላይ ፕሮጀክቶች እና ከ8 በላይ የማሰልጠኛ ማዕከላት መካከል ማካሄድ ነው፡፡ በመሆኑም ጠቅላላ ጉባኤው ይህንን እንዲገነዘብ በማድረግ ከዚህ በኋላም ችግሩ የማይቀረፍ ከሆነም ፌዴሬሽኑ መሰል ውድድሮችን እስከመሰረዝ የሚደርስ ውሳኔ ላይ መድረሱን በፕሬዚዳንቷ በኩል አስታውቋል፡፡

## የጨረታ ማስታወቂያ

በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሎካ አባያ ወረዳ ፍርድ ቤት በ2015 በጀት ዓመት ሊያሠራ ያቀደውን የዐቃቤ ህግ እና ፍርድ ቤት የቢሮ ህንፃ ቀሪ ሥራዎችን ለማሠራት ህጋዊ ተጫራቾችን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ማሠራት ይፈልጋል፡፡

**በዚሁ መሠረት**

1. ደረጃቸው GC-5/BC-6 እና ከዚያ በላይ የሆኑ የሥራ ተጫራቾች 2015 ዓ/ም የንግድ ሥራ ፍቃዳቸውን ያሳደሱ፣ የዘመኔን ግብር የከፈሉ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፣ ከፌደራሉ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ወይም አግባቢነት ካለው መንግስት ተቋሚ የታደሰ የብቃት መረጋገጫ ሰርትፍኬት ማቅረብ የሚችለ የተጨማሪ እሴት ታክስ /VAT/ ተመዝጋቢ የሆኑ እና የአቅራቢዎች ምዝገባ ምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
2. አስፈላጊውን የግንባታ ዕቃዎች፣ የሥራ መሳሪያዎች እና ሌሎች ሀብቶችን በግላቸው አቅርበው ግንባታውን መሥራትና ማጠናቀቅ አለባቸው፡፡
3. በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ ፕሮጀክቶችን ሠርቶ ለማስረከብ ከአሰሪ እና ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር ህጋዊ ውል ገብተው በስራ ወቅት ከአሰሪ መሥሪያ ቤት ወይም ከአማካሪ መሥሪያ ቤት ማንኛውም ዓይነት የሥራ አፈፃፀም መስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ሥራ ተቋራኞች የጨረታ ሰነድ መግዛትም ሆነ መወዳደር አይችሉም::
4. በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በዋናው ውል ስምምነት ገብተው ሦስትና ከዚያ በላይ ሥራ ጀምረው ያላጠናቀቁ (ያልጨረሱ) ተቋራጮች ጨረታውን መግዛት ሆነ መወዳደር አይችሉም፡፡
5. የሥራ ተቋራጮች ለውድድር ያቀረቡትን ብቃት (ቴክኒክ) መወዳደሪያ ሰነዶች ዋና (ኦርጅናል) ሲጠየቁ አቅርበው ማመሳከር አለባቸው፣ ይህ ተጣርቶ ኮፒው ከዋናው ጋር ተመሳክሮ ትክክለኛ ካልሆነ ተቋራጩ ከውድድር ውጭ ይሆናል፡፡
6. የጨረታ ማስከበሪያው (bid security) ብር 40,000,00 (አርባ ሺ ብር) በባንክ የተረጋገጠ ዋስትና /BANK GAURANTEE/ ወይም ክፍያ ማዘዣ (CPO) ከመጫረቻ ሰነድ ማቅረብ የሚችሉ::
7. የሥራ ተቋራጮች በተጫራቾች መመሪያ መሠረት ህጋዊ ፍቃዳቸውንና ተ.ዕ.ታ / VAT/ የተመገቡበትን ሠርተፍኬትና ታክስ ክሊራንስ በማቅረብ የጨረታ ዶክሜንቱን ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን አንስቶ ለ21 (ሃያ አንድ) ቀናት የማይመለስ ብር 400 (አራት መቶ ብር) በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሎካ አባያ ወረዳ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት በመክፈል ሰነዱን መውሰድ ይችላሉ፡:
8. የሥራ ተቋራጮች ከጨረታው መዝጊያ ቀን በፊት የግንባታን ቦታ በራሳቸው ወጪ አይተው ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
9. የጨረታ ሰነድ በተጫራቾች መመሪያ መሠረት ተሞልቶ የጨረታ ማስከበሪያ (bid security) ፋይናንሽያል አንድ ዋና (ኦርጅናል) እና ሁለት ኮፒዎችን እንዲሁም ቴክኒካል አንድ ዋና (ኦርጅናል) እና ሁለት ኮፒ ሰነዶችን በተለያየ ኤንቨሎፕ በሰም ለየብቻቸው ታሽጎ በአንድ ትልቅ ፖስታ ውስጥ ተከተውና በሁሉም ዶክሜንት ላይ ስምና አድራሻ በመፃፍ ህጋዊ የሆነ ማህተም በመምታት ይህ ማስታወቂያ ከመጣበት ቀን አንስቶ በ22ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 እስከ 6፡00 ሠዓት በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሎ/አ/ወ/ ፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት ለዚሁ አገልግሎት በተዘጋጀ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ የጨረታ ማስከበሪያው ከቴክኒካል ሰነድ ጋር አብሮ ማሸግ አለበት፡፡
10. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ከላይ በተራ ቁጥር 9 ላይ በተገለፀው ቦታ ከቀኑ 6፡00 ሰዓት ላይ ተዘግቶ ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ይከፈታል፡ ፡ አለመገኘት የጨረታው መክፈት አያግደውም፡፡
11. የአሠሪ መ/ቤት የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በክፍል ወይን ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
12. አሸናፊው ተጫራች በጨረታ ሰነዱ ላይ በተጠቀሰው መሠረት ለቅድመ ክፍያ በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ የባንክ ዋስትና ማቅረብ ይኖርበታል::
13. የጨረታው መዝጊያና መክፈቻ ቀን የሥራ ቀን ላይ ካልሆነ በሚቀጥለው የሥራ ቀን ከላይ በተገለው ቦታና ሰዓት ይሆናል::

**ሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሎካ አባያ ወረዳ ፍርድ ቤት**